መለያችን ኢትዮጵያዊነታችን!

# ግዮን

በየሳምንቱ ቅዳሜ

ግዮን ቅጽ 1 ቁጥር 37 ታህሳስ 2011 ዓ.ም ዋጋ 14.99

## ቦሎ የሚያስፈልጋቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች

## የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የሰሞኑ ውሎ



# የኦነግ አጣብቂኝ ‘በዳውድ ኦሮሚያ’ እና ‘በለማ ኢትዮጵያ’ መካከል



## “ኦነግ በኦሮሞ ሕዝብ ተገፍቶ መውደቁ አይቀርም”

መምህርና አክቲቪስት ስዩም ተሾመ



## “ ኦነግ መንግሥት ያለውን አልቀበልም፣ ሥርዓቱን በኃይል አፈርሳለሁ ካለ ስህተት ነው”

አቶ ኦልባና ሌሊሳ
(የኦፌኮ አመራር)

ግዮን


8 የኦነግ ታሪክን የመድገም አባዜ

9 አልጨበጥ ያለው ኦነግ ሸኔ
ተስፋዬ ሽብሩ

11 የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የሰሞኑ ውሎ

12 አርበኞች ግንቦት ሰባት በወቅታዊ ጉዳይ መግለጫ ሰጠ

13 ጀበና የመስበር ስነስርዓት በብሔራዊ ቤት መንግሥት !
አሌክስ አብርሃም

14 "ኦነግ በኦሮም ሕዝብ ተገፍቶ መውደቁ አይቀርም"



መምህርና አክትቪስት ስዩም ተሾመ

18 አዲሱ ድብቅ ጦርነት በምሥራቅ አፍሪቃ
ብሩክ መኮንን

19 የበዓሉ ግርማ ሕይወት እና ሥራዎቹ "መቃብሬ እንደ ሙሴ አይታወቅም"
ደረጀ ይመር




4

# የኦነግ አጣብቂኝ 'በዳውድ ኦሮሚያ' እና 'በለማ ኢትዮጵያ' መካከል

21 ቦሎ የሚያስፈልጋቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች
ተስፉ (ኢትዮጵያ) አልታሰብ

23 " ኦነግ መንግሥት ያለውን አልቀበልም፣ ሥርዓቱን በኃይል አፈርሳለሁ ካለ ስህተት ነው"



አቶ አልባና ሌሊሳ
(የኦፌኮ አመራር)

28 "ልውጥ" እና "ኢ-ልውጥ"
አቤል መንግሥተአብ





ቁጥር 36 ዕትም

ግዮን
ቀጣይ ዕትም
ቅዳሜ ታህሳስ
27
ይጠብቁን!

## የእርቀ ሰላም ኮሚሽን ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሪፐብሊክ 5ኛው የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት 4ኛ አመት የስራ ዘመን 14 መደበኛ ስብሰባው የእርቀ ሰላም ኮሚሽንን ለማቋቋም የወጣውን ረቂቅ አዋጅ አጸደቀ:: ምክር ቤቱ የውጭ ግንኙነትና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ እና የህግ የእርቀ ሰላም ኮሚቴ ለማቋቋም ያቀረበውን ሪፖርትና የውሳኔ ሀሳብ መርምሮ በ1 ድምፅ ታቅቦ በ1 ተቃውሞ በአብላጫ ድምጽ አፅድቆታል:: በሀገሪቱ ለበርካታ አመታት በተለያዩ ማህበረሰባዊና ፖለቲካዊ ግጭቶች ምክንያት በህዝቦች መካከል የተደራረቡ የቁርሾ ስሜቶችን ለማከም እውቀ እንዲኖር ለማድረግ የሚሰራ መሆኑ ተገልጿል::

## ከ120 ሺ ዶላር በላይ ሕገወጥ ገንዘብ ተያዘ

በሕገወጥ መንገድ ሲንቀሳቀስ የነበረ 120 ሺ በላይ የአሜሪካ ዶላር በብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ቁጥጥር ሥር ዋለ፡፡ ይህ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ.ከተማ በቁጥጥር ስር የዋለው ህገ ወጥ ገንዘብ በሀገሪቱ ምስራቃዊ ክፍል በቶጎ ጫሌ በኩል ከሀገር ሊወጣ የነበ መሆኑም ተገልጿል፡፡ በተጨማሪም ከአሜሪካ ዶላሮች ውጭ የተለያዩ ሀገር ገንዘቦችም ጭምር እንደነበሩበት ታውቋል፡፡

## የንግድና ኢንቨስትመንት ማሻሻያ መርሃ ግብር ተጀመረ

ጠቅላይ ሚንስትር ዐቢይ አሕመድ የኢትዮጵያን የንግድና የኢንቨስትመንት ከባቢ ሁኔታን ለማሻሻል የሚያስችል ብሔራዊ መርሃ ግብር አስጀምረዋል:: ብሄራዊ መርሃ ግብር በ10 አስፈፃሚ ተቋማት የሚተገበሩ 80 ልዩ ተግባራትን ይዟል:: ይህም የኢትዮጵያ የሥራ ፈጠራ መርሃ ግብር አካል ሲሆን ንግድን ለመጀመርና ለማሳደግ ኢትዮጵያ ያላትን ተወዳዳሪነት ይጨምራል ተብሎ ይታመናል:: በጠቅላይ ሚኒስትሩ ተቀማጣሪነት በጠ/ሚ ጽ/ቤት ፖሊሲና አፈፃፀም ክፍል ክትትል እየተደረገበት፣ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የሚያስተባብረው ይሆናል::

## በአፋር ክልል በተቀሰቀሰ ግጭጥ የአራት ሰዎች ሕይወት አለፈ

በአፋር ብሔራዊ ክልል እንድፎ በተባለ ልዩ ቀበሌ ውስጥ በተቀሰቀሰ ግጭት አራት ሰዎች መገደላቸውን 13 ሰዎች መቁሰላቸው ታወቀ:: ታህሳስ 15 ቀን 2011 ዓ.ም ሌሊት በተቀሰቀሰውና እስከ ማክሰኞ ረፋድ በዘለቀው ግጭት ሳቢያ ወደ ትግራይና አዲስ አበባ የሚጓዙ ተሽከርካሪዎች መንገድ ተዘግቶባቸው እንቅስቃሴያቸው ተቋርጦ መቆየቱ ተሰምቷል:: ግጭቱ በቀበሌው ውስጥ ከሳምንት በፊት የሕዝብ የተቃውሞ ሠልፍ ከተካሄደ በኋላ እየተባባሰ እንደመጣ መረዳት ተችሏል:: የተቀሰቀሰውን ግጭት ለማርገብ የአፋር ክልል ልዩ ኃይል ወደ ቀበሌው መግባቱንና ከታጠቁ ግለሰቦች ጋር ተኩስ መለዋወጡን የአካባቢው ነዋሪዎች ገልፀዋል::

በግጭቱ ወቅት የአፋር ብሔራዊ ክልልን ሰንደቅ ዓላማ በማውረድ የሶማሌ ክልልን ሰንደቅ አላማ ለመስቀል የሞከሩ ሰዎች እንደነበሩ ነዋሪዎቹ አስታውቀዋል::

## የጎዳና ነጋዴዎች ወደ ሕጋዊ የንግድ ሥርዓት እየገቡ ነው

በተፈቀደላቸው ቦታ ላይ ብቻ በሕጋዊ መንገድ ለመነገድ ከተመዘገቡ 38 ሺ 675 የጎዳና ላይ ነጋዴዎች መካከል 10 ሺ 137ቱ ሕጋዊ የንግድ ሥርዓት ውስጥ ገብተው መነገድ መጀመራቸውን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ አስታወቀ፡፡

ቢሮው ባመቻቸው የንግድ ሥርዓት ውስጥ ለመግባት ካለፈው ዓመት መጋቢት ወር አንስቶ እስከ ጥቅምት ወር 2011 ዓ.ም ድረስ በደንቡና መመሪያው መሠረት መታቀፍ የሚጠበቅባቸው 27ሺ 735 የጎዳና ላይ ነጋዴዎች ተመዝግበዋል፡፡

በዘጠኝ ወራት ውስጥ በደንቡና መመሪያው መሠረት መታቀፍ የሚጠበቅባቸውን ከ27ሺ በላይ የሚሆኑ የጎዳና ላይ ነጋዴዎችን እንዲሁም ከመመሪያውና ደንቡ ውጪ የሆኑና የነዋሪነት መታወቂያ የሌላቸው ከ10ሺ በላይ የሚሆኑ ነጋዴዎችን በተጨማሪነት መመዝገቡም ተጠቁሟል፡፡

## 4 አየር መንገዶች የኢትዮጵያን የበላይነት ለመቀናቀን ጥምረት ሊፈጥሩ ነው

አራት የአፍሪቃ መንገዶች በመጪዎቹ 2 ወራት ውስጥ በአፍሪቃ የመጀመሪያ የሆነውን የሲቭል አቭየሽን ጥምረት ለመመስረት ማቀዳቸው ታውቋል፡፡ አራቱ አየር መንገዶች የሞሪሸስ፣ የደቡብ አፍሪቃ፣ የሩዋንዳ እና የኬንያ ሲሆኑ ዓላማቸው አንድ መሆኑ ተገልጿል፡፡ አየር መንገዶቹ አዳዲስ አሰራሮችን በመከተል በአህጉሪቱ የኢትዮጵያ አየር መንገድን ብቸኛ የበላይነት መመከትና ኩባንያዎቻቸውን ማበልፀግ ጭምር መሆኑ ታውቋል፡፡

የኬንያ መገናኛ ብዙኃን ታህሳስ 15 ቀን 2011 ዓ.ም ባሰራጩት ዘገባ መሰረት የአየር መንገዶቹ መጣመር የወጪ ቅነሳ እንዲያገኙ ከማስቻል ባሻገር የተሳለጠ የበረራ ማዕከል ለመፍጠር እንዲሁም የኮድ ሼር ስምምነት በማድረግ በርካታ መዳረሻዎችን ለማስፋፋትና የኢትዮጵያ አየር መንገድንና ከአፍሪቃ ውጭ ያሉትን ኩባንያዎች በመሮኳከር በአፍሪቃ ያላቸውን ተደራሽነት ማስፋፋት፣ በጥምረታቸው ለማሳካት ከሚፈልጓቸው መካከል የሚጠቀሱት መሆናቸው ታውቋል፡፡

## ኢትዮጵያ የኦንላይን ኢንቨስትመንት መመሪያ ይፋ አደረገች

ኢትዮጵያ ከታህሳስ 21 ቀን 2018 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ የሚደረግ በድረ ገፅ የተደገፈ አዲስ የኦንላይን ኢንቨስትመንት መመሪያ ይፋ አደረገች፡፡ ኢትዮጵያ ከማዳጋስካርና ሞሪሸስ በመቀጠል የኦንላይን ኢንቨስትመንት መመሪያ ይፋ ያደረገች ሰባተኛዋ የአፍሪቃ አገር ስትሆን መመሪያው በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን በተመድ የአፍሪቃ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን እና በተመድ የንግድ ልማት ኮንፈረንስ ድጋፍ የተዘጋጀ ሲሆን አላማውም ውጤታማ ኢንቨስተሮችን ወደ አገሪቱ ለመሳብ እንደሆነ ተገልጿል፡፡

## በሊቢያ የተገደሉት 34 ሰዎች አፅም ተገኘ

ከ3 ዓመት በፊት በፅንፈኛው ቡድን አይ ኤስ አንገታቸውን ተቀልተው እና በጥይት ተደብድበው ሕይወታቸው ያለፈ 34 ኢትዮጵያውያን አፅም ተገኘ:: የሊቢያ መንግሥት አይኤስ በአሰቃቂ ሁኔታ ሕይወታቸው ያለፈውን ኢትዮጵያውያን አፅም ማግኘቱን ያስታወቀ ሲሆን አፅማቸው የተገኘውም ባሳለፍነው እሁድ እለት ነበር:: አፅማቸው በጅምላ መቃበሩ ቦታ የእርሻ ማከናወኛ ሳይሆን እንዳልቀረ ተገምቷል:: ሕጋዊ አካሄድን ተከትሎ በቅርብ ወደ ሀገር ቤት ይመለሳል ተብሎ ይጠበቃል::

## ኦዴፓ በኦሮሚያ ለተከሰተው ግጭት ኦዴፓ ገለጸ

የኦሮሞ ነጻነት ግንባር (ኦነግ) እና የኦሮሞ ዴሞክራቲክ ፓርቲ (ኦዴፓ) መካከል የተደረጉ ስምምነቶች እንደነበሩ ይታወሳል:: ነገር ግን ኦዴፓ ኦነግ አሁን በኦሮሚያ የተለያዩ አካባቢዎች በተፈጠሩና ለሚፈጠሩት ችግሮች ምክንያት እንደሆነ ገለፀ:: የኦዴፓ ጽ/ቤት ኃላፊ የሆኑት ዶ/ር ዓለሙ ስሜ ጨምረው እንዳብራሩት ከሆኑ በሁለቱ ፓርቲዎች መካከል የተደርሰውን ስምምነት የጣሰው ኦነግ ነው ሲሉ በአንጻሩ በኦነግ በኩል ደግሞ በቅድመ ስምምነት ላይ ቃል የተገባላቸው የመኪና እና የቤት ጥቅማ ጥቅሞች እንዳልተከበረላቸው ተናግረዋል::

## የሕዳሴው መሐንዲስ መጽሐፍ በገቢያ ላይ ዋለ

በ 30 ምዕራፍ የተከፋፈለው እና በ202 ገጽ የተቀነበበው ይህ መጽሐፍ በጃፋር መጻሕፍት መደብር አከፋፋይነት በ150 ብር ለገቢያ ቀረበ::እውነተኛው የሕዳሴው መሐንዲስ ታላቁ የኢትዮጵያ ንጉሥ አጼ ቴዎድሮስ እንደሆኑ የሚያትት መጣጥፍን ጨምሮ ሌሎች ማኅበራዊ፣ፓለቲካዊ እና ፍልስፍናዊ ይዘቶችን የሚዳስሱ መጣጥፎች ፣ እንዲሁም አዝናኝ ወጎች እና አጫጭር ልበወለዶችን መጽሐፉ በውስጡ አካቶ ይዟል::

## በሳዑዲ ታስረው የነበሩ ኢትዮጵያውያን ወደ ሀገራቸው ተመለሱ

በቅርቡ ከመጣው ለውጥ ጋር ተያይዞ በውጭ ሀገር የሚኖሩና በእስርና በእንግልት ላይ የነበሩ በርካታ ቁጥር ያላቸው ኢትዮጵያውያን ወደ ሀገራቸው በሰላም እንዲመለሱ መደረጋቸው ይታወሳል:: ከሰሞኑ በሳዑዲ ማረሚያ ቤት ታስረው የነበሩ 451 ኢትዮጵያውያን ወደ ሀገር ቤት ተመልሰዋል:: እነዚህ ተመላሽ ኢትዮጵያውያኑ በጄዳ፣ በጂዛን እና አካባቢዋ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ታስረው የነበሩ መሆናቸው ተገልጿል::

## ካሣ ተክለብርሃን ከአምባሳደርነታቸው ተነሱ

የፌዴራል ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ኮሚሽነርና የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ኃላፊ በመሆን ሲያገለግሉ የነበሩት አቶ ፍጹም አረጋ በአሜሪካ የኢትዮጵያ ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደር ሆነው ተሹመዋል:: አቶ ፍጹም አረጋ የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ኃላፊ ሆነው በሚሠሩበት ጊዜ የማኅበራዊ ሚዲያን በተለይ ቲውተርን በመጠቀም የጽ/ቤቱን የዕለት ተዕለት የሥራ እንቅስቃሴን በተገቢው ፍጥነት ለሕዝብ በማድረስ ስኬታማ እንደነበሩ ይታወቃል::ከዚህ ኃላፊነታቸው ተነስተው በተመደቡት አዲሱ የሥራ ዘርፍ የወራት ዕድሜ ቆይተው ነው ሌላ ሹመት ያገኙት::

አቶ ፉጹም አረጋ የተኳቸው አምባሳደር ካሳ ተክለብርሃን ከዚህ ቀደም በዲያስፓራው ማኅበረሰብ ዘንድ ከፍተኛ ተቃውሞ ሲደርስባቸው እንደነበር ይታወቃል:: የቀድሞውን የብአዴን አመራር የነበሩት አምበሳደር ካሣ በሕወሓት/ኢሕአዴግ አስተዳደር ውስጥ ቁልፍ ሚና ከነበራቸው ሹመኞች መካከል ዋንኛው ነበሩ:: የሕወሓት ኢሕአዴግ አገዛዝ በትውልደ ኢትዮጵያዊያን በተለይ በሰሜን አሜሪካ ከፍተኛ ቅዋሜ ይደርስበት እንደነበረ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው:: በተለይ የዶላር ዕቀባን በማስተባበር ከፍተኛ ድርሻ የነበራቸው የዲያስፓራው አካላት ዋንኞቹ ነበሩ:: የአሁኑ ሹም ሽር አዱሱን የዶ/ር ዐቢይ አሕመድ አስተዳደር ከዲያስፓራው ጋር የጀመረውን የእርቅ መንገድ ይበልጥ ያቃናዋል ተብሎ ይጠበቃል::በተለይ በቅርቡ የውጪ ምንዛሬ እጥረትን ለመቅረፍ የተከፈተው የዲያስፓራ ፈንድ ላይ አዲሱ አምባሳደር ሊኖራቸው የሚችለው ሚና የጎላ እንደሚሆን እሙን ነው::እሳካሁን በትረስት ፈንዱ አማካኝነት ሊሰበሰብ የታሰበው የውጪ ምንዛሬ የተገመተውን ያህል እንዳልሆነ መዘገቡ ይታወሳል::

## ጋዜጠኛና መምህር ደምስ በለጠ አረፉ

ከ30 ዓመታት የስደት ሕይወት በኋላ ወደ አገሩ የተመለሰው አንጋፋው የዩኒቨርስቲ መምህርና ጋዜጠኛ ደምስ በለጠ ታህሳስ 13 ቀን 2011 ዓ.ም ሕይወቱ አልፏል::

ጋዜጠኛና መምህር ደምስ በአዲስ አበባ ከተማ ነው የተወለደው:: የነፃ ትምህርት እድል በማግኘት ወደ ሶቪየት ሕብረት አምርቶ ጎርኪ የሥነ ፅሁፍ ኢንስቲትዩትን በመቀላቀል ትምህርቱን ተከታትሏል:: እስካሁን ድረስ በታዋቂው የጎርኪ የስነ ፅሁፍ ኢንትስቲትዩት ውስጥ ከተማሩት ሁለት ኢትዮጵያኖች መካከል ደምስ አንዱ ሲሆን ሌላኛው ፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሳ ናቸው::

ከ32 ዓመት በኋላ በቅርቡ ወደ አገሩ የተመለሰው ጋዜጠኛና መምህር ደምስ ለረጅም ዓመታት የኖረው በአሜሪካ ነው:: በእነዚህ የስደት ዓመታት ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር በነበረው የፖለቲካ ልዩነት ሳቢያ ወደ አገሩ መመለስ ሳይችል ቀርቷል:: ጋዜጠኛ ደምስ በለጠ "የአማራ ድምጽ ራዲዮ" ዋና አዘጋጅና የመጀመሪያ ኢትዮጵያዊ የኢንተርኔት ሬዲዮ ባለቤትም ነበር:: ባልታወቀ ምክንያት ቅዳሜ ታህሳስ 13 ቀን 2011 ዓ.ም ሕይወቱ አልፎ ታህሳስ 15 ቀን 2011 ዓ.ም በቅድስተ ሥላሴ ካቴድራል የቀብር ሥርዓቱ ተፈፅሟል::

## ለመንግሥት ፕሮጀክቶች ረቂቅ ደንብ ተዘጋጀ

የመንግሥት ፕሮጀክቶች አስተዳደርና አመራር ሥርዓትን በግልፅ ለማስቀመጥ የሚያስችል ረቂቅ ደንብ ተዘጋጀ፡፡ረቂቅ ደንቡ በስኳር ፣በባቡር፣ በማዳበሪያና እና በኃይል ማመንጫ እንዲሁም መንገድና መስኖን በመሳሰሉ የመንግሥት ፕሮጀክቶች ላይ ከፍተኛ የጊዜና የበጀት መናር ችግር ያለ ሲሆን ፕሮጀክቶቹ አዋጭነታቸው በውል ሳይታወቅ በፖለቲካ ውሳኔ ጭምር ይተገበሩ ነበር፡፡የሕግ ማዕቀፍ አለመኖሩም ኪሳራውን እንዳባባሰው ተገልጿል፡፡ ከነዚህ ችግሮች ምክንያት በመነሳት የወጣው ረቂቅ ደንብ በፕላንና ልማት ኮሚሽን የተዘጋጀ ሲሆን ከአሠራርና አደረጃጀት አንፃር የሚስተዋሉት እነዚህን ችግሮች ይቀርፋል ተብሎ ታስቧል፡፡

## ፕሬዚዳንት ሣህለወርቅ ለመጀመሪያ ጊዜ የአምባሳደርነት ሹመት ሰጡ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት ሣህለወርቅ ዘውዴ ኢትዮጵያን በውጭ ሀገሮች ለሚወክሉ 20 አምባሰደሮች ሹመት ሰጡ፡፡ በዚሁ መሰረት፡-

1. አቶ ዘነበ ከበደ
2. አምባሳደር ሱሌይማን ደደፎ
3. ወ/ሮ ሙሉ ሰለሞን
4. አቶ አብዱልአዚህ መሐመድ
5. ወ/ሮ ናሲሴ ጫሊ
6. አቶ ሐሰን ታጁ
7. አቶ ረታ አለሙ
8. አቶ ሄኖክ ተፈራ
9. ወ/ሮ አለምፀሐይ መሰረት
10. ዶ/ር ትዝታ ሙሉጌታ
11. አምባሳደር ተስፋዬ ይልማ
12. አምባሰደር ተሾመ ቶጋ
13. አቶ ተፈሪ ታደሰ
14. አቶ ፍፁም አረጋ
15. ዶ/ር አዲሱ ገ/እግዚአብሄር
16. አቶ ሚሊዮን ሳሙኤል
17. አቶ መለስ አለም
18. ኦቶ ብርሃኔ ፍስሐ
19. ዶ/ር አይሮራት መሐመድ
20. አምባሳደር ሳሚያ ዘካርያ

በባለሙሉስልጣን አምባሰደርነት ተሹመዋል፡፡

# የኦነግ አጣብቂኝ ‘በዳውድ ኦሮሚያ’ እና ‘በለማ ኢትዮጵያ’ መካከል

መላክ ቢ.

የኦሮሞ ነጻነት ግንባር (ኦነግ) ትግል ግማሽ ምዕተ ዓመት አስቆጥሯል። ለኦሮሞ ሕዝብ በመታገል ረገድ ኦነግ ቀዳሚውን ቦታ ይይዛል። ኦነግ ትግል ሲጀምር አሁን ያለው የብሔር ድርጅቶች ጥምረት (አሕአዴግ) ቀርቶ በ1967 የተመሠረተው የአሕአዴግ አባት ሕዝባዊ ወያነ ሃርነት ትግራይም አልተፈጠረም። ከኦነግ ጋር ተመጣጣኝና አንጋፋ የትግል ታሪክ ያለው ድርጅት ሻዕቢያ ብቻ ነው።

አብሮት የታገለው ሻዕቢያ ኤርትራን ከደርግ አገዛዝ ነጻ ሲያወጣ ፣ ከርሱ ኋላ የተፈጠረው ሕወሓት/አሕአዴግም ሥልጣን ሲይዝ ነው ኦነግ በኢትዮጵያ ሽግግር መንግሥት አካል እንዲሆን የቀረበለትን ጥሪ ተቀብሎ ወደአዲስ አበባ የገባው። በጊዜው የማስመሰል ፖለቲካ ጨዋታ ላይ የነበረው የአቶ መለስ ዜናዊ አስተዳደር ጠመንጃ ያለውንና በተነጻጻሪ ብዛት ያለው ሰራዊት ያሰለፈውን ኦነግን ጉልበት ለማሳጣት አንዳንድ አባላቱን በመንግሥት ሥልጣን ላይ ካስቀመጠ በኋላ ሰራዊቱን ግን ካምፕ አስገብቶ አቀለጠበት። የሽግግር መንግሥቱን ቻርተር ሐሳብ ያቀረብነው እኛ ነን ያለው ኦነግ ፣ ሕገመንግሥቱንም ያረቀቅነው እኛ ነን ያለው ኦነግ ይህንን ምክንያት ይዞ ራሱን ከሽግግር መንግሥቱ በማግለል ወደትጥቅ ትግሉ ተመለሰ። ከዚያ በኋላ የነበሩትን ጊዜያት ብዙም ማሰብ አያስፈልግ ይሆናል። ምክንያቱም ኦነግ የዳውድ ኢብሳና የሌንጮ ለታ፣ የገላሳ ዲልቦ እና የከማል ገልቹ በሚባሉ ትንንሽ ኦነጎች ተከፋፍሎ አንድነቱ ፈራርሷል። የሰራዊቱ ቁጥር ተዳክሞና ኃይሉም ላልቶ በኤርትራ በረሃ ውስጥ መሽጎ አንዲትም ጥይት ሳይተኩስ ኖሯል።

ይህ ድርጅት ኦብነግም ተባለ ኦነግ፣ ኦዴግም ተባለ ሸኔ ያው የኦሮሞን ሕዝብ ትግል ሀ ብሎ የጀመረ አንጋፋ ድርጅት እንደመሆኑ በመላው ኦሮሞ ዘንድ ትልቅ ሥፍራ ያለው ድርጅት ነው። የኦሮሞ ሕዝብ በአሕአዴግ ከሁለት ዐሥርተ ዓመታት በላይ የተሰቃየው፣ የተገረፈው እና የተገደለው ኦነግ ነህ እየተባለ ነው። “ሁሉም ኦሮሞ ሲፋቅ ኦነግ ነው” ያለው ሕወሓት/አሕአዴግ ኦሮሞ የተባለውን ሁሉ ከኦነግ ጋር አዳብሎ መክሰሱ እና መውቀሱ ህዝቡ ኦነግን እንደወኪል ፓርቲው እንዲቆጥርና ለትግሉም ራሱን አሳልፎ እንዲሰጥ ምክንያት ሆኗል።

ብዙዎች የክልሉ ወጣቶች ኦሮሞን ነጻ ለማውጣት በሚደረገው ትግል ውስጥ ለመሳተፍ ኦነግን በረሃ ድረስ እየሄዱ ተቀላቅለውታል። በቀላል አማርኛ የኦሮሞ ሕዝብ አጠገቡ ያለውን እና በሕወሓት የተፈበረከውን ‘ኦሕዴድን’ ወደጎን ብሎ ኦነግን ድርጅቴ በማለት መጠጋቱ በሁለቱ መካከል ከፍ ያለ መቀራረብ እንዳለ ማሳያ ነበር።

ኦነግ የትግል ስልቱ ወደውጤት ሊያቀርበው ሳይችል መስራቾቹም የታገሉለት ዓላማ ግብ መትቶ ሳያዩ አልፈዋል። በኦነግ ስም ታርጋ እየተለጠፈባቸው ለብዙ ስቃይና እንግልት የተዳረጉት የቀድሞው ኦሕዴድ አባላት ቀስ እያሉ የቲም ለማን አሰላለፍ ተጠቅመው አሕአዴግን ከሥር ንደውታል። ከዚህ በኋላም የኦሮሞ ሕዝብ ለነጻነቱ ያደረገው ትግል ፍሬ አፍርቶ አለማየቱና በተለይም ከድህነት መውጣት አለመቻሉን በመገንዘብ ይህቺን ሀገር እንደአልቅት ተጣብቷት በሙስና እና ሰብኣዊ መብት ጥሰት ሲናውዝ ከኖረው ሕወሓት አላቅቀውታል።ብዙዎች እንደሚናገሩትም የእነዶ/ር ዐቢይ ትግል ሕዝቡን ብቻ ሳይሆን የፖለቲካ ፓርቲዎችንም ነጻ ያወጣ ነው።

በውጭ ሀገራት የሚኖሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ወደ ሀገር ውስጥ ተመልሰው በመምጣት በሰላማዊ መንገድ እንዲታገሉ የቀረበላቸውን ጥሪ ተቀብሎ ወደ ሀገር ውስጥ ለመግባት ያልቻለው ኦነግ ወደ ሰላማዊ መድረክ የመጣው እነ አቶ ለማ መገርሳ ማዘዣ ጣቢያው ወደ ነበረው የኤርትራ በረሃዎች ድረስ ሄደው ካነጋገሩት በኋላ ነበር።

## ያልታወቀው ስምምነትና የኦነግ እሺታ

ብዙዎች ኦነግን ሲተቹ እንደሌሎች ያለትጥቅ ትግልም ፣ በትጥቅ ትግልም ተሰማርተው የነበሩ ድርጅቶች ዶክተር አብይ የቀረቡትን የሰላማዊ ትግል ጥሪ ተቀብለው አዲስ አበባ ሲገቡ ኦነግ ግን በኤርትራ በረሃ ላይ መሽጎ ዝም ማለቱ ሰላም ወዳድነቱን አያሳይም ብለዋል። ከማንም ድርጅት በተሻለ ከኦሮሚያ የወጡት የለውጥ ሃይሎች ለኦነግ ይቀርባሉ የሚሉት ተቺዎች ሌሎች እነርሱን አምነው ሲመጡ ኦነግ ግን ማንገራገሩ የድርጅቱን ለሰላም ደንታቢስነት ያሳያል ብለው ወቅሰውም ነበር። ከተቺዎቹ ወቀሳ ▶



*አቶ ዳውድ ኢብሳ እና አቶ ለማ መገርሳ በኤርትራ በድርድሩ ወቅት*

በላይ ኦነግ ቶሎ ምላሽ ላለመስጠቱ እና የተለየ ድርድር ለመፈለጉ ምክንያት ግን በ1984 ዘመነ አሕአዴግ ያየው እባብ ዛሬ ድረስ በልጥ እንዲደነገጥ ያደረገው መሆኑና ከመንግስት ተጠግቶ የመስራት እምነቱንም ስለሸረሸረው መሆኑ ሚዛን ይደፋል። በርግጥም ኦነግ አገር ሰላም ብሎ ለመንግስት ያስረከበውን ሙሉ ጦር ህወሃት/አሕአዴግ በካምፕ አጉሮ እስረኛ ከማድረጉ ባሻገር ረሽኗል መባሉ ኦነግ አምኖ መጠጋቱ ያስከፈለው ዋጋ በመሆኑ የቲም ለማን ቃል አሁንም ቢጠራጠር ሳይፈረድበት ይችላል።

ለብዙዎች ግራ የሆነው ነገር ግን ከኦነግ ጋር ለመደራደር አስመራ ድረስ በመሄድ ኢሳያስ አፈወርቂ ባሉበት አቶ ለማ መገርሳ፣ ዶክተር ወርቅነህ ገበየሁ ከአቶ ዳውድ ኢብሳ ጋር ያደረጉት ስምምነትና የደረሱበት ውል ምን እንደሆነ ያለመገለጹ ነው። ይህ ስምምነት ለሕዝብ ይፋ አለመሆኑ በራሱ ችግር ሆኖ በባሰ ሁኔታ ደግሞ በአሁኑ ወቅት በሁለቱ ድርጅቶች መካከል ላለው ውጥረት እንደመነሻ ምክንያት ሆኗል።

ለኦነግ አባላት መኪና ቤት እና መገልገያ ለመስጠት የተገባው ቃል አልተፈጸመም ተብሎ ከሚናፈሰው ያልተረጋገጠ መረጃ ባሻገር ኦነግ ራሱ አልተከበሩም ያላቸውን ስምምነቶች ዘርዝሯቸዋል። ከመንግሥት ጋር በተደረሰው ስምምነት የፀጥታ ኃይሉ ገለልተኛ እንዲሆን የኦነግ ሰራዊት በፀጥታ መዋቅር እንዲካተት እና ይህንን የሚሠራ ኮሚቴ እንዲቋቋም ከስምምነት እንደተደረሰ ነው አቶ ዳውድ ኢብሳ የሚናገሩት ።

በአሁኑ ወቅት ግን ከመንግሥት በኩል የተገባው ስምምነት እየተጣሰ መሆኑንና በሥልጠና ላይ ያሉ የኦነግ ሰራዊት በአመራር አባላት እንዲጎበኙ አለመፍቀድ ጉዳዩን ለውጥረት እንደዳረገው ነው የተገለጸው።

> **ኦነግ የዳውድ ኢብሳና የሌንጮ ለታ፣ የገላሳ ዲልቦ እና የከማል ገልቹ በሚባሉ ትንንሽ ኦነጎች ተከፋፍሎ አንድነቱ ፈራርሷል። የሰራዊቱ ቁጥር ተዳክሞና ኃይሉም ላልቶ በኤርትራ በረሃ ውስጥ መሽጎ አንዲትም ጥይት ሳይተኩስ ኖሯል**

አቶ ዳውድ የመከላከያ ሰራዊት የኦነግ ታጣቂዎች ባሉበት አካባቢ መስፈሩ ግጭት እንዲከስት ምክንያት መሆኑንም በዚህ ሳቢያም በምእራብ ወለጋ በመከላከያ ኃይል እና በኦነግ ታጣቂዎች መካከል ግጭት መፈጠሩንም ተናግረዋል። አሁንም መንግሥት በክልሉ ሰላም እንዲኖር ቁርጠኛ አቋም ካለው የኦሮሞ ነፃነት ግንባር ከመንግስት ጋር ለመነጋገር ዝግጁ ነው በማለት ዳግም ስምምነት እንደሚያስፈልግ ጠቆም አድርገዋል አቶ ዳውድ።

## ኦነግ ዳግም ወደተኩስ?

የአቶ ዳውድ ኢብሳ መግለጫ ላይ የተካተተው "ሰራዊቱ ራሱን እንዲከላከል ትዕዛዝ ተሰጥቷል" የሚል ቃል ሁለቱ ፓርቲዎች በግልጽ ወደ ጦርነት መግባታቸውን አመላካች ነበር። አቶ ዳውድ እንዳሉት መንግሥት የኦነግ ወታደሮችን አያያዝ በተመለከተ የገባውን ቃል እያከበረ ባለመሆኑ ሰራዊቱ ቅሬታ ገብቶታል። በተለይም በምግብ እና በሥልጠናው ላይ በተጨማሪም አመራሮች እንዳያዩት በመከልከሉ ላይ ከባድ ቅሬታ ውስጥ በመግባቱ ሳቢያ አምጿል። ተተኩሶበታል። ይህ ደግሞ በሌላ አካባቢ በተከማቸው የድርጅቱ ጦር በመሰማቱ ረብሻ መነሳቱን አቶ ዳውድ አልካዱም። "ማሰልጠኛ ለገቡት የኦነግ ታጣቂዎች ከሚቀርበው ምግብና ተገቢ አያያዝ እንዲሁም በስልጠና የሚቆዩበት ጊዜ በውል ካለመታወቁ ጋር ተያይዞ ቅሬታዎች መቅረባቸውንና በመንግሥት የተገባው ቃል

አልተፈጸመም” ይላሉ አቶ ዳውድ፡፡

ኦነግ ወደሃገር ቤት ሲገባ በባሌ እና በመቀሌ የገቡ የታጠቁ ወታደሮቹን ይዞ ነው፡፡ በአንዳንዶች ግምት 40 ሺህ በሌሎች ደግሞ 25 ሺህ አካባቢ ይሆናሉ ተብለው የሚገመቱት የኦነግ የታጠቁ ወታደሮች በስምምነቱ መሠረት ትጥቅ እንዲፈቱ ጥያቄ ሲቀርብ ከኦነግ በኩል የስምምነታችን አንድ አካል አይደለም የሚል ተቃውሞ ቀርቦ ነበር፡፡ ሊቀመንበሩ ዳውድ ኢብሳ በጋዜጠኞች ሲጠየቁ “ትጥቅ ፈቱ መባል አንፈልግም፣ይህ አባባል አንዱ አስፈቺ ሌላው ፈቺ ያስመስለዋል” በማለት ወታደሮቻቸው ትጥቅ እንዲፈቱ አለመፈለጋቸውን ተናግረው ነበር፡፡ ይህም እንደብዙዎች ገለጻ ኦነግ በ1984 የገጠመው ዓይነት ችግር እንዳይደርስበት ሰግቶ ነው ሲሉ ድርጅቱ ለሰላም ሙሉ በሩን አለመክፈቱንና በዚህ አጋጣሚ ተጠቅሞ ወደሥልጣን ለመንጠላጠል ፈልጎ ነው ያሉም አልታጡም፡፡

ኦነግ በሰላማዊ መንገድ በፓርቲነት ተመዝግቦ ውድድር እንዲያደርግ ተስማምቶ የመጣ ፓርቲ እንደመሆኑ ወታደር አያስፈልገውም፡፡ ወታደሮቹ በስምምነቱ መሰረት ተገቢው የተሃድሶ ሥልጠና ተሰጥቷቸው ወደክልሉ ፖሊስና ወደፌዴራሉ ልዩ ሃይል እንደሚጠቃለሉ ተነግሯቸዋል፡፡ በዚህ መሰረትም 1300 ወታደሮች ሻሸመኔ አካባቢ በሚገኝ አርዳይካ በሚባል ካምፕ ውስጥ ገብተው ሥልጠና በመውሰድ ላይ ሳሉ ነው ኦነግ መብታቸው አልተከበረም ብሎ መግለጫ ያወጣው፡፡ ከዚያ በፊት በነበሩት ጊዜያት በምዕራብ ኦሮሚያ ያለውና የታጠቀው ኃይል (የኦነግ ኃይል እንደሆነ  የሚነገረው) ከኦሮሚያ ፖሊስ ጋር ሰፊ ግጭት ላይ ሰንብቶ ብዙ ጉዳት አድርሶ ነበር፡፡ ያ ብቻ ሳይሆን የመንግሥት መዋቅርን አፈራርሶ አካባቢውን እንደነጻ መሬት ተቆጣጥሮ ከፌዴራል ኃይል ጋር ሳይቀር ሲታኮስ ቆይቷል፡፡ ለምሳሌም ቦረና አካባቢ ሞያሌ ድንበር ላይ የተከማቸው የኦነግ ኃይል ብዙ ጥፋቶችን ፈጽሟል፡፡ ሰሜን ሸዋ ወረጃርሶ ወረዳ ላይ ባለፉት ቀናት ሲዋጋ ቆይቷል፡፡ ነቀምትና ወለጋ ዙሪያ  ባሉት ሻምቦ እና  ደምቢዶሎ ወረዳዎች ከመከላከያ ሰራዊት ጋር ተታኩሷል፡፡

የኦሮሚያ ፖሊስ ኮሚሽነር ጄኔራል ሲናገሩ በምዕራብ ኦሮሚያ የተፈጠሩ ችግሮችን በውይይትና በሰከነ መንገድ በሰላማዊ ሁኔታ ለመፍታት ላለፉት ስድስት ወራት ጥረት ሲደረግ ቢቆይም የከፋ ዋጋ ማስከፈሉን ተናግረው ባለፉት አራት ወራት ብቻ በክልሉ በተፈጠሩ ችግሮች 29 ንጹሃን ዜጎች ሕይወት መጥፋቱን የገለጹት ከሚሽነሩ የዜጎችን ደህንነት የሚያስጠብቁ ሁለት የዞን መምሪያ ኃላፊዎችን ጨምሮ 12 የፖሊስ አባላት ሕይወት ማለፉንም ገልጸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም 77 የፖሊስ አባላት እና 40 ሚሊሻዎች መቁሰላቸውን ነው የገለጹት፡፡

በቄለም ወለጋ እና ምዕራብ ወለጋ 2 ሺህ 72 ክላሽንኮቭ መሳሪያዎች ከፖሊስ ተዘርፈዋል ያሉት ኮምሽነር አለማየሁ፥ በምዕራብ ወለጋ ከመንግሥት ካዝና ከ3 ሚሊየን ብር በላይ ተዘርፏል ብለው ነበር፡፡ በምዕራብ ኦሮሚያ ለተከሰቱት ችግሮች ተጠያቂ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር (ኦነግ) ታጣቂዎች መሆናቸውን የተናገሩት ኮሚሽነሩ፥ የኦነግ አመራሮች በአስመራ ከተማ ከኦዴፓ አመራሮች ጋር ስምምነት ላይ መድረሳቸው አስታውሰዋል፡፡

በአዲስ አበባም የኦነግ አመራሮች በሚያደርጉት ውይይት የሰላማዊ ትግል

> “...እንደኦሮሞ ብሔርተኛነቴ አንድ ነገር ልንገራችሁ። ያ’ ለችው ኢትዮጵያ እኛን ገድላ መኖር ስለፈለገች የኛን ሕዝብ ከሞት ለማትረፍ ኢትዮጵያን ዝቅ አድርገን ኦሮሞን ከፍ የሚያደርግ ስብከት ተጠቅመናል። ኢትዮጵያን አፍርሰን ኦሮሞን ለመገንባትም ነበር የሰራነው።

ለማድረግ ስምምነት ላይ እንደደረሱ የሚገልጹ ቢሆንም የኦነግ ታጣቂዎቹ የዜጎችን የመንቀሳቀስና በሕይወት የመኖር መብት አደጋ ላይ ጥለዋል በማለት ከስሰዋል፡፡ ዛሬም በሁለቱ ወገኖች መካከል እየተካሄደ ያለው ግጭት አልበረደም፡፡

## የኦፒዲ ክስ እና የኦነግ ምላሽ

የኦሮሚያ ክልል መንግሥት በተለይ በምዕራብ ኦሮሚያ አካባቢ የተጀመሩት ትናንሽ ጦርነቶች ያስከተሉትን ውድመት እና የሕይወት ህልፈቶች በግልጽ በመተንተን መግለጫ ሰጥቷል፡፡ ከዚያ አስቀድሞ አንድ ኮማንድ ፖስት ተቋቁሞ በስፍራው የተበራከተውን ሰላም መደፍረስ እና ሰላም አዋኪ ተግባራት ለመቆጣጠር እርምጃ ለመውሰድ መዘጋጀቱንና በ25 ኪሎሜትር ርቀት ቀይ ቀጠና በማስመር የጦር መሳሪያ ይዞ በተንቀሰቀሰ ማንኛውም አካል ላይ እርምጃ ለመውሰድ መዘጋጀቱን መናገሩ በኦነግ ዘንድ አልተወደደም ነበር፡፡ የኦሮሚያ ክልል ከቤኒሻንጉል እና ከሱዳን ጋር በመተባበር በአካባቢው የመሸገ ነው ያለውን ኃይል  (ኦነጎችን ማለቱ ነው) ለመደምሰስ ተዘጋጅቻለሁ ባለ በሁለተኛው ቀን የክልሉ መንግሥት ሙሉ መግለጫ ሰጥቷል፡፡

የክልሉ መንግሥት በመግለጫው በተቀነባበረ ተንኮል የሕግ የበላይነት መጣሱን፣ ሕገወጥነት ተስፋፍቶ የሕዝቡ እንቅስቃሴ መደናቀፉንና በተለይ በምዕራብ ኦሮሚያ ትምህርት መቋረጡንና የንግድ እንቅስቃሴ መቋረጡን ተናግሯል፡፡ በነዚህ አካባቢዎች ልክ መንግሥት እንደሌለበት ሀገር የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች አገልግሎት እንዳይሰጡ መዘጋት፣ የጦር መሳሪያ መዝረፍ፣ ሕግ ባለበት አገር የቢሮ ኃላፊ ማባረር፣ መደብደብ፣ አልፎ አልፎም ጠልፎ መውሰድ፣ ባንክ መዝረፍ ተግባራት እንደሚፈጸሙም ዘርዝሯል፡፡

የክልሉ መንግሥት ኦነግን በነካካበት መግለጫ “...በእጃችን የገባውን ድል በመንከባከብ ከዳር እስከ ዳር በፖለቲካ ነጻ የወጣውን ሕዝብ በኢኮኖሚም ነጻ ለማውጣት እየተሠራ ባለበት ወቅት በሰላማዊ መንገድ ትግል ለማድረግ የተገባው ቃል ፈርሶ ፣ የኢዲፒ ትእግስት እንደ ፍራቻ ታይቶ ከሥልጣን የተባረሩ አካላት በገዙት ተላላኪ ኦሮሚያን እና ኦሮሞን የጦርነት አውድማ ለማድረግ እየተሠራ ነው” ብሎ ነበር፡፡ “ዛሬም ቢሆን እርስ በእርስ መዋጋት እና መታኮስ አንዱ አንዱን ከሰበረ እንጂ ወደ ቀጣይ ምእራፍ አያሻግረንም” ያለው ክልሉ እርስ በርሳችን ተደጋግፈን ለኦሮሞ ሕዝብ እንታገል የሚመስል ዓይነት መግለጫ ነበር የሰጠው፡፡

ኦዲፒ የተካሄዱትን የጠመንጃ ተኩስ ልውውጦች በመንተራስ እነዚህን ውጊያዎች ከኦነግ ጋር ነው ላለማለት ከታጠቀ ኃይል ጋር ነው ብሎ ሊሸፋፍነው ቢሞክርም በጊዜው ግን መገለጡ አልቀረም፡፡ ለምሳሌም በቅርቡ የኦነግ ሰራዊት አባላት መታኮስ ሲጀምሩ የኦፒዲ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ የሆኑት ዶክተር ዓለሙ ኦነግን በግልጽ ወቅሰዋል፡፡ “… ኦነግ፣ በአንድ በኩል በሰላም ለመታገል አሥመራ ያለውን 1ሺ300 ወታደሩን በሰላም ትጥቅ አስፈትቶ አስገብቶ እያለ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የታጠቀ ኃይል በምዕራብ ኦሮሚያ በኩል ማንቀሳቀሱ ለሰላም ያለውን ቁርጠኝነት ጥርጣሬ ውስጥ ያስገባዋል፡፡ በሰላምና ዴሞክራሲያዊ መንገድ የአገሪቱን ሕግና ሕገ መንግሥት አክብረን እንታገላለን ማለት እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በሰላም እንንቀሳቀሳለን ብሎ በትጥቅ መንቀሳቀስ ሕገ ወጥ ነው፡፡ ምክንያቱም በሰላም መንቀሳቀስ ማለት ከትጥቅ ውጪ ያለ እንቅስቃሴ ነው፡፡ ” ብለው ነበር፡፡

የኦሮሞ ነጻነት ግንባር (ኦነግ) በውጭ የሚንቀሳቀሱት ወታደሮቹ ቁጥር በካምፕ ከሚገኙት እንደሚልቁ በራሱ አንደበት መስክሯል፡፡ አስካሁን ትጥቅ የፈቱት 1500 ብቻ ሲሆኑ ቀሪ 3000 አባላቱ አሁንም በተለያዩ ሰፍራዎች ትጥቃቸውን ሳይፈቱ እየተንቀሳቀሱ ነው፡፡

የግንባሩ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል አቶ ኢብሳ ነገዎ በአንድ ወቅት ለሪፖርተር ያመኑት ነገር ድርጅታቸው አሁንም ትጥቅ ያልፈቱ ወታደሮች እንዳሉት ነው፡፡ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የገጠር ፖለቲካ አደረጃጀት ኃላፊ አቶ አዲሱ አረጋ፣ ኦነግ አሁንም አስታጥቆ እያንቀሳቀሰ ያለውን ጦሩን በአስቸኳይ ትጥቅ እንዲያስፈታ መጠየቃቸውን ተከትሎ ግንባሩ ወታደሮቹን ትጥቅ አስፈትቶ፣ በአስቸኳይ መንግሥት ወዳዘጋጀለት ካምፕ እንዲያስገባ አሳስበው ነበር፡፡ የኦነግ አመራር አባል አቶ ቶሌራ ▶

አደባ፣ አሁንም በተለያዩ የኦሮሚያ ክፍሎች የታጠቁ የኦነግ ወታደሮች እንዳሉ አምነዋል። በአፋጣኝ ትጥቅ ለማስፈታት ከመንግሥት ጋር እንሰራለን ብለዋል። እንዲያም ሆኖ ተግባራዊ ባለማድረጋቸው የታጠቀው ክንፋቸው ዛሬ ከመንግሥት ጋር ግልጽ ጦርነት ውስጥ እንዲገባ ምክንያት ሆኗል።

"እኛ ከተጋጨን በመሀል ሕዝቡ ይጎዳል በሚል ታግሰን ነበር ከዚህ በላይ ግን ጥፋቱ ከቀጠለ የሕዝብ እልቂት እና የሀገር መበተንን ያስከትላል" በማለት መግለጫ የሰጠው የኦዲፒ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የጸጥታ ኃይሉ እርምጃ እንዲወስድ መታዘዙንም ተናግሯል። " ኦዲፒ የጥፋት ኃይሎች በተቀናጀ መንገድ የሚሸርቡትን ሴራ አክሽፎ የሕዝቡን ሰላም ለማረጋገጥ ማንኛውንም ዓይነት እርምጃ ለመውሰድ ወስኗል " ብሏል በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ መግለጫው ላይ።

አቶ ዳውድ ግን በኦሮሞ ዴሞክራቲክ ፓርቲ የተሰጠውን መግለጫም ፓርቲያቸው እንደማይቀበለው ነው የተናገሩት። ወታደሩም ራሱን እንዲከላከል መታዘዙን ገልጸዋል።

## የኦነግ መንገድ ወዴት?

ኦነግ በሰላማዊ መንገድ ለመታገል ቢገባም አሁን ድረስ ያልጠራ ዓላማ አለው። ይህም ኦሮሚያን መገንጠል የሚለው ዓላማው ነው። ይህ አላማ አሁንም ከድርጅቱ ጋር ካለ ከማንም ጋር ተባብሮ እንዲሠራ አያደርገውም። በቅርቡ የቀድሞ የኦነግ ቃል አቀባይና አሁን የኦሮሞ ዴሞክራቲክ ፓርቲ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ሌንጮ ባቲ በአዲስ አበባ አስተዳደር ተካሂዶ በነበረው የፓናል ውይይት ላይ ተገኝተው የቀድሞ ድርጅታቸው ኦነግ ብዙዎቻችን በምናውቀው የመገንጠል እውነት ውስጥ ሽሽጎ ያኖረውንና ብዙም የማናውቀውን

> ኦነግ በዳውድ ኢብሳ ኦሮሚያ እና በለማ ኢትዮጵያ መካከል ቅርቃር ውስጥ የገባ መስሏል። በዚህ ሂደት ከቀጠለም ኦሮሚያንም ኢትዮጵያንም እንዳያጣ መስጋት አለበት ይላሉ ተንታኞች። በወታደራዊ ኃይል ተሸንፎ ከወጣ ኤርትራ አታስጠጋውም

ኢትዮጵያን የማፍረስ ዕቅድ ተናግረው ነበር።

"...እንደኦሮሞ ብሔርተኛነቴ አንድ ነገር ልንገራችሁ። ያ'ለችው ኢትዮጵያ እኛን ገድላ መኖር ስለፈለገች የኛን ሕዝብ ከሞት ለማትረፍ ኢትዮጵያን ዝቅ አድርገን ኦሮሞን ከፍ የሚያደርግ ስብከት ተጠቅመናል። ኢትዮጵያን አፍርሰን ኦሮሞን ለመገንባትም ነበር የሰራነው። "

የአሁኑ የውጭ ጉዳይ ኃላፊ ሸጉጥ ገለታ (ዶክተር) ግን ይህንን የኦነግን የመገንጠል ፕሮግራም ይክዳሉ። ዶክተር ሸጉጥ ቢቢሲ አማርኛ ላቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ "የድርጅቱን ጥያቄ የመገንጠል፣የዘረኝነት፣የአክራሪነት ጥያቄ ነው እየተባለ የሚወረወሩበት ውንጀላዎች አሉ። ኦነግ በታሪኩ ውስጥ በኢትዮጵያ ውስጥ ከነበሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች እራሱን ገለልተኛ አድርጎ ለሀገር መገንጠል ነው የምሠራው ብሎ በግልፅ የተናገረበት ጊዜ የለም "

ኦነግ የመገንጠል ዓላማውን ትቷል ወይስ ቀጥሎበታል ተብለው በቢቢሲ አማርኛ ተጠይቀው የሰጡት ምላሽ አገም ጠቀም የበዛበት ነበር።

ዶክተር ሸጉጥ "ጥያቄው በተሳሳተ መንገድ በድርጅቱ ላይ የተለጠፈ ነው" በማለት መልሳቸውን ከጀመሩ በኋላ ሲሉ ያስረግጣሉ።

"ከኢትዮጵያ ምሥረታ ጀምሮ የኦሮሞ ሕዝብ የተያዘው በኃይል ነው።" በማለት የሚሞግቱት ኃላፊው ቀጥለው የመጡ አገዛዞች የሕዝቦችን ፍላጎት እና ስሜት ለማክበር አለመፍቀዳቸው የችግሮች መነሻ ሆኖ ኖሯል ይላሉ። ድርጅታቸው ለዚህ መፍትሄ የሚሆነውን፣ ሕዝቦች በመብታቸው ላይ ለመወሰን ያላቸውን ልአላዊነት እንዲከበር መታገል፣ባሻቸው አስተዳደራዊ ብሂል እና ቋንቋ ካለ ከልካይ እንዲጠቀሙ መሚገትን በመሰሉ የመብት ጥያቄዎች ላይ መሥራትን ወደፊትም እንደሚገፋበት ያሰምሩበታል። የለም እንዳይሉም ጨንቋቸው፣ አለ እንዳይሉም ከዚህ ቀደም ብሎ ደግሞ የኦነግ የአሁኑ ሊቀመንበር አቶ ዳውድ ኢብሳ እንዳሉትም ኦነግ ሕዝቦችን ዕድል በራስ የመወሰን አንቀጽ 39 መብት መከበር ላይ የያዘውን አቋም አሁንም አልቀየረም ፣ የኦሮሚያ ሕዝብ ሲገዛ ነው የኖረው። አሁን የራሱን እድል ይወስናል ብለዋል።

ከታሪካዊ ዳራው አከራካሪ የሆነው አንቀጽ 39 በሕገመንግሥቱ ውስጥ እንዲካተት ያደረጉት ሕወሓት ሻዕቢያ እና ኦነግ መሆናቸውን ከድርጅቱ መሪ አፍ መስማት ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያልተወከለበት ሕገመንግሥት ሀገር እያስተዳደረ ነው የሚለውን ድምጽ ቅቡልነት ያጠናክረዋል። አቶ ዳውድ ኢብሳ በአንድ ወቅት "የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት ቻርተር የተዘጋጀው በኦነግ ሐሳብ ነው። ሕገመንግሥቱ ደግሞ በኦነግ ፣ ሕወሓት እና ህግሃኤ (ሻዕቢያ) የተረቀቀ ነበር" ነው ያሉት።

የኦነግን ተቃውሞ የሚቃወሙት የቀድሞ ቃል አቀባዩ አቶ ሌንጮ ባቲ ቆጣ ባለ ድምጽ ኦነግን ወደቀልብህ ተመለስ ዓይነት ነገር ተናግረውታል።

"....አሁን ኦሮሞ ይህንን መንግሥት የሚቃወምበት ምን መነሻ አለው ?...እስኪ አንድ ምክንያት ንገሩኝ ይህንን መንግሥት የምንቃወምበትን? ዓላማ ነው ወይስ ድርጅት ነው የሚቀድመው? ዓላማ የሚቀድም ከሆነ የኔ ዓላማ ትክክለኛ መንገድ ላይ ወጥቷል። እሱ ከመንገዱ ሲወጣ ብቻ ነው የምቃወመው።"

"ከኢትዮጵያ ምሥረታ ጀምሮ የኦሮሞ ሕዝብ የተያዘው በኃይል ነው።" ይላሉ ኦነጎች። ነገር ግን ኦሮሚያን መገንጠል ይፈልጋሉ የሚላቸውን ኃይሎች አይስማሙም። "የድርጅቱን ጥያቄ የመገንጠል፣የዘረኝነት፣የአክራሪነት ጥያቄ ነው [እየተባለ]የሚወረወሩበት [ውንጀላዎች] አሉ። ኦነግ በታሪኩ ውስጥ በኢትዮጵያ ውስጥ ከነበሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች እራሱን ገለልተኛ አድርጎ ለሀገር መገንጠል ነው የምሠራው ብሎ በግልፅ የተናገረበት ጊዜ የለም።" ነው የሚሉት ኃላፊዎቹ።

## በዳውድ ኦሮሚያ እና በለማ ኢትዮጵያ መካከል

"የኦሮሞን ሕዝብ ጥያቄ በጠመንጃ ኣፈሙዝ ማፈን ትላንት ኣልተቻለም፡ ዛሬም ኣይቻልም" በሚል ርዕስ ሓምሌ 05 ቀን 2018ዓም መግለጫ የሰጠው ኦነግ የእነአቶ ለማንና ዐቢይን መንግሥት የወያኔ ተላላኪ ሲል ይከስሳል። በዚያን ጊዜ ወደ ሀገር ውስጥ ባይገባም ዛሬ ድረስ ግን በዚህ ገለጻው የጸና ይመስላል። መግለጫው እንዲህ ሲል እነአቶ ለማን ይወቅሳቸዋል።

"...የለማ መገርሳ ኣስተዳደርና ኦፒዲኦ በኣንድ በኩል ስለለውጥና ተሃድሶ እያወራና ሕወሓትን የሚኮንኑ መስለው ወደ ኦሮሞ ሕዝብ እየቀረቡ በሌላ በኩል ደግሞ በኦሮሞ ሕዝብ ላይ በግልጽ የዘር-ማጥፋት ዘመቻ ሲያካሄዱ ለነበሩት እንደነጄኔራል ገብሬ ዲላ ሙሉ ሥልጣን ሰጥተው በኦሮሞ ሕዝብ ላይ እያሰማሩ ነው። ዛሬ በተሃድሶና በለውጥ ስም የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥትንም ሆነ የፌዴራሉን መንግሥት የሚመሩት ግለሰቦች ወደ ሥልጣን እንዲመጡ የረዳቸው የኦሮሞ ነጻነት ግንባርና ወታደራዊ ኃይሉ(የኦሮሞ ነጻነት ስራዊት)፣ ቄሮ ቢሊሱማ ኦሮሞና የኦሮሞ ልጆች ባጠቃላይ ከምስራቅ-ምዕራብ፣ ሰሜን-ደቡብ በጋራ ለነጻነታቸው ሲሉ የከፈሉት መስዋዕትነት መሆኑ ማንም ሊክደው የማይችል እውነታ ሆኖ ሳለ፡ እነዚህ ሰዎች የኦሮሞ ነጻነት ትግልና ኦነግን ብቻም ሳይሆን ለኦሮሞ ሕዝብ ህልውና ከፍተኛ ጠላታዊ ስራ መስራታቸውን መቀጠላቸው በጣም ኣሳዛኝና ኣሳፋሪ ተግባር ነው።"

ይህ አመለካከት ዛሬም ድረስ በኦነግ አባላት ውስጥ ሰርጾ አለመተማመን ነግሷል። በዚህ መሀል ግጭት እየተከሰተ የዶ/ር ዐቢይን አስተዳደር ለመጣል ለሚፈልጉ ኃይሎች በር እየከፈተ ነው። በቅርቡ የኦነግ ሸኔ ኃይሎች ለመንግሥት ወታደሮች እጅ ቢሰጡም ያላመኑትና ጫካ ያሉት ግን አሁነም የጸጥታ እና አለመረጋጋት ሥጋት ከሆኑ የዚህች ሀገር ሰላም ከአዙሪት እንዳልወጣ ማሳያ ይሆናል የሚሉ ብዙዎች ናችው።

ኦነግ በዳውድ ኢብሳ ኦሮሚያ እና በለማ ኢትዮጵያ መካከል ቅርቃር ውስጥ የገባ መስሏል። በዚህ ሂደት ከቀጠለም ኦሮሚያንም ኢትዮጵያንም እንዳያጣ መስጋት አለበት ይላሉ ተንታኞች። በወታደራዊ ኃይል ተሸንፎ ከወጣ ኤርትራ አታስጠጋውም። ከዚህ በኋላ ማን ጋ መሽጎ ለየትኛዋ ሃገር እንደሚታገል ራሱ ያውቃል ይላሉ ተቺዎች ። የሁሉም ልብ ግን በመነጋገር ሰላም ማምጣትን ዋና መፍትሄ አደርጎ በተስፋ ይጠብቃል። ለጊዜው ኦነግ ግን አጣብቂኝ ውስጥ የገባ ይመስላል።

# የኦነግ ታሪክን የመድገም አባዜ

በዘውግ ማንነት ዙሪያ ከተሰባሰቡ የፓለቲካ ኃይሎች መካከል ኦነግን በዕድሜ የሚተካከለው ደርጅት የለም፡፡በዚህ ረጅም የትግል ዘመን ውስጥ ድርጅቱ ያስመዘገበው ገድል እዚህ ግባ የሚባል እንዳልሆነ ከማንም የተሰወረ ሐቅ አይደለም፡፡ደርጅቱ እንደ ዋንኛ የመታጊያ መርህ አንግቦ የተነሳው ታላቋን ኦሮሚያ የመመሥረት ተምኔታዊ ህልም ሁሉነገሩን ነጥቆታል፡፡ኦነግን ያነዱት እንደ እነሌንጮ ለታ፣ሌንጮ ባቲ እና ዲማ ነገዎ ያሉ አንጋፋ ፓለቲከኞች ከዘመኑ ነባራዊ ሁኔታ ጋር ሊሄድ የሚችል መርህን እንደ አዲስ በመከለስ ድርጅቱን በይፋ ከተለዩት ሰንበትበት ብለዋል፡፡በዚህም የተነሳ ኦነግ አራት ቦታ ተሰነጣጥቆ በተዳከመ አቅም በስም ብቻ የቀረ ድርጅት ለመሆን በቅቷል፡፡

የመገንጠል አጀንዳ ሕዳጣን ማኅበረሰብ የሚያቀነቅኑት ፓለቲካዊ ስሌት እንጂ እንደ ኦሮሞ ላለ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ብዙ መስዋዕትነት በመክፈል፣ እናት ሀገሩ ነጻነቷን ጠብቃ በኩራት በሁለት እግሯ እንድትቆም ከፍተኛ ተጋድሎ ላደረገ ታላቅ ሕዝብ የሚመጥን አይደለም፡፡የኦነግ እና የሕወሓት የጨቋኝ ተጨቋኝ ተረክ ከአንድ ወንዝ የሚቀዳ ነው፡፡ሁለቱም ድርጅቶች በጨቋኝነት በፈረጁት ማኅበረሰብ ላይ ሁሉንም የታሪክ ዕዳ በማሸከም ሕዝባቸውን በተገፊነት እና በተብሰልሳይነት ሥነልቦና ውስጥ ጨምረውት ኖረዋል፡፡ይህ ዓይነት የፈጠራ ተረክ ከኦነግ ይልቅ ለሕወሓት ግዜያዊ የፓለቲካ ትርፍ እንዳስገኘለት ለማወቅ ዞር ብለን ያለፉትን የሁለት ዐሥርተ ዓመታት ገበናችንን መመልከት ብቻ በቂ ይሆናል፡፡

ባለፉት 27 ዓመታት ያለምንም ተቀናቃኝ ሕወሓት በፓለቲካው ምህዳር ላይ እንዳሻው ለመፈንጨቱ አንዱ ምክንያት ብዙኃኑን የሚወክለው ኦነግ ከሚወክለው ሕዝብ ታሪክ፣ሥነልቦና እና ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማይገጥም ፓለቲካዊ አጀንዳ ራሱን ቅርቃር ውስጥ በመክተቱ ነበር፡፡

የኦሮሞ ሕዝብ መብት እና ጥቅም ሊከበር የሚችለው በኢትዮጵያ ማዕቀፍ ውስጥ ብቻ እንደሚሆን አስቀድሞ አቋም ይዞ ቢሆን ኖሮ ሕዳጣኑ ሕወሓት ይህን ያህል ዘመን የግፍ አገዛዙን በሀገራችን ሕዝብ ጫንቃ ላይ በማንአለብኝነት ባልጫነ ነበር፡፡ለዚህ ምሥክር የሚሆነን የቲም ለማ እና የቲም ገዱ የቅርብ ጊዜ የትብብር ገድል ነው፡፡ሰፊው የኦሮሞ ሕዝብ ጥንት አያቶቹ በደም እና በአጥንታቸው ያጸኗትን ሀገር ለመጠበቅ ከሌሎች ወንድሞቹ ጋር በአንድነት ሲሰለፍ፣ የአምባገነኖችን ዕድሜ እንዴት እንደሚያሳጥር የቅርቡ የለውጥ መንግሥት ስኬት ዋቢ ምስክር ይሆናል፡፡

ኦነግ ግን ከዚህ በተቃራኒ ሐዲድ ላይ ነው ሲነጉድ የኖረው፡፡ የራሱን ደሴት ቀልሶ፣ የኦሮሞ ዘውግ ከሌሎች የሀገራችን የዘውግ ማኅበረሰቦች ጋር የሚያስተሳስረውን የአንድነት ገመድ በፈጠራ ታሪክ በመበጣጠስ እና ጽንፍ የረገጠ ዘውገኝነትን በማቀንቀን የራሱን ውድቀት አፋጥኗል፡፡ በደርግ ሽንፈት ማግሥት እንደ ሕወሓት ባለ አናሳ ቡድን ከጥቅም ውጪ የሆነበት ምክነያት በያዘው የተብሰልሳይነት፣የተበዳይነት እና የከበባ ሥነልቦናዊ ማእቀፍ(siege mentality) ፓለቲካዊ መርህ ነው፡፡

በሀገራችን የሚነፍሰውን የፓለቲካ ለውጥ ተከትሎ በሰላም ለመታገል ወደ ሀገር ቤት ከገቡት የኦነግ አንጃዎች መካከል፣ የዳውድ ኢብሳው ኦነግ ሸኔ በዋንኛነት ይጠቀሳል፡፡ይህ የኦነግ ክንፍ በኤርትራ በረሃ ሲታገሉ የነበሩ 1300 ታጋዮችን ከአዲሱ የለውጥ አስተዳደር ጋር በደረሰው ስምምነት መሠረት፣ ትጥቅ ፈቶ ወደ ሀገር ቤት በመግባት የተሀድሶ ሥልጠና መውሰድ ከጀመረ ወራት እንዳለፉ ይታወቃል፡፡የሰሞኑ እሰጣ ገባ እንግዲህ የተከሰተው ይህ ሁሉ ነበራዊ ሁኔታ በሰከነ መንገድ እየሄደ ባለበት ወቅት ነው ፡፡

የለውጡን አስተዳደር እየተቀናቀነ ያለው ፣በወለጋ በኩል የገባ የታጠቀ ኃይል ማን እንደሚያዘው እና ዓላማውም ምን እንደሆነ የታወቀ ነገር የለም፡፡ሀገራችን በቆመችበት መስቀለኛ መንገድ ላይ ይህ የኦነግ ክንፍ ከሕወሓት ባልተናነስ ደረጃ የጎን ውጋት መሆን ጀምሯል፡፡ ሀገሪቱ በየአቅጣጫ ለምትናጥበት ነውጥ የራሱን እሳት እያቀበለ ይገኛል፡፡

የፀረ ለውጡ የሕወሓት ቡድን እና ሀገሩን እያሸበረ ያለው የኦነግ አንጃ በማንኛውም ሰዓት ግምባር ሊፈጠሩ መፍጠራቸው የማይቀር ነው፡፡ ይህ ያልተቀደሰ ጋብቻ ውሎ አድሮ ለለውጡ አስተዳደር የራስምታት መሆኑ አይቀርም፡፡ስለዚህ ሳይቃጠል በቅጠል በሚለው የአበው ብሂል መሠረት፣ ብስለት የታከለበት ፓለቲካዊ ውሳኔ ከዶ/ር ዐቢይ አስተዳደር በእጅጉ የሚጠበቅበት ጊዜ ላይ ደርሰናል፡፡

የኦነግ የሰሞኑ የነውጥ መንገድ የሚነግረን ነገር ቢኖር ድርጅቱ ከሁለት ዐሥርተ ዓመታት በፊት በሕወሓት ያጋጠመውን ታሪካዊ ውርደት ለመድገም የውድቀት ፈለግን እያነፈነፈ መሆኑን ነው፡፡ ታሪክ ራሱን እንዳይደግም ያሰጋል፡፡በእንዲህ ዓይነት የአመጻ አካሄድ አይደለም የሰፊውን የኦሮሞ ሕዝብ መብት እና ነጻነት ይቅር እና የድርጅቱን ኅልውና ማስጠበቅ አይችልም፡፡በጎጥ እና በሃይማኖት ተከፋፍሎ አጽሙ ብቻ የቀረው የዳውድ ኢብሳው ኦነግ በሰሞኑ የነውጥ እንቅስቃሴ ዳግም ላይመለስ ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ ከፓለቲካው ዓለም የሚሰናበትበትን ወጥመድ እራሱ እያበጃጀ ነው፡፡


**ግዮን መጽሔት**

**ኢትዮ ሐበሻ ኅትመትና**

**ማስታወቂያ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር**

**በየሳምንቱ ለኅትመት የምትበቃ መጽሔት**

**ማኔጂንግ ዳይሬክተር**

ፍቃዱ ማ/ወርቅ

**ዋና አዘጋጅ**

ሮቤል ምትኩ

አድራሻ፡- የካ ክ/ከተማ ወረዳ 2 የቤት ቁጥር 475

**ማኔጂንግ ኤዲተር**

ደረጀ ይመር

**ተባባሪ ዘጋቢያችን**

ቶማስ አያሌው(**ከአሜሪካ**)

**ከፍተኛ አዘጋጅ**

ብሩክ መኮንን

**አዘጋጅ**

ተስፋዬ ሽብሩ

ሔማስ ታፈረ

**አምደኞች**

ፍቅሩ ኪዳኔ (**ከሲውዘርላንድ**)

ዶ/ር ዘሪሁን ሙላቱ

መስፍን ጌታቸው

አስማማው ኃ/ጊዮርጊስ(**ከአሜሪካ**)

ተስፉ (ኢትዮጵያ) አልታሰብ

ታምራት መርጊያ

**ጸሐፊ**

ሠላም ግርማ

**ክርኤቲቭ ዲዛይን**

ሀብታሙ መኮንን

**የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ**

አራዳ ክ/ከ ወረዳ 09 የቤት ቁጥር 552/1

አምባቸው ህንፃ 5ተኛ ፎቅ ቢሮ ቁ. 501

ፖስታ ቁ. 676 ኮድ 1029

ስልክ ፡ +251 911 227661

+251 912 165606

+251 118 12 2333

ኢ-ሜይል፡

enqu2013@ gmail.com

Ghion2011mag@gmail.com

Facebook

Gihon-meg Fekadu

www. facebook.com/enqu2013

**አታሚ**

አስክ ማተሚያ ቤት

ክ/ከተማ ቂርቆስ ወረዳ 15 የቤት ቁ. 23/10

ስልክ ቁ. 0913 18 12 12



በዚህ መጽሔት ላይ የሚወጡ ጽሑፎች በሙሉ ማተሚያ ቤቱን አይመለከትም

# አልጨበጥ ያለው ኦነግ ሾኔ



ተስፋዬ ሽብሩ



የኦነግ ሰራዊት በትግራይ የተደረገለት አቀባበል

## የማወላወል ፖለቲካ ኦነግን ያዋጣው ይሆን?

ያለፉት ስድስት ወራት የኢትዮጵያ የፖለቲካ ድባብ አሳዛኝ አንዳንዴም በአስገራሚ ሁኔታዎችና ውጥንቅጦች የተሞላ ነው:: ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድና የለውጡ ኃይሎች ማዕበል እንዳንገላታት መርከብ ወዲያና ወዲህ ስትናጥ የነበረችውን አገር፣ አመራርነት ተረክበው በርካታ መሠረታዊ የሆኑ ለውጦችን በማድረግ መርከቧን ለማረጋጋት ብዙ ደክመዋል::

በተለይ በፖለቲካ አመለካታቸው የተነሳ ከአገር ተሰደው የትጥቅ ትግልን አማራጭ ያደረጉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ወደ አገር ገብተው በሰላማዊ መንገድ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ዕድል አግኝተዋል::ይህንን ዕድል ካገኙት የፖለቲካ ድርጅቶች መካከል ኦነግ ዋነኛው ነው:: ከአራት ዓመታት በላይ የኦሮሞን ሕዝብ የብሔርና የፖለቲካ መብት ጥያቄ በመያዝ ሲታገል የኖረው ኦነግ በግምባሩ አመራሮች መካከል በተፈጠረ አለመግባባት ወደ አራት ቦታ መከፈሉ ይታወቃል:: ግንባሩ እርስ በርሱ መስማማት ሳይችል በተቃርኖ ተሞልቶ ሰፊውን የኦሮሞ ሕዝብ ለመምራትና ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ መብቶቹ እንዲከበሩ ለማድረግ መነሳቱ በራሱ አነጋጋሪ ነው::

በተለይ የአቶ ዳውድ ኢብሳ ኦነግ ከመንግሥት ጋር ስምምነት አድርጎ ትጥቁን ፈትቶ እንደሌሎቹ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ሰላማዊ የሆነ የሀሳብ ሙግት በማድረግ በፖለቲካው ምህዳር ውስጥ የሚችለውን ያህል አስተዋፅኦ እንዲያደርግ በር ተከፍቶለት ቢቆይም፤ የለመደው የትጥቅ ትግል ስልት ባህሪው ያገረሸበት መስሏል:: ለዚህም ማሳያ የሚሆነው ባለፉት ጥቂት ወራቶች ከመንግሥት ጋር የገጠመው እሰጣ ገባ እና በክልሉ እየፈፀመ ያለው ግጭት የመፍጠር አባዜ ነው::

ሰሞኑን የኦሮሚያ ክልል ፖሊስ ኮሚሽነር ዓለማየሁ እጅጉ የክልሉ ፖሊስ በምዕራብ ወለጋ ያሉትን የኦነግ ታጣቂዎችን አይቅጡ ቅጣት ለመቅጣት ስምሪት ማድረጉን ገልፀው ሕግን በተላለፉ አካላት ላይ አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ ጥብቅ ትዕዛዝ መተላለፉን ኮሚሽነሩ አስታውቀዋል::

ባለፉት አራት ወራት በቄለም ወለጋ የተገደሉትን 2 የዞን ፖሊስ አመራሮችን ጨምሮ 12 ፖሊሶች፣ 29 ነዋሪዎች ተገድለዋል፤77 ፖሊሶችና 40 ሚሊሻዎች መቁስላቸውን ተናግረዋል ፤ በምሥራቅና በምዕራብ ወለጋ የመንግሥት መዋቅሮች መፍረሳቸውን የጠቀሱት ኮሚሽነሩ፣ ከፖሊስ ጣቢያዎች ከ2ሺህ በላይ ክላሽንኮቭ ጠመንጃ መዘረፉን እና በምዕራብ ወለጋ ለደረሰው ጥፋት ሁሉ ተጠያቂው ኦነግ መሆኑን አስረድተዋል::

ከዚህ በተጨማሪም የኦሮሚያ ክልል የመንግሥትና የሕዝብ ሃብትን በመመዝበር የተጠረጠሩ 56 ግለሰቦችን ታህሳስ 15 ቀን 2011 ዓ.ም በቁጥጥር ሥር አውሏል:: ተጠርጣሪዎች በቁጥጥር ሥር የዋሉት የክልሉ ፀረ ሙስና ኮሚሽን ሲያደርግ በቆየው ምርመራ መሰረት ሲሆን ተጨማሪ የሙስና ተጠርጣሪዎችን የማሰሩ ዘመቻ በተከታታይ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ታውቋል::

የኦሮሚያ ጣጣ በዚህ ብቻ የሚያበቃ አልሆነም:: የክልሉ ኮሚኒኬሽን ቢሮ እንዳስታወቀው "አባ ቶርቤ" በሚል መጠሪያ ራሳቸውን የሚጠሩ ኃይሎችንም በቁጥጥር ስር መዋላቸው ገልጿል::፡ ብሔራዊ መረጃና ደህንነት ባደረገው ክትትል አዲስ አበባ በመሸጉት ተጠርጣሪዎች እጅ ጦር መሳሪያዎችና ቦንቦች ተገኝተዋል:: "አባ ቶርቤ" (ባለ ሳምንት) በክልሉ በህቡዕ ተደራጅቶ የመንግሥት ባለሥልጣናትን የፀጥታ አካላትን እና ንፁሀን ዜጎችን ሲገድል የቆየ ቡድን ነው:: ከተያዙት ታጣቂ ኃይሎች መካከል በነቀምት በደምቢ ዶሎ ነጆ እና ሰሜን ሸዋ ሰዎችን ሲገድሉና ሲያስገድሉ የነበሩ ቢሆኑ አዲስ አበባም ባለስልጣናትን የመግደል ዕቅድ እንደነበራቸውና ተጠርጣሪዎቹ በምዕራብ ኦሮሚያ ከሚንቀሳቀሱ ታጣቂ ኃይሎች ጋር ግንኙነት አላቸው ተብሏል:: ▶

### "ሰውየው አለ ወይ?"

ኦነግ ወደተለያየ አንጃነት ከተከፋፈለ በኋላ የቀድሞ 'አቀሙ' አለ ወይ ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው:: አሁን ኦነግ ስሙ ብቻ እንጂ በተለይ በመዋቅር በእዝ ደረጃ አለ ለማለት ይቸገራል:: በተለይም የአቦ ዳውድ ኢብሳ ኦነግ ወደ አገር ቤት ሲገባ የተደረገለት አቀባበል፤ ለግንባሩ የልብ ልብ ሳይሰጠው የቀረ አይመስልም:: ከአዲስ አበባና ከተለያዩ የኦሮሚያ ከተሞች የጎረፈ የግንባሩ ደጋፊዎች ያን መሰል አቀባበል ያደረጉለት በክልሉ ደም አፋሳሽ እልቂቶች እንዲፈፀሙ በመፈለግ አለመሆኑ ማንም የማይስተው ሀቅ ነው:: ኦነግና አመራሩ ግን ይሄን የኦሮሞ ሕዝብ የድጋፍ ድባብና ስሜት ለሕዝቡ በሚበጅ መንገድ የያዘውና ያስተናገደው አይመስልም:: ኦነግ ከገባበት የመደናገር ቅርቃር ካልወጣ ከሕዝብ የሚነጠልበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም::

### የሚፈልገውን የማያውቀው ኦነግ

የኦነግ ፍላጎት ምንድን ነው? ብሎ ለሚጠይቅ አካል መልሱ ግራ አጋቢ ነው:: ከመንግሥት ጋር ተስማማን በማለት ወደ አገር ከገቡ በኋላ መንግሥትንና ሕዝቡን የሚያሸብር ድርጊት በመፈፀም ግራ አጋቢ የሆነ ተግባር ላይ ተሰማርቷል:: የግንባሩ ሊቀ መንበር የሆኑት አቶ ዳውድ ኢብሳም ሠራዊታቸው ራሱን እንዲከላከል ትዕዛዝ መስጠታቸውን አሳውቀዋል:: ቆየት ብለው ደግሞ መንግሥት በክልሉ ስለተፈጠረው ችግር ሊያነጋግራቸው ከፈለገ ፈቃደኛ መሆናቸውን የሚያሳይ ዓይነት ንግግር አድርገዋል::የመከላከያ ሠራዊት የኦነግ ታጣቂዎች ባሉበት አካባቢ በተለይም በምዕራብ ወለጋ መስፈሩ ግጭት እንዲከሰት ምክንያት እንደሆነም አቶ ዳውድ በመግለጫቸው አንስተዋል:: ኦነግ በኦዴፓ በኩል ጫና እየደረሰበት ስለመሆኑ አንስተው፤በኦዴፓ የወጣው መግለጫም የውጊያ አዋጅ ይመስላል ብለዋል::

ጥያቄው ኦነግ ትጥቁን ፈቶ መግባቱን ካሳወቀ በኋላ የሚያዘው ሠራዊት ከየት አመጣ? በአገር ቤትስ ሠራዊት ከነበረው ወደ ሰላማዊ ፖለቲካ ሲገባ ሠራዊቱን ሙሉ ለሙሉ ወደ ካምፕ ለማስገባት ለምን አልፈለገም? የሚሉ ጥያቄዎች ይነሳሉ:: ግንባሩ ከማድበስበስ በዘለለ ለዚህ ግልፅና የማያሻማ መልስ ሲሰጥ አልተስተዋለም:: መንግሥትም ተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያና መግለጫ በማውጣት ኦነግ እየሄደበት ያለውን መንገድ እንዲያስተካክል ሲጠይቅ ቆይቷል::

ኦነግ የሚፈልገውን አውቆ ቢጠይቅና ከለውጡ ኃይሎች ጋር ቢሰራ ሠፊው የኦሮሞ ሕዝብና የኢትዮጵያ ሕዝብ ተጠቃሚዎች ሊሆኑ ይችሉ ነበር:: ግንባሩ ግን ከዚህ እውነታ ጋር በመላተም የፖለቲካ አዙሪት ውስጥ መግባቱ ለራሱም የሚበጅ አይመስልም::

### ኦነግና የማይጨበጥ አቋሙ

ኦነግ ከአራት ዐሥርት ዓመታት ለዘለለ የኦሮሞ ፖለቲካን በብሄር ጥያቄ ላይ በመመስረት ኦሮሚያ የምትሰኝ ሪፐብሊክ ለመመስረት የመገንጠል አማራጭን ይዞ ሲንቀሳቀስ የኖረ ድርጅት ነው::

"ቲም ለማ" እና የኢትዮጵያ ሕዝቦች ባመጡት የተቀናጀ የለውጥ ሂደት ተዋናይ ለመሆን ከመሸገበት አስመራ ከገባ በኋላ የጠራ የፖለቲካ አቋም ለመያዝ መቸገሩን የግንባሩ መሪዎች ከሚሰጡት የተምታታ መግለጫ መረዳት ይቻላል::አቶ ዳውድ ለውጡ በኦነግና በኦሮሞ ሕዝብ ትግል ብቻ እንደመጣ አድርገው መናገራቸው በራሱ ከቀደመው የኖሩበት የአስተሳሰብ ቅርቃር አለመውጣታቸውን ከማሳየት ውጪ ምን ሊሆን ይችላል::

ኦነግ በክልሉ ሕዝባዊ መሰረት የለውም ማለት ባይቻልም አሁን የለውጥ ኃይሉን እየመራ ያለው ኦዴፓ በክልሉ የማይናቅ የመዋቅርና የፖለቲካ ልምድ እንዲሁም ተቀባይነት እንዳለው ይታወቃል:: ኦነግም ይህንን የኦዴፓ የኃይል ሚዛን የበላይነት ይስተዋል ተብሎ አይጠበቅም::ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይም ሆኑ የክልሉ ባለሥልጣናት የኃይል እርምጃ መውሰድ ከባድ እንዳልሆነና የተጀመረውን የለውጥ ጉዞ ከማደናቀፍ የዘለለ ትርጉም እንደማይኖረው በተደጋጋሚ ሲናገሩ ቆይተዋል::

ኦዴፓም ሆነ የፌደራሉ መንግሥት በተደጋጋሚ ኦነግን የያዙበት የመለማመጥ እና የማባባል የሚመስል መርህ (Appeasement policy) የት ድረስ ያስጉዘዋል የሚል ጥያቄ ይነሳበታል:: ሰሞኑን የፖሊስ ኮሚሽነሩ እና የኦዴፓ ማእከላዊ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ ሞገስ ኢዳኤ እንደገለጹት በክልሉ መንግሥት በኩል የተወሰደው መጠኑ የበዛ ትዕግስት ዋጋ እንዳስከፈላቸው ጠቁመዋል::

በርግጥ የክልሉ መንግሥትም ሆነ የፌደራሉ መንግሥት ኦነግ ላይ ሕጋዊ እርማጃ የመውሰድ የአቅምም ፣የሕግም መንገድ እንዳለው ይታወቃል:: ነገር ግን የኦነግን የትርምስ ፍላጎት በማስታመም የለውጡን መንገድ የማስቀጠል እና በሂደት ግንባሩን ከሕዝብ የመነጠል ሥራ ላይ የተጠመደ መስሏል:: መንግሥትና የክልሉ አስተዳደር የያዙት መንገድ የሚያዋጣ ይሁን አይሁን በቅርቡ መልስ የሚያገኝ ጉዳይ ሆኖ፣ ኦነግ የያዘውን የማይጨበጥ ፖለቲካ መርምሮ መንገዱን ያስተካክል ይሆን ወይ የሚለው የሚታይ ጉዳይ ነው::

ኦዴፓ የኦሮሞን ሕዝብ ጥያቄ ከብሄር ጭቆናና ወደ መደብ ትግል ትርክት በመቀየር ከዜግነት የፖለቲካ አራማጆች ጋር "ፍቅር" ውስጥ የወደቀ መምሰሉ ኦነግን ድንጋጤ የፈጠረበት አስመስሎታል:: ከአስመራ ወደ ሀገር ቤት ሲገባም ከቀድሞ ደመኛው ከአሁን የጡት አባቱ ሕወሓት ጋር የሞቀ የምሳ ግብዣ እና ሽር ጉድ ማሳየቱ ሁለቱን የጎሳ ፖለቲካ አቀንቃኞች ጋብቻ ያሳየ ሆኖ አልፏል::

ኦነግ ዛሬም የመገንጠል አጀንዳውን ኪሱ ውስጥ ደብቆ ሲያሻው እየመዘዘ ሊጫወትበት ይቃጣዋል:: የኦሮሞ የመብት ጥያቄ እና የፍትሓዊ ሀብት ተጠቃሚነት ጉዳይ በሂደት እየተመለሰ ከመጣ መታገያ ካርታውን እንደሚያጣው የተረዳው ኦነግ ፣ ምርጫው ካልተደረገ ባንገቱ ገመድ በማለት፤ ከአገርና ከሕዝብ ጥቅም ይልቅ የራሱ የሥልጣን ጥም የሚያናውዘው ቡድን ሆኗል በማለት ብዙዎች ይከሱታል::

የቀድሞው የኦነግ መሪ አሁን የኦዴግ ሊቀ መንበርና አንጋፋው ፖለቲከኛ ሌንጮ ለታም ኦነግም ሆነ ሌሎቹ የኦሮሞ ድርጅቶች ለኦሮሞና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅም በማሰብ ራሳቸውን በክልሉ ሰፊ ልምድና የፖለቲካ መዋቅር ካለው ኦዴፓ ጋር በመተባበር በጋራ መስራት እንደሚገባቸው በመጠቆም የኦሮሞ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ለትብብር ጋብዘዋል:: ኦነግም ከዚህ የማይጨበጥ አቋሙ በመውጣትና ከቀድሞው ስህተቱ በመማር አገርንና ሕዝብን የሚጠቅም ተግባር ላይ ቢሳተፍ ይሻላል::

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በተለያዩ የኦሮሚያ ከተሞች ተገኝተው በወቅታዊ የአገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ እየተከሰቱ ባሉ ግጭቶች ላይ በአዲስ አበባ፤ በአምቦ፤በቡሌ ሆራ ከሕዝብ ጋር ውይይት ሲያደርጉ ሰንብተዋል::

### "ድሉን ማንም ከሕዝቡ ወደ ራሱ ሊጎትተው አይገባም"

ታህሳስ 6 ቀን 2011 ዓ.ም "የኦሮሞ ሕዝብ ትግል ከየት ወዴት ?" በሚል ርዕስ በተካሄደ ስብሰባ ላይ ከኦሮሚያ የተለያዩ ወረዳዎችና ዞኖች የተውጣጡ የሃይማኖት አባቶች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ወጣቶችና ምሁራን የተሳተፉበት ሲሆን ከተሳታፊዎች በየቦታው ጥቃት ያለመቆሙ የዜጎች መፈናቀልና የመንግሥት የሕግ የበላይነትን ያለማስከበር ጉዳይ በስፋት ተነስተው ውይይት ተደርጎባቸዋል::

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ለጥያቄዎቹ ማብራሪያና ምላሽ ሰጥተዋል:: የለውጡ ጉዞ የማይቀለበስበት ደረጃ ላይ የደረሰ ቢሆንም አሁንም የመላውን ሕዝብ ድጋፍ እንፈልጋለን ብለዋል::ለውጡን ማን አመጣው በሚለው ላይ ንትርክ ውስጥ መግባቱን ያነሱት ጠ/ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ፣ "ለውጡን ያመጣሁት እኔ ነኝ፤ አይ እሱ ነው ከሚለው ውዝግብ መውጣት አለብን፤ ድሉ የሕዝብ ነው፤ ድሉን ማንም ከሕዝቡ ወደ ራሱ ሊጎትተው አይገባም፤ በዚህ ጉዳይ ተማምነን ስንጓዝ ብቻ ነው ከምንፈልገው ግብ መድረስ የምንችለው" በማለት ተናግረዋል::

### "ቀኑ ከመጨለሙ በፊት ወደ ትክክለኛው አሠራር መግባት አለበት"

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ መብቴን እወጣለሁ መብቴን እጠይቃለሁ " በሚል መሪ ሐሳብ በተከታታይ የሚካሄደውን አገር አቀፍ የማኅበረሰብ የታክስ ንቅናቄ ታህሳስ 12 ቀን 2011 ዓ.ም በአፍሪቃ ኅብረት አዳራሽ ከፍተው እንደነበር ይታወሳል::

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ባደረጉት ንግግር ግብር የሚከፍሉ ዜጎች በቢሮክራሲ በጉቦ ባልተገባ አሰራርና በእንግልት የሚቀጣው የመንግሥት ኃላፊም ሆነ ሠራተኛ፣ ግብር ከሚያጭበረብሩ የአገር ጠላቶች ለይተን ዐናያቸውም:: ገንዘብ ለአገሩ ሊከፍል የመጣን ሰው አክብሮና ጋብዞ ከመቀበል ይልቅ ያልሆነ ቢሮክራሲ የሚፈጥር ሰውም ሆነ አሠራርን ከእንግዲህ ፈፅሞ እንታገለው በማለት ከግብር ጋር ተያይዘው የሚነሱ ዘረፋዎችን ለማስወገድ መንግሥት ሌት ተቀን እንደሚሠራ አስረድተዋል::

በአሁኑ ወቅት የሚሰበሰበው ግብር ከአጠቃላይ ሀገራዊ ምርት ጋር ያለው እምርታ በመቶኛ 10 ነጥብ 7 ብቻ ነው ያሉት፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ከሰሃራ በታች ▶

# የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የሰሞኑ ውሎ

◀ ካሉ የአፍሪቃ ሀገራት ጋር አገሪቱ ስትወዳደር እጅግ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች ብለዋል:: በአገሪቱ የተፈጠሩት አለመረጋጋቶች በግብር አሰባሰቡ ሂደት ላይ የራሱን አሉታዊ ጎን መፍጠሩን የጠቀሱት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ግብር የመክፈል ግዴታችንን ካልተወጣን የምናስባትን አገር ልናያት የምንችለው በህልማችን ብቻ ነው፤ በድርጊት ያልተደገፈ ፍላጎት ስያሜው ህልም ሳይሆን የቀን ቅዠት ነው ብለዋል::

"ኢትዮጵያ የሁላችን እናት ናት ማንም ልጅና የእንጀራ ልጅ የለም:: አንዱ በሚከፍለው ግብር ሌላው የሚንደላቀቅበት ምክንያት አይኖርም" በማለት ግብር የሁሉም ዜጋ ኃላፊነት መሆኑን የጠቀሱት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ የተሳሳተ መስመር ውስጥ ገብተው ግብር የሚሰውሩና የሚያጭበረብሩ ሁሉ ቀኑ ከመጨለሙ በፊት ወደ ትክክለኛው አሠራር እንዲገቡ መክረዋል::

### " የኦሮሞ ሕዝብ ነጻነቱን ተጎናፅፏል"

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ታህሳስ 15 ቀን 2011 ዓ.ም በአምቦ መሰናዶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለተገኘው ሕዝብ ንግግር አድርገዋል::

"የአምቦ ከተማና አካባቢው እውነተኛ እኩልነትና ትክክለኛ ዴሞክራሲ እንዲጎለብት የትግል ማዕከል ሆኖ አገልግሏል" በማለት ንግግራቸውን የጀመሩት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ የከተማዋ አካባቢው ሕዝብ ጨቋኙን ሥርዓት ለመለወጥ በተደረገው ትግል ውስጥ የማይተካ ሚና መጫወቱን ጠቅሰዋል:: "አባቶቻችን የጀመሩትን ትግል ቄሮና ቀሬ በሁሉም አካባቢዎች መስዋዕትነት ከፍለው ዛሬ ለኦሮሞ ሕዝብ ነጻነትን አጎናፅፈዋል:: ሕዝባችን ሰላማዊና ተስፋ ያለው አየር እንዲተነፍስ ትልቅ ዕድል ሰጥተዋል" ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ "መስዋዕትነት ለከፈለው ሕዝባችን በሙሉ ትልቅ ክብር እንዳለን ለመግለፅ እወዳለሁ" ሲሉ ተናግረዋል::

"ከዚህ በኋላ ሕዝባችን ለነጻነት ዋጋ መክፈል የለበትም:: የኦሮሞ ሕዝብ ነጻነቱን ተጎናፅፏል::›› ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ከአሁን በኋላ ሰምተንና ተለውጠን ለእኛም ብቻ ሳይሆን ለጎረቤቶቻችን መትረፍ እንድንችል ለትምህርታችሁ ልዩ ትኩረት በመስጠት መማር አለባችሁ በማለት አስገንዝበዋል::

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ንግግራቸውን በመቀጠል "አሁን የሚያስፈልገው መስዋዕትነት ሌት ተቀን በማጥናትና ነገሮችን በመገንዘብ ሐሳብ ማካፈል፤ አዲስ ነገር ለመፍጠር ጥረት ማድረግ መሆን" እንዳለበት ገልፀዋል:: ይህንን ማድረግ ከተቻለ የዛሬው ድል ሊቀጥል እንደሚችል ካልሆነ ግን ባለንበት ሁኔታ እንኳን ለመቆየት ያስቸግራል በማለት አስረድተዋል::

በመጨረሻም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ይህንን ተረት በመናገር ንግግራቸውን አጠቃለዋል::"እንቁራሪት እና እባብ መንገድ እየተጉዋዙ ወንዝ ጋር ተገናኙ:: እባብ እንቁራሪትዋን እንዲህ አላት" ይሄን ትልቅ ውሃ መዋኘት ስለማልችል በወገብሽ አዝለሽኝ አሻግሪኝ" ይላታል:: እንቁራሪትዋም አሻፈረኝ ትለዋለች:: "ምነው እኔኮ መዋኘት ስለማልችል ነው" ሲላት እንቁራሪትዋም አይ "ካሻገርኩህ በኋላ በመርዝህ ወግተህ ብትገለኝስ ትለዋለች:: እባብ ኧረ በፍፁም አላደርገውም ብሎ ቃል ገባ እሱዋም በወገብዋ አዝላ አሻገረችው:: ከተሻገረ በሁዋላ ግን እባብ እንቁራሪትዋን ነደፋት:: "እንዴ ምነው አልነድፍሽም ብለህ ምለህ አልተገዘትክም እንዴ?" ብትለው…… "አይ አመሌ ነው መተው አልችልም" አላት አሉ::"



በሌለው ምክንያት ወንድም ወንድሙን በመግፋት ለውጡን ወደኋላ ለመጎተት እየተሞከረ መሆኑን የጠቀሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ አብዛኛው የክፉ ሐሳብ ፍላጎት ባይሳካም ተማሪዎች ያጋጣማችሁንና ያደረባችሁን ጉዳት ተረድቻለሁ› በማለት ተማሪዎቹን አጽናንተዋቸዋል::

"ባለፉት ጥቂት ሳምንታት ደጅ አድራችኋል፤ ተጎሳቁላችኋል፣ ተርባችኋል፣ ቁር መቷችኋል" ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ተማሪዎቹ ለኢትዮጵያ አንድነት መስዋዕትነት እንደከፈሉ ቆጥረው ለአንድነትና ሰላም ቁርጠኛ አቋም እንዲወስዱ ጠይቀዋል:: የዩኒቨርስቲ ተማሪ የብሩህ አእምሮ ባለቤት መሆኑን ገልጸው፣ ተማሪዎቹም ያጋጠማቸውን ፈተና ለማለፍ ብሩህ አእምሯቸውን መጠቀም እንዳለባቸው ነግረዋቸዋል::

"እባብ መናደፍ ባሕሪው መሆኑን ገልፀው፤ "እኛ ግን ለእባብ አስተሳሰብ ላላቸው ገፊ አካላት እባብ በመሆን ሳይሆን የሰው አዕምሮ በመጠቀም ልቀን ማላቅ መርዙን ማስተፋት ይገባናል ብለዋል:: ተማሪዎቹም አሁን ያሉበትም ሆነ እንሂድ የሚሉበት ቦታ አገራቸው መሆኑን ገልጸውላቸዋል::

አማራና ኦሮሞ የተሳሰረና የተቀላቀለ ነው ያሉት ዶ/ር ዐቢይ አዋጪው ጉዳይ በማይመች ሁኔታም ቢሆን የገጠመን ፈተና በመቋቋም ሕዝቡ አንድና የተዋኻደ ሆኖ አገሪቷን አንድ እንዲያደርጋት ልብ በልብ በመደማመጥ፣ በቆራጥነት ችግሩን በትዕግስት ማለፍ ይጠይቃል በማለት ተማሪዎቹ የገጠማቸውን ችግር በማስተዋልና በብልሃት እንዲያልፉት መክረዋል::

### "ችግሩን ለማለፍ ብሩህ አዕምሯችሁን ተጠቀሙ"

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በሰሞኑ ትኩረት ከሰጡበት ጉዳዮች መኻከል ሀገረ ማርያም ከሚገኘው ቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ጋር በቴሌ ኮንፈረስ ውይይት ያደረጉበት ይጠቀሳል:: ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በዩኒቨርስቲው በተፈጠረው ጊዜያዊ ችግር ተማሪዎች ሳይደናገጡ ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ አሳስበዋቸዋል:: "ፍሬ



# አርበኞች ግንቦት ሰባት በወቅታዊ ጉዳይ መግለጫ ሰጠ

የአርቦኞች ግንቦት ሰባት ለአንድነት እና ለዴሞክራሲ በወቅታዊው የሀገራችን የፖለቲካ ትኩሳትን አስመልክቶ በግንባሩ ዋና ጸሐፊ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ አማካኝነት መግለጫ ሰጠ፡፡ግንባሩ ይህንን መግለጫ ለመስጠት ያስገደደው ሰሞኑን በሰላማዊ መንገድ የፓለቲካ ትግል ለማካሄድ ወደ ሀገር ቤት የገባው ኦነግ ከመንግሥት ጋር የገባውን እሰጣ ገባ ተክትሎ ነው፡፡ ግንባሩ እንደ ኦነግ በኤርትራ በርሃ የትጥቅ ትግል ሲያደርግ የነበረ ቢሆንም ከመንግሥት ጋር በደረሰው የሰላም ስምምነት መሠረት በአሁኑ ሰዐት ከማንኛውም አመጽ የራቀ የፓለቲካ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ እንደሆነ ዋና ጸሐፊው በጋዜጣዊ መግለጫው ላይ አጽኖት ሰጥተው አብራርተዋል ፡፡ ሙሉ መግለጫውን እነሆ፤

### የትጥቅ ትግል ሀገራዊ ውድመትን ያስከትላል

የአርበኞች ግንቦት 7 ሊቀ መንበር አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ በወቅታዊ ጉዳይ ላይ ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጡ፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ አፈና እንዲያበቃ ከከፈሉት መስዋዕትነት ጋር፣ ኢሕአዴግም ውስጥ ለዚህ መስዋዕትነት ከከፈለው ሕዝብ ጋር የወገኑ አመራሮች በመኖራቸው ሀገሪቱ ከአስፈሪ ወደ ተስፋ ሰጪነት ተሸጋግሯለች ብለዋል፡፡

ያለፉትን ሂደቶችንና የተለያዩ ሀገሮችን ተሞክሮ በመመልከት አመፃን ያካተተ ትግል ለኢትዮጵያ አይበጅም፡፡ አንድ ቋንቋ አንድ ባህል ያላቸው የየመን፣ የሊቢያ እና የሶሪያ ሀገሮች ለዴሞክራሲ ብለው የጀመሯቸው ትግሎች ዛሬ ሀገራቸውን ሲኦል አድርጎታል፡፡ ምንም እንኳን አሁን ያለው ለውጥ ሙሉ ነው ባይባልም፣ ተስፋ የሚሰጥ፣በሰላምና ሕጋዊ በሆነ መንገድ መሥራት የሚቻልበት ነው፡፡ የእኛ ግንባር ከማንም ቀድሞ የመንግሥትን ጥሪ በመቀበል ወደ ሰላማዊ ትግሉ ለመሻገር ቁርጠኛ ወስኔ ማሳለፉ የሚታወቅ ነው፡፡ በኢትዮጵያ በዚህ ከቀጠለ ከአመፅ ጋር በተያያዘ አንድ ሺ ቦታ ላይ የተከፋፈለ ፣ የራሱን ሰራዊት ይዞ እርስ በርስ የሚናቆርበት ሀገርና ሕዝብ የማይሆንበት ምንም ዓይነት ምክንያት የለም በማለት ዋና ጸሐፊው ጨምረው ተናግረዋል፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ አሁን ያለው ነገር በምንም ዓይነት መንገድ እያጣቀሱ መሄድን የማይፈቅድ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ የፖለቲካ ትግል፣ ከየትኛውም ሀገር በላይ ሰላማዊና ህጋዊ የሆነ ትግል የሚያስፈልግበት አገር ነው ብለዋል፡፡

ግንቦት ሰባት ያመፃና ትጥቅ ትግሉን ለማቆም ከተስማማበት ጊዜ ጀምሮ በኤርትራ ይኖሩ የነበሩን 300 ወታደሮች ታጣቂዎች ትጥቅ እንዲፈቱ መደረጋቸውንና 140ዎቹ ወደ ወረታ ካምፕ መግባታቸው ቀሪዎቹ ወደ የሀገራቸው መላካቸውንና በሀገር ውስጥ ይንቀሳቀሱ የነበሩ 500 ታጣቂዎች ትጥቅ ለመመለስ የመንግስትን ጥሪ ብቻ እየተጠባበቁ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ማናቸውም አባሎቻቸው በማንኛውም አይነት አመፅ ላይ እንዳይሳተፉ መልዕክት ማስተላለፋቸውን የገለጹት የግንባሩ ጸሐፊ፤ እኛ ይህንን መልዕክት ካስተላለፍንበት ጊዜ ጀምሮ በስማችን ምንም አይነት ክስ ቀርቦብን የማያውቅ ሲሆን ይሄ የሚያሳየው እኛ በዚ ጉዳይ ላይ ያለንን የፀና አቋም የሚያሳይ ነው፤ ሌሎችም የፖለቲካ ድርጅቶች በተመሳሳይ መንገድ የፖለቲካ ፓርቲ ድርጅቶች ሰላምን በማስጠበቅ መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል ብለዋል፡፡

## የሪፐብሊካን የደህንነት ጠባቂዎች ወታደራዊ ትርዒት አቀረቡ

ታህሳስ 14/2011 ዓ.ም የሪፐብሊካን ኃይል በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ለስድስት ወር የወሰደውን ሥልጠና ማጠናቀቁን በማስመልከት ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አሕመድ በተገኙበት ትርኢቱን አቅርቧል፡፡

ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት የተጣለባቸውን የሥራ ኃላፊነት ለመወጣት በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ ደህንነታቸውን ለመጠበቅ፣ የሚቃጣባቸውንም ጥቃት መከላከል ዋናው ዓላማው ያደረገው ይህ ግብረኃይል፣ ያለውን ሙሉ አቅምና ዝግጁነት ለጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥና ለጠ/ሚ ዐቢይ አሕመድ በወታደራዊ ትዕይንት የታጀበውን ትዕይንት አቅርበዋል፡፡ ከነዚህም ትርዒቶች መካከል በእሳት ውስጥ በማለፍ ጠላትን ማጥቃት፣ ስካይ ዳይቪንግ ያሳዩ ሲሆን፤ ትርኢቱን ካቀረቡትና ሥልጠናውን አጠናቀው ከተመረቁት የሪፐብሊካን ኃይል አባላት መካከል ጥቂቶቹ ሴቶች ናቸው፡፡

አዲሱ የሪፐብሊካን የጥበቃ ኃይል አስፈፃሚ አካላትን እንደ ሌሎች የመከላከያ ክፍሎች ሕገ መንግሥቱን መከላከል ዋነኛ ተልዕኮው ነው ተብሏል፡፡ ይህ ግብረኃይል በሚኒስትሮች ደንብ ቁጥር 426/ በ2010 ዓ.ም የተቋቋመ ሲሆን፣ ይህንንም ትርዒት ማሳየት የተፈለገበት ዋና ምክንያት፣ ሕዝብ የመሪዎቹ ደህንነት ሁኔታ ሥጋት እንዳይገባው፣ አመራሮቹም ሥራቸውን በአግባቡ እንዳይሠሩ ለማደናቀፍ የሚሞክሩ ኃይሎችም እጃቸውን እንዲሰበስቡና እንዲጠነቀቁ ለማሳሰብም ጭምር እንደሆነ የተገለፀ ሲሆን፣ ሰልጣኞቹም በወሰዱት ሥልጠና በቂ ሥልጠና ማግኘታቸውንና የተሰጣቸውን ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት ዝግጁ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

መንግሥት የከፍተኛ አመራሮቹን ለመጠበቅ ያደረገው ነገር ይበል የሚያሰኝና የሚበረታታ ቢሆንም፣ "የሪፐብሊካን ሴኩሪቲ ጋርድ" የሚል መጠሪያ የተሰጣቸው ወታደሮች አሁን ካሉበት ደረጃ የተሻለና ሁሌም ከፍ ያለ የብቃት ጫፍ ላይ በመገኘት የሀገር መሪዎቹን በአስተማማኝ ሁኔታ ከጥቃት እንዲጠብቁ ተከታታይ የሆነ የውጭ ሀገር ሥልጠና የሚያገኙበት ዕድል ቢመቻች የበለጠ ውጤታማ መሆን ይቻላል፡፡

# ጀበና የመስበር ስነስርዓት በብሔራዊ ቤተ መንግሥት !



አሌክስ አብርሃም

የትም አገር ወታደራዊ የተኩስ ልምምድም ይሁን ትርዒት በሰው አምሳል በተሰሩ አሻንጉሊቶች እንደሚካሄድ የታወቀ ነው! እኛጋር ለምን ለወታደራዊ ትርኢት ጀበና ተመረጠ ?! ጓዶች ጉዳዩ <<ሲሪየስ >> ነው!! በብዙ የአገራችን ክፍሎች አንድ ባህል አለ ! ሰው ሲሞትና አስከሬኑ ከቤት ሲወጣ በር ላይ ጀበና ደሽ ተደርጎ ይሰበራል! መልእክቱ አንድም ሟች እንደሸክላ ተሰበረ ሲሆን ሁለትም የሞት መንፈስ ከእንግዲህ ልክ ቡና እንደተጠራ ጎረቤት ዘው ብሎ መመለስ እና የፈለገውን አንጠልጥሎ መሄድ ሲያምረው ይቅር ፣እዚህ ቤት ላይ እጣ ፋንታ የለውም በቃ የወሰደውን ወስዶ ተሸኝቷል እንደማለት ነው!! እንግዲህ የቤተ መንግስቱ 27 ጥቁር ጀበና በሪፐብሊኩ ልዩ ሃይል መንኮታኮቱ ያለፈው የአፈና የእስር የግድያ ስርዓት እንደሞተ ዘመድ ጀበና ተሰብሮ ተሸኘ የሚል ዕድምታ ሳይኖረው አልቀረም! (ነው ብያለሁ ነው)

ወዲህም ጀበናው ለህዝብ ወሳኝ መልእክት አለው! የዘመናት ታሪካችን ሲወሳ አንድ ኢትዮጲያዊ ቤተሰብ ሩብ ያህል እድሜውን የሚፈጀው ጀበና ከቦ ሲያወራ መሆኑ እሙን ነው! እንግዲህ ጀበናውን ደሽ የማድረግ ተምሳሌቱ ዳይ ወደስራ የሚል ቆፍጣና ትዛዝ ቢጤም አለበት! ሃሜት በቃ ፣ ወሬ በቃ ፣ ጉልት ብሎ ድህነት ጋር <<ሶሻል ላይፍ>> መመስረት በቃ ! እዚህ ላይ ሴቷ ወታድር ለምን አጎንብሶ መተኮስ አስፈለጋት ?ወሳኝ ጥያቄ ነው ! ያጎነበሰችውን ልጅ ምስል ተመልከቱ ቀጥ ብላ መተኮስ አቅቷት ነው ? በፍጹም !መቀናጣት አምሯት ነው? በጭራሽ ! ነገሩ ወዲህ ነው! ለዘመናት በየጓዳው አጎንብሰው ቡና ሲቀዱ የኖሩ ሴት እህቶቻችን እድሉ ከተሰጣቸው የባህልና የወግ ጫና ተሸክመው እንዳጎነበሱ ጠላትን መከላከል እንደሚችሉ ያስጎነበሰቻቸውን አገር አጎንብሰው ቀና ሊያደርጓት ብቃቱ እንዳላቸው እንማር ዘንድ ነው (ነው ብያለሁ ነው)

እንግዲህ ጀበናን ጀበና ያነሳዋልና አንድ ነገር ብየ ልጨርስ ! አገራችን ከምታመርተው ቡና ግማሹ አገር ውስጥ ተጠጥቶ ያልቃል! አስባችሁታል ? አገራችን ላይ የሚገኘውን ቆዳና ሌጦ አንድ እንኳን ሳናስቀር ወደውጭ በርካሽ እንልከዋለን መቸስ ቆዳ ከበን አናወራ ! የምናመርተውን የቅባት እህልም እንደዛው ወደመድሃኒት ወደዘይት ወደሌላም ምርት ለመቀየር ጊዜ ጉልበትና እውቀት ይጠይቃላ ! ቡናዋን ግን ባንድ ማንከሽከሻና ባንድ ጀበና እዳዋን ጨርሰን እዚሁ ፉት ነው! ዶላርኮነው የምንጠጣው ጓዶች !ምንዛሬኮ ነው እንደቀልድ ፉት የምንለው !! በየኬላው ዶላር እናሯሩጣለን እንጅ እያንዳንዱ ሰው ቢመረመርኮ ራሱ ጆንያ ሙሉ ዶላር ነው! ብዙሃኑ ወጣት ቦርጭ ያወጣው ድራፍቱ መሰላችሁ እንዴ ? በየመንገዱ የጀበና ቡና የሚጠጣው ህዝብ ዶላር እያቆረኮ ነው! ሃሃ (ትንሽ አጋነንኩት እንዴ? ታዲያ ካልተጋነነ ምኑን የፖለቲካ ትንታኔ ሆነው)

ወገኖቸ ጨዋታችን እንዳለ ሆኖ. . . እንደአገር በስልጠናና ዲስፕሊን የታነጸ ጠባቂ ማደራጀት ጥሩ ቢሆንም ቅሉ ቅዱስ ቃሉ እንደሚለው ((((((((እግዚአብሔር ፡ ከተማን ፡ ካልጠበቀ ፡ ጠባቂዎች ፡ በከንቱ ፡ ይደክማሉ)))))))) ነውና እግዚአብሔር ህዝባችንንና አገራችንን ይጠብቅ !!

# አስደናቂው ውሻ

መሐመድ እስማኤል





እንደው እግር ጥሏችሁ ጃፓን ቶኪዮ ከተማ ብትደርሱ የዚህን ውሻ ሀውልት በአንድ ባቡር ጣቢያ ውስጥ ታገኙታላችሁ:: ይህ ውሻ ለ10

አመታት ፍቅርን የሰበከ ታማኝነትን ያወጀ በመሆኑ ጃፓናውያን ይኮሩበታል ይወዱታል:: በነገራችን ላይ የዚህ ውሻ ታሪክ ፊልም ሆኖ ተሰርቷል:: ይህ ውሻ ስሙ ሀቺኮ ተብሎ የሚጠራ ሲሆን የፕሮፌሰር ኢዛቡሮን ውሻ ነበር:: ፕሮፌሰሩ ውሻውን በፍቅር አሳደጉት:: ሁሌም ውሻው ጠዋት አብሮ ባቡር ጣቢያ ሄዶ ፕሮፌሰሩን ሸኝቶ ይመለሳል ማታ 11 ሰዓት ባቡር ጣቢያ ሄዶ ይቀበለውና ቤት ድረስ አብሮ ይመጣል:: ታድያ ከእለታት ሁሉ በአንዱ ከፉ ቀን በግንቦት 21 - 1923 ዓ.ም ውሻው ፕሮፌሰሩን ሸኝቶ ማታ እንደልማዱ ሊቀበላቸው ባቡር ጣቢያ ቢጠብቃቸው ሰውዬው ለካ በልብ ድካም ሞተው ኖሯል ሳይመጡ ቀሩ:: ውሻው ግን ይመጣሉ ብሎ ፕሮፌሰሩን ጠበቀ 1 ቀን ብቻ አደለም ጥቂት ወራትም አደለም ድፍን 10 አመት እንጂ እሳቸውን ጥበቃ እዛችው ባቡር

ጣቢያው ጋር 10 አመት ጠብቆ እዛው ሞተ:: እናም ሀቺኮ ወዳጁን 10 አመት በፅናት መጠበቁ አያስደንቅም?

# የጂማ ሕዝብ ደግ ነው !

ዘውድአለም ታደሠ

ወደአባ ጂፋር መናገሻ ከተማ ጂማ ገብቻለሁ! ይሄን አመት በስራ ምክኒያት ወደተለያዩ የኢትዮጵያ ከተሞች ሄጃለሁ ጂማ ስገባ ግን ቅልል ነው ያለኝ! በአራዶች አባባል “አየሩ ተበርግዷል!”

የሰዉ ትህትናና ግልፅነት ይማርካል! የከተማዋ መሃል አደባባይ ላይ የለማና አብይ ፎቶ በትልቁ ተሰቅሏል! ፎቷቸውን ሳይ ዘመዶቼን ያየሁ ይመስል ፈገግ አልኩ :) መኪናው፣ የሱቁ መስታወት፣ ሁሉም ነገር ላይ የለማ ፎቶ ታትሟል!

ምርጥ ክትፎ በልተን ዋጋው መቶ ብር መሆኑን ስንሰማ የአዲሳባን ባለሆቴሎች ረገምናቸው :) ምሳ የበላንባት ቤት የአሊ ቢራን ዘፈን ሰማሁ:: ቡና ምንጠጣባት ቤትም የአሊቢራን ዘፈን ሰማሁ:: ከተማዋ የለማና የአሊቢራ ትመስላለች :)

የጠጣነው ቡና በጉዞ የተመሳቀለች ነፍሳችንን የሰላም ባህር ውስጥ አንሳፈፋት! በየጥጋጥጉ በጥቂት ዱካዎች ተከበው ከተቀመጡት ረከቦቶች መሃል የሚወጣው የእጣን ጭስ እንደባቢሎን ግንብ ቀጥ ብሎ ወደሰማይ ይተምማል! ምን እንደነካኝ እንጃ ብቻ የጅማን መሬት ገና ስረግጠው የሆነ ደስታ አጥምቆኛል!

ቡና ስንጠጣ ያገኘነው ትሁት የአራተኛ አመት የዩኒቨርስቲ ተማሪን ስለጂማ ስንጠይቀው እንዲህ ነበር ነፍስ በሚያክም ቃል አራት አመት የተማረባት ጂማን የገለፃት …«የጂማ ህዝብ ደግ ነው!»

ግዜ ቢኖረኝና ዞር ዞር ብዬ ያየሁትን በተረክሁላችሁ ደስ ባለኝ! ጀምኣው ግን ሰላም ነህ ወይ?



# “እነግ በኦሮሞ ሕዝብ ተገፍቶ መውደቁ አይቀርም”

## መምህርና አክትቪስት ስዩም ተሾመ

መምህርና አክትቪስት የሆነው ስዩም ተሾመ በሀገራችን ፖለቲካዊ ጉዳዮች ዙሪያ በሚፅፋቸው መጣጥፎች በስፋት ይታወቃል፡፡ ባለፈው ዓመት አጋማሽ በሀገሪቱ የተፈጠረውን ለውጥ ተከትሎ ወደ ሀገር ቤት የገባውና በታጣቂ ኃይሎቹ አማካይነት በኦሮሚያ የተለያዩ ቦታዎች የሚያደርጋቸውን እንቅስቃሴዎች ተከትሎ ባለው ወቅታዊ ጉዳይ ዙሪያ ከግዮን ጋር ያደረገውን ቆይታ እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡ በተመሳሳይ የኦፌኮ (የኦሮሞ ፌደራል ኮንግረስ) ከፍተኛ አመራር የሆኑት አቶ ኦልባና ሌሊሳ የሰጡትን ቃለምልልስ በገጽ 23 እና 24 አቅርበነዋል፡፡ መልካም ቆይታ፡፡

**ግዮን፡- ኦነግ ወደ ሀገር ቤት በገባበት ወቅት ከመንግሥት ጋር የደረሰው ስምምነት ምን ቢሆን ነው "ትጥቅ አልፈታም" ያለበት ምክንያት?**

**ስዩም፡-** የስምምነቱን ይዘቱን አስመልክቶ በይፋ የተገለፀ ነገር የለም፤ መንግሥት ባለበት ሀገር ውስጥ የትጥቅ ትግል ሲያደርግ የነበረ ቡድን ወደ ሀገር ውስጥ ሲገባ፣ ይጠቀምበት የነበረውን የጦር መሳሪያ ማስረከብና ትጥቅ የመፍታት ግዴታ አለበት ተብሎ ይታመናል:: በዚህና በተዛማጅ ጉዳዮች ዙሪያ የተደረሱ ስምምነቶችን የሚያመለክቱ መግለጫዎች ባይኖሩም፣ መንግሥት ወዳለበት ሀገር ሠላማዊ ትግል ልታደርግ አምነህ ስትመጣ ትጥቅ የመፍታትህ ጉዳይ የመወያያ አጀንዳ ሊሆን አይገባም::

መንግሥት አለ ብሎ አምኖ ተቀብሎ ከመንግሥት ጋራ ድርድር ያደረገ ቡድን፣ ወደ ሀገር ሲገባ ትጥቁን መፍታቱ ግድ ነው፣ ምንም የሚያጠያይቅ ጉዳይ አይደለም:: እኔ እንደሚመስለኝ ምናልባት ታጣቂ የነበሩትን ኃይሎች መልሶ ማቋቋምና ወደ መደበኛ ሕይወታቸው እንዲገቡ በማድረግ ረገድ የተስማማቸው ስምምነቶች ላይ ያልተሟሉና የተጓደሉ ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ እንጂ፣ የኦነግ ትጥቅ የመፍታት ጉዳይ በትልቅ ደረጃ ለውይይት የሚቀርብ አይደለም::

የትጥቅ ትግል የምታደርግ ድርጅት ስትሆን መንግስታዊ ሥርዓቱን አስወግደህ፣ የፖለቲካ ስልጣኑን ትይዛለህ ወይም ስምምነት በማድረግ መንግስት መኖሩን አምነህ ተቀብለህ ፣በአንድ ሀገር ውስጥ ሁለት መንግስት ሊኖር ስለማይችል፣ ትጥቅ ፈትተህ ለመግባት ትስማማለህ ማለት ነው:: ኦነግም በዚህ መንገድ (ማለትም በሁለተኛው) የመጣ ስለሆነ፣ ትጥቅ መፍታቱ ተገቢ ጉዳይ ነው ብዬ ነው የማምነው::

**ግዮን፡- ሰሞኑን የኦነግ ሊ/መንበር አቶ ዳውድ ኢብሳ ሰራዊታቸው ዕርምጃ ለመውሰድ እንደሚገደድ የተናገሩበትን መግለጫ ተከታትለኸዋል ብዬ አስባለሁ፤ እሱንስ እንዴት አየኸው?**

**ስዩም፡-** ኦነግ እንደ ድርጅት ብቻውን የቆመ አይደለም፣ ተከፋፍሏል:: የተለያዩ ቦታዎች ተሰነጣጥቆ ሁሉም "ኦነግ ነኝ" እያለ ነው:: እንግዲህ ከእነዛ ውስጥ አንዱን ወገን ነው ለይተን እያየን ያለነው፤ በአቶ ዳውድ ኢብሳ የሚመራውን ቡድን:: ምናልባት ካስታወስክ ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አሕመድ ወደ ኤርትራ ከሃያ ዓመት በኋላ ሄደው ለሰላም ስምምነት ንግግር ሲያደርጉ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ይህን የአቶ ዳውድ ኢብሳን ቡድን አነጋግረው እንደነበር ሰምተናል:: ከዛ በኋላ ደግሞ ሊያገኟቸው ሙከራ ሲያደርጉ እንዳልተገኙ፣ የሰላም ስምምነቱ ላይም ለመሳተፍ ፍቃደኛ እንዳልነበሩ ተገልፃ ነበር፣ በተለይም ማኅበራዊ ሚዲያዎች ላይ::

ከዛ ቆይቶ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንት አቶ ለማ መገርሳና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዶ/ር ወርቅነህ ገበየሁ አስመራ ሄደው ዳግም ተነጋግረው ነው ከስምምነት ላይ መድረስ የቻሉት:: ምናልባት የሰላም ጥያቄውና የስምምነቱ ጉዳይ ከሁለቱም ወገኖች በአቻ ፍላጎት የመነጨ ነው ብዬ አላምንበትም፤ እኔ በግሌ:: በዶ/ር ዐቢይና የለማ ቡድን ሁሉም የታጠቁ ቡድኖች መታረቅና ወደ ሀገር ቤት መግባት አለባቸው በሚል ዕሳቤ ግፊትና ጫና በመደረጉ የገቡ፤ ምናልባትም ደግሞ የአቶ ዳውድ ኢብሳ ኦነግ ተቀምጦበት የነበረው የኤርትራ መንግሥት ከኢትዮጵያ ጋር ስምምነት ማድረጉ፣ የኦነግ ቡድኖች ሊንቀሳቀሱባቸው ይችሉ የነበሩ እንደ ሱዳን ያሉ ሀገሮች ከኢትዮጵያ ጋር መስማማታቸው፣ በለውጡ ቡድን አማካይነት ኢትዮጵያ አንፃራዊ በሆነ መልኩ ወደ ተሻለ ሰላም መሸጋገሯ፣ ይሄን የኦነግ ቡድን መሸሸጊያና ድጋፍ እንዲያጣ በማድረጉ ምክንያት ወደ ሀገር ውስጥ ለመስገባት ተገዶ የመጣ ነው የሚመስለኝ::

ሙሉ ደስተኞች ሆነው የገቡ ስላልሆኑ ይመስለኛል አንዴ ከትጥቅ መፍታት ጋር በተያያዘ የሚናገሩት፣ አሁን ደግሞ "ሰራዊቴ እርምጃ እንዲወስድ ትዕዛዝ ሰጥቻለሁ" የሚሉት:: እንዲህ ዓይነቱ መግለጫ በተጨባጭ እውነታ ላይ ያልተመሰረተ፣ ከአንድ ኃላፊነት ከሚሰማው የፖለቲካ ቡድን የማይጠበቅ፣ አላስፈላጊ ዋጋ ሊያስከፍል የሚችል ነገር ነው፤ በኦቶ ዳውድ ኢብሳ ንግግር ላይ የተመለከትኩት::

**ግዮን፡- ኦነግ አንዴ ከኦዴፓና ከፌደራል መንግሥቱ ጋር ተስማምቻሁ ሲል፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሲጠላና በተለያዩ የኦሮሚያ ከተሞች አላስፈላጊ እንቅስቃሴ ሲያደርግ መንግሥት በታጋሽነትና በሆደሰፊነት ነገሮችን መታዘቡ በዝቷል የሚሉ ወገኖች አሉ::**

**ስዩም፡-** የመንግሥት ታጋሽነትና ነገሮችን በለዘብተኝነት ብሎም በአስተዋይነት መልኩ ለማስተናገድ መሞከሩ ትልቅ ነገር ነው:: እርግጥ ነው ይህንን ክፍተት ተጠቅሞ በዜጎች ሕይወት፣ በሀገር ሠላምና ደህንነት ላይ አደጋ ሊከሰት ይችላል፤ እሱ የራሱ የሆነ አንድ ተፅዕኖ አለው:: የዜጎች ሰላምና ደህንነት መከበር የሚያጠያይቅ ጉዳይ እንዳለ ሆኖ በአንድ የፖለቲካ ቡድን ላይ ነጥለህ የኃይል ዕርምጃ ስትወስድ ተፅዕኖው ከእዛ የፖለቲካ ቡድን አመራሮች ይልቅ፣ የቡድኑ ደጋፊ በሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች ላይ መገፋትን ነው የሚያስከትለው::

ስለዚህ ስለመደመር፤ ስለ አንድነትና ስለይቅርታ እየተናገርን ባለበት ወቅት ተቻኩሎ የኃይል ዕርምጃ መውሰድና አንድን የፖለቲካ ቡድን ለይቶ መገፋት ተገቢነት አለው ብዬ አላምንም:: ምናልባት ነገሮችን በጥልቀት ከተመለከትነው የሕወሓት ቡድን እየፈፀመ ያለው ነገርና በኦነግ ታጣቂዎች እየተፈፀመ ባለው ነገር መካከል ሰፊ ልዩነት የለም::ሁለቱም ሰላምና መረጋጋት በሀገሪቱ እንዳይፈጠር እየተንቀሳቀሱ ያለበት ሁኔታ ነው ያለው::

ኦነግን ብቻ ሳይሆን ሕወሓትንም በብልሃት በትዕግስት እንዲሁም ነገሮችን በጥንቃቄ መያዝ አስፈላጊ ስለሆነ በዛ መንገድ እየተሄደበት ያለው የመንግሥት ታጋሽነት እንደ ጥሩ አመለካከት ሊወሰድ ይገባል፤ ጉዳቶችን ይቀንሳልና:: ይህ እንዳለ ሆኖ ወደ አልተፈለገ አቅጣጫ ምናልባትም የጠ/ሚ/ር ዐቢይን አመራር ወደ ኃይል የመግፋት አዝማሚያዎችን እመለከታለሁ፤ እሱ ትክክል አይደለም:: ምክንያቱም ከዚህ ቀደም ባየነው ታሪክ መሰረት በሕዝብ ግፊትና ጫና ነው መንግሥታት አምባገነን ሆነው የኃይል ዕርምጃ የሚወስዱት::

**ግዮን፡- ለምሳሌ?**

**ስዩም፡-** የደርግ መንግሥት አምባገነን የሆነው በ1967 ዓ.ም ይመስለኛል:: ጓድ መንግሥቱ ኃ/ማርያም በጥይት ጉዳት ከደረሰበት በኋላ ነው የኃይል ዕርምጃ ውስጥ የገባው:: ተመሳሳይ የሆነ ድርጊት በዶ/ር ዐቢይ ላይም ተደርጓል፤ ዶ/ር ዐቢይ ላይ የምታየው ለየት ያለ ነገር ምንድን ነው፣ ግጭቶች ጫናዎችንና ብሎም ጥቃቶችን በተመለከተ ያሉ ጉዳዮችን በጥንቃቄ ይዞ፣ ችግሮችን ለመፍታት ጥረት ማድረጉ ትልቅ ለውጥና ዕመርታ ይመስለኛል:: በፍጥነት የኃይል ዕርምጃ ለመውሰድ አልሞከረም፣ አላሰበም:: ይሄ ትልቅነት ነው::

**ግዮን፡- ባለፉት 27 ዓመታት በተለየ ሁኔታ የኦሮሞ ሕዝብ ሲበደል ነበር፤ ከዛም በፊት እንዲሁ:: ለዘመናት የዘለቀው የኦሮሞ ሕዝብ መከራ መቼ ነው የሚያበቃው? ኦዴፓና ኦነግ መስማማት ካልቻሉስ የእዚህ ማኅበረሰብ መጨረሻ ምን ይሆናል?**

**ስዩም፡-** የኦሮሞ ሕዝብ እንደማንኛውም ሕዝብ ስለምና መረጋጋት ይፈልጋል:: ዕድገትም ይፈልጋል:: አሁን ጥሩ ሚና የሚጫወቱ ቡድኖች ወደ አመራርነት እንዲመጡና ሥልጣን እንዲይዙ ይሻል:: የቲም ለማ ቡድንና ጠ/ሚኒስትሩ እየወሰዱት ላለው ዕርምጃና መልካም የለውጥ ጅምር ደግም ይህ የኦሮሞ ሕዝብ ትልቅ ድጋፍ እንዳለው በርግጠኝነት ልነግርህ እችላለሁ:: የተወሰኑ የፖለቲካ ቡድኖች አመራሮችና ግለሰቦች (ለምሳሌ የኦነግ አመራሮች) በዚህ ዓይነቱ ዕርምጃ ደስተኛ ላይሆኑ እንደሚችሉ መገመት ይቻላል:: እንደ ጠቅላላ የኦሮሞ ሕዝብ ካየኸው ግን ሰላምና ደህንነቱ መረጋገጥ ስላለበት፣ በየትኛውም የኦሮሚያ አካባቢ እንደዚህ ዓይነት እንቅስቃሴዎች ድጋፍ የላቸውም::

እንዲህ ዓይነት አፍራሽ ዓላማ ያላቸው የፖለቲካ ቡድኖች በሂደት ከሀገሪቱ ፖለቲካና ከክልሉ ፖለቲካ ውስጥ እየተገፉ የሚወጡበት ሁኔታ ይፈጠራል:: ምክንያቱም የሕዝብን መብት ከማስጠበቅ ይልቅ ሕዝብን መጠቀሚያ የሚያደረጉ ቡድኖች በሀገሪቱ ፖለቲካ ውስጥ ፋይዳ ያለው ሚና አይጫወቱም:: ተቀባይነትም አያገኙም:: ድጋፍና ተቀባይነት የሌለው የፖለቲካ ቡድን ደግሞ ያው ጊዜውን ተብቆ መውደቁ የማይቀር ነው፤ አሁን በዚህ መንገድ እየተጓዙ ያሉት የፖለቲካ ቡድኖች ሕወሓትም ሆነ ኦነግ ተመሳሳይ ዕጣ ፈንታ እንደሚገጥማቸው በርግጠኝነት መናገር

ይቻላል:: ኦነግ በዚህ መንገድ ከቀጠለ በኦሮሞ ሕዝብ ተገፍቶ መውደቁ አይቀርም::

**ግዮን፦ በዚህ ግጭት አትራፊ ማነው? …… ከኦነግ እንቅስቃሴ ጀርባ ትግራይ ውስጥ የመሸገው የፀረ ለውጥ ኃይል እጅ አለበት የሚሉ አስተያየቶች እየተበራከቱ ነውና::**

**ስዩም፦** እንግዲህ አንድ መታወቅ ያለበት ነገር ሕወሐት ለ27 ዓመት በዚህች ሀገር ላይ የነበረውን የበላይነት ነው ያጣው፤ ፈላጭ ቆራጭነቱን ተነጥቆ ወደ ትግራይ ሄዷል:: ከዚህ በኋላ ኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ከተዘረጋ፣ ነጻና ትክክለኛ ምርጫ ከተካሄደ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ምንም ዓይነት ፋይዳ ሊኖረው የማይችል ቡድን ነው:: ሕወሓት ሥልጣን ላይ በነበረበት ወቅት በዘረፋ ያካበተውን ከፍተኛ ሐብት ይዞ ነው ወደ መቀሌ የሸሸው፤ ስለዚህ አሁን የተጀመረው የለውጥ ሂደት ስኬታማ እንዳይሆን ይፈልጋል በዋናነት::

ምክንያቱም በሁሉም የሀገሪቱ ክልሎች ሰላምና መረጋጋት ከመጣ፣ ለውጡ ቀጣይነት ካለው የሕወሓት መጨረሻ ውድቀት ከመሆኑ ባሻገር በወንጀል ተጠርጥረው መቀሌ የመሸጉት ሰዎች ለሕግ ተላልፈው ይሰጣሉ:: ከዚህ በመነሳት ሰላምና መረጋጋት እንዳይፈጠር የሚፈልገው ማነው ስትል ለኦነግ አቀባበል ከማድረግ ጀምሮ፣ ግብዣ ከማድረግ ጀምሮ፣ አሁን በተለያዩ አካባቢዎች የተነሱትን ሁከቶችና ብጥብጦች ከመደገፍና ከማበረታታት አንጻር ስትመለከተው በቀዳሚነት የሕወሓት እጅ እጅ እንዳለበት መገመት ትችላለህ::

ይሄ ቡድን ከአዲስ አበባ ወደ መቀሌ ከሄደ በኋላ በቤንሻንጉል በሱማሌ በኦሮሚያ የተለያዩ አካባቢዎች በሰሜን ጎንደር ቅማንት፣ ራያ አካባቢ አፋርን የመሰሉ ቦታዎች ላይ በእጅ አዙር ከመሳተፍ ባሻገር ከዚህ ቀደም አባል የነበሩ የጦርና የደህንነት ኃላፊዎችን በመጠቀም ብጥብጥ እያስነሳ ነው ያለው:: ይሄን ብጥብጥ የሚፈልግ ቡድንና ግርግሩን ተጠቅመው ሥልጣን መያዝ የሚፈልጉ ቡድኖች ኦነግን ጨምሮ፣ ሌሎች አክራሪ የብሔርተኝነት አቋም የሚያራምዱ የፖለቲካ ቡድኖች ተመሳሳይ እንቅስቃሴ ሊያደርጉ ይችላሉ:: እያደረጉም ነው:: በጥቅሉ ሕወሓትን ጨምሮ አክራሪ የብሔር የፖለቲካ የሚያራምድ ቡድኖች በአንድ ወገን፣ ለውጡን የሚደግፉና የሚያስቀጥሉ ደግሞ በሌላ ወገን ሆነው የተፋጠጡበት ሁኔታ እንዳለ ነው የሚታየኝ:: የብሔርተኞቹ አካሄድ ሀገርን የማፍረስ፣ ሰላም የማደፍረስና በአጋጣሚው ተጠቅሞ ሥልጣን መያዝ ፣እስከሆነ ድረስ አላማቸው ነገሮችን በለዘበ መንገድና በብስለት መፍታት ከተቻለ መጨረሻቸው ክስረት ነው የሚሆነው::

**ግዮን፦ የኦዴፓ ጽ/ቤት ኃላፊ ዶ/ር ዓለሙ በካምፕ ከሚገኘው የኦነግ ሠራዊት ውስጥ ትግርኛ ተናጋሪዎች ተገኝተዋል ብለዋል፤ ይሄ ምንን ያመለክታል?**

**ስዩም፦** እስካሁን ድረስ ስንታገለው የነበረው የፖለቲካ ቡድን ማንነትና ተፈጥሯዊ ባሕሪይ ጠንቅቀን ያወቅነው አይመስለኝም:: ከዚህ ቀደም በሕወሓት የተመሠረተውን መንግሥት አምባገነን ነው ብለን ነበር ነገር ግን በ1997 ዓ.ም ምርጫ ከዛም በላይ እንደሆነ አረጋግጠናል:: ይሄ ቡድን አሁን ተገፍቶ ትግራይ ስለተቀመጠ ቴክኒካሊ የበላይነቱ የለውም፤ አሁን እያደረገ ያለው ለውጡን ለመቀልበስ ፍላጎት ካላቸውና ሕገ -መንግሥቱን ከሚንዱ ኃይሎች ጋር ጥምረት ፈጥሮ መሥራት ነው:: ለእዚህ ደግሞ ከገንዘብም አልፎ የሰው ኃይል ድጋፍ እያደረገ እንዳለ ነው ይሄ መረጃ የሚያሳየው::


ሰዩም ተሾመ

የሕወሓት መንግሥት የማፍያ ቡድን ነበር አሁንም ነው:: ብዙዎቻችን የምናውቀው የማፊያ ቡድን የመንግሥት ሥልጣን ሰርስሮ በመግባት የራሱን ፍላጎት የሚያሟላ አድርገን ነው የምናየው፣ "የማፊያ መንግስት" የምንለው ግን ከዚህ የተለየ ነው:: ቡድኑ ራሱ የፖለቲካ ሥልጣኑን ይዞ ዘረፋና ሌብነትን ጨምሮ የተለያዩ ወንጀሎችን መፈፀምና ከሕግ ተጠያቂነት ነጻ መሆን ነው:: ላለፉት 27 ዓመታት በዚህ መንገድ የሚሰራው የሕወሓት የማፍያ መንግሥት ነው::

ይሄ አሳፋሪ የማፍያ ቡድን በዚህ ሰዓት ተገፍቶ በተጠላበት ክልል ላይ ሆኖ በተለያዩ ቦታዎች ሁከትና ብጥብጥ ለማስነሳት አቅሙ የፈቀደውን በሙሉ እያደረገ ነው:: በሰው ኃይል ድጋፍ ጨምሮ በሶማሌ ክልል የተፈጠረውን አሁን ደግሞ ከኦነግ ጋር የሚያደርገውን እንቅስቃሴ በማስረጃነት መጥቀስ ይቻላል:: የኋላው መግለጫም ይሄንን ነው የሚያመለክተው ገንዘብ እንደ ኩንትታል ጤፍ በጆኒያ ተጭኖ በተለያዩ አካባቢዎች የሚያዘው እነዚህን የፖለቲካ ቡድኖች ለመደገፍ ሲባል ነው::

**ግዮን፦ ኦነግ በተለያዩ አካባቢዎች የሚያደርጋቸውን እንቅስቃሴዎች በተመለከተ የኦሮሞ ፖለቲካ ድርጅቶች አስተያየት ሲሰጡ መግለጫ ሲያወጡ አለመታየታቸውን ተከትሎ ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች በኦነግ ጥላ ሥር ናቸው እየተባለ ነው::**

**ስዩም፦** በመጀመሪያ ደረጃ አሁን የምትለው የኦነግ ቡድን ወሳኝ የሆነ የፖለቲካ አቅም ያለውና ተፅዕኖ መፍጠር የሚችል አይደለም:: ከዛ ይልቅ ኦነግ ሲባል እንደ ድርጅት የኦሮሞን ሕዝብ መብትና ነጻነት እኩልነት እንዲሁም ፍትሓዊ ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ በሚል የትግሉን እንቅስቃሴ የጀመረ፣ የትግሉን አርማ የያዘ ፣ስለ ኦሮሞ ሕዝብ ድምፅ ሆኖ ቅድሚያ የተነሳ ቡድን ነው:: ይህ በታሪክ ነው ከዛ በዘለለ ግን መሬት ላይ በተጨባጭ ይህ ነው ብለህ ልታስቀምጥ የምትችለውና ባለፉት ዓመታት ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል እንቅስቃሴ ሲያደርግ ነበር ወይ ብትል ምንም ነገር አልሠራም::

ይሁን እንጂ የሕዝቡን አርማና ዓላማ የያዘ የፖለቲካ ድርጅት እንደመሆኑ መጠን በብዙኃኑ ልብ ውስጥ ሊኖር ይችላል:: ያ እስከሆነ ድረስ ብዙኃኑ የኦሮሞ የፖለቲካ ድርጅቶች ይሄንን ነገር ፊትለፊት የመጋፈጥና ከብሔርተኛው ኦነግ ጋር ላለመጋጨት ጥረት ሲያደርጉ ይስተዋላል:: ይሄ ይሄን የፖለቲካ ቡድን በመፍራት ሳይሆን ቀድሞ ለነበረው ስብዕና ፣የትግል አርአያነት ክብር ከመስጠትና ወደ አላስፈላጊ እሰጣ ገባ ውስጥ ላለመግባት የሚያደርጉት ጥረት እንጂ ሌላ ዓላማ የለውም::

ያንን ስያሜ የያዘው ቡድን አሁን አፍራሽ በሆነ እንቅስቃሴ ውስጥ ሲሳተፍ፣ የኦሮሞ ሕዝብን ጥቅም በሚጎዳ ተግባር ውስጥ ተጨማልቆ ሲታይ በሂደት ከሕዝብ ልብ ውስጥ እንደሚሄድና የተጀመረውም ለውጥ ሙሉ ድጋፍ እንደሚያገኝ፣ የኦሮሞ ሕዝብም ይህንን በአቶ ዳውድ ኢብሳ የሚመራውን ቡድን ወደ ማውገዝ እንደሚመጣ እምነት አለኝ::

**ግዮን፦ እናመሰግናለን::**

## አንደበት



"የእውነትና የእውቀት ቅዱስ ስፍራ መሆን የሚገባቸው ዩንቨርስቲዎች፣ ....የዘረኝነት "ማሰልጠኛ ቤተሙከራ" እስኪመስሉ ድረስ፣ ለጭፍን ስሜት፣ ለግርግር ግጭትና ለዘረኝነት ክፋት ሲሸነፉ ዕያየን ነው። የዘረኝነት በሽታውና ቁልቁለቱ የምር የሚታየን፣ የበሽታው መዘዞች ገንፍለው አፍጥጠው ሲመጡብንና፣ ነውጥ ተፈጠሮ ጥፋት ከደረሰ በኂላ ነው።"

*አቶ አባንግ ሜቶ*

*አዲስ አድማስ ጋዜጣ ታህሳስ 13 ቀን 2011 ዓ.ም*



"ሕወሓት አሁን ካለው የፌደራል መንግሥት ጋር ተስማምቶ ለመኖር ጥረት ማድረግ የሚችል ይመስለኛል። ቢሆንም ሕወሓት በጣም የተጠላ ድርጅት ነው። በጣም ብዙ ችግር፣ ግፍ ሲፈጽም የነበረ ነው። ማንኛውም የኢትዮጵያ ሕዝብ አይቀበለውም። የትግራይም ሕዝብ አይቀበለውም፤ በመሆኑም በኢሕአዴግ ውስጥ ያሉ ፓርቲዎች ይቀበሉታለል ብለን አናስብም።"

*አቶ አብርሃ ደስታ*

*አዲስ ማለዳ ጋዜጣ ታህሳስ 13 ቀን 2011 ዓ.ም*



"ኦህዴድ ማለት ላም የወለደችው ጥጃ ሲሞትባት ወተቷን ለማለብ ሲባል በኦሮሚኛ "ቢዖ" ይባላል፤ በገለባ የጥጃ ቅርፅ ያለው አሻንጉሊት ይሰራና ጨው እላዩ ላይ ረጭተው ለላሚቷ ያቀርቡላታል። ላሟ ጥጃ እየመሰለቻት ስትልሳት አንተ ወተቷን ታልባለህ። ኦህዴድ ማለት እንደዛ ነበር፤ የማይንቀሳቀስ ሕይወት የሌለው ጥጃ ነበር።"

*አቶ ሱሌይማን ደደፎ መንገድ*

*ቁም ነገር መጽሔት ታህሳስ 2011 ዓ.ም*



ጉንዳን መጥፎ ወቅቶችን ለማለፍ ክረምት ሳይገባ በትብብር ምግቡን እንደሚያዘጋጅ ሁሉ፣ ተማሪዎችም ወቅታዊ ችግሮችን ለመሻገር የጉንዳንን መንገድ መከተል እንጂ የመንጋ ወሮ በላ አንበጣ ስልት መከተል የለባቸውም።

*ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ*

*ለቡሌ ሆራ ዩንቨርስቲ ተማሪዎች ካደረጉት ንግግር የተወሰደ*

## ጠቃሚ ምክሮች

### ሀዘንን ለመቋቋም የሚረዱ ዘዴዎች

- ቤተሰቦችህና ወዳጆችህ የሚያደርጉልህን ድጋፍ ተቀበል፤ እንደ አስፈላጊነቱ ከሌሎች ጋር የምትሆንበትና ለብቻህ የምታሳልፈው ጊዜ ይኑርህ
- ለአመጋገብህ ትኩረት ስጥ፤ እንዲሁም እንቅስቃሴ አድርግ፤ ለጤና ተስማሚ የሆነ ምግብ ተመገብ፤ ውኃ በብዛት ጠጣ፤ እንዲሁም መጠነኛ የሰውነት እንቅስቃሴ አድርግ::
- ከጎጂ ልማዶች ራቅ፦ አልኮል ከመጠን በላይ ከመጠጣት ወይም ዕፆችን ከመውሰድ ተቆጠብ፤ እነዚህ ነገሮች የባሰ ችግር ይፈጥራሉ::
- ቋሚ ፕሮግራም ይኑርህ፦ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎችን የምታከናውንበት ቋሚ ፕሮግራም ማውጣትህ ሕይወትህ እንዲረጋጋ ይረዳሃል::
- የሚያዝናናህ ነገር አድርግ፦ ለአንድ ቀን ወይም ለተወሰኑ ሰዓታትም እንኳ ቢሆን ከተለመደው እንቅስቃሴ ወጣ ያለ ነገር ለማከናወን ጊዜ መድብ::
- ቅድሚያ የምትሰጣቸውን ነገሮች ገምግም፤ ይህን አጋጣሚ፣ በሕይወት ውስጥ ከሁሉ ይበልጥ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው ነገር ምን እንደሆነ ቆም ብለህ ለማሰብ ተጠቀምበት:: እንዲሁም ቅድሚያ በምትሰጣቸው ነገሮች ረገድ እንደ አስፈላጊነቱ ማስተካከያ አድርግ::

## ጠቅላላ እውቀት

### የአውሮፕላን ንድፍና ዓሣ ነባሪ

ለአካለ መጠን የደረሰ ሃምፕባክ ዓሣ ነባሪ ወደ 300 ኩንታል የሚያህል ክብደት ሲኖረው ይህም ሙሉ ጭነት ከጫነ ከባድ መኪና ጋር ይስተካከላል፤ ይህ ዓሣ ነባሪ ሰውነቱ በቀላሉ የማይተጣጠፍ ሲሆን በጣም ትልቅ የክንፍ ቅርፅ ያለው መቅዘፊያ አለው። ዐሥራ ሁለት ሜትር ርዝመት ያለው ይህ እንስሳ በባህር ውስጥ ሲንቀሳቀስ በጣም ቀልጣፋ ነው።

አስደናቂው ነገር ዓሣ ነባሪው በጣም ጠባብ በሆነ ቦታ መዞር መቻሉ ነበር፤ ምስጢሩም የነበረው በዓሣ ነባሪው መቅዘፊያ ቅርጽ ላይ እንደሆነ አውቀዋል። የመቅዘፊያው ፊተኛ ጠርዝ እንደ አውሮፕላን ክንፍ ልሙጥ ሳይሆን ወጣ ገባ ነው።

ዓሣ ነባሪው ውኃውን እየሰነጠቀ በፍጥነት በሚንቀሳቀስበት ጊዜ እነዚህን ወጣ ገባዎች፣ ዓሣ ነባሪውን ወደ ላይ በመግፋት እንዲንሳፈፍ የሚያደርገው ግፊት እንዲጨምር ያደርጋሉ፤ እንዲሁም ዓሣ ነባሪውን ወደ ኂላ የሚጎትተውን የውኃ ግፊት በመቀነስ ወደፊት የመወንጨፍ ኃይል ይጨምሩታል። ዓሣ ነባሪው ሽቅብ በሚወጣበት ጊዜም እንኳ ወጣ ገባዎቹ ውኃውን ክብ ቅርፅ በመሥራት ከመቅዘፊያው በላይ ሥርዓት ባለው መንገድ በፍጥነት እንዲያልፍ ስለሚያስችሉ ነው።

## ነጠላ ጥለት

‹‹ደጉ አምላኬ ሆይ...
ሽማነ ነህ ስላል፣ በድር አካላቴ
በጅህ መወርወሪያ፣
ተቀምሮ ሳለ፣ አካል ሰውነቴ
ማጉን አወፍረህ፣
ፈሳጊ እንዳለው፣ የጥለት አማራጭ
ያላንዳች መንተሪያ፣
ወርቀዘቦ አርገው፣ ህይወቴን ባቋራጭ››፡
እያልሁ ስማፀንህ፣
ፀሎት ልመናዬ፣
ከሌላ ሰው ፀሎት፣ ተደባልቋል መሰል
እርቃኔን አለሁኝ
ከሰው ተገንጥዬ፣ ከአይኖች ሳልጠለል።
ደራርበህ አልብሰህ፣
በጋቢ እያኖርከው፣ ሀገሩን በሙላ
ዋጋ እንደሌለው፣ እቅፍ እንደጠላ
ምነው እኔን ብቻ፣ አረከኝ ነጠላ።

*የወፍ ጎጆ ኤፍሬም መኮንን 2011 ዓ.ም*

## አባባል

- አምላክ ምላሽ የሚሰጠን በሶስት መንገድ ነው:: የመጀመሪያው ጥያቄያችንን "እሺ" ብሎ የምንፈልገውን ይሰጠናል:: ሁለተኛው "አይሆንም" ብሎ ሌላ የተሻለ ነገር ይሰጠናል:: በሶስተኛ ደረጃ ደግሞ "ታገስ" ብሎን እጅግ በጣም የተሻለ ነገር ይሰጠናል::
- ስራ የምንሄደው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ሳይሆን ህይወታችን ትርጉም እንዲኖራት ጭምር ነው:: ስራችን ለዛሬ ላለንበት ማንነታችን አብዛኛውን ክፍል ነውና::
- እያዳንዷን ሳንቲም ከቋጠርክ ምናልባት ሚሊየነር ትሆን ይሆናል፤ እያንዳንዷን ዶላር በአግባቡ ካወጣህ ግን ቢሊየነር የመሆን ዕድል ይሆርሃል::
- በዚች ምድር ላይ የከፋው ነገር ብቸኛ መሆን ሳይሆን ልክ ብቸኛ የሆንን ያክል እንዲሰማን በሚያደርጉ ሰዎች መከበብ ነው::
- የተለያዩ ነገሮች ደስታን ሊሰጡህ ቢችሉም፣ እውነተኛ ደስታን ግን የምታገኘው ከአምላክህ ዘንድ ብቻ ነው::
- በማንነትህና በአንተነትህ ደስተኛ እስካልሆንክ ድረስ መቼም ቢሆን ባለህ ነገር ደስተኛ አትሆንም::
- ጓደኝነት ልክ እንደ መጽሐፍ ነው..... ለመፃፍ አመታትን የሚፈጅ፤ ለማቃጠል ግን አንዲት ደቂቃ!
- የፍቅር ሃይል የሃይል ፍቅርን ሲያሸንፍ፣ ያኔ ዓለም እውነተኛ ሰላምን ማጣጣም ይጀምራል::
- እባብ ካየህ ፈጥነህ ግደለው! እባብን ለመግደል ኮሚቴ ማዋቀር አያስፈልግምና!
- ሃብት ማለት የኪስ በገንዘብ መታጨቅ ሳይሆን የአእምሮና የልብ ፀጋ ነው::



ብሩክ መኮንን

# አዲሱ ድብቅ ጦርነት በምሥራቅ አፍሪቃ

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ቻይና፣ ቱርክ፣ ሳውዲአረቢያ፣ አቡዳቢ፣ ኳታር፣ ሩሲያ፣ እስራኤል እና ፈረንሳይ በተለያየ መልኩ ዳግም አፍሪቃ አህጉርን ለመቀራመት ድብቅ የኢኮኖሚ ጦርነት በማካሄድ ላይ መሆናቸውን የሚያሳዩ ፍንጮች እየታዩ ነው።

ልክ እንደቀዝቃዛው ጦርነት የዓለም ኃያላን መንግሥታት በአፍሪቃ አህጉር ኢኮኖሚያዊ ፖለቲካዊ የበላይነት ለመቀዳጀት የራሳቸው ዕቅድ ነድፈው መንቀሳቀስ መጀመራቸውን ማረጋገጫ ባሳለፍነው ሳምንት የአሜሪካ መንግሥት በአፍሪቃ አህጉር የሚከተለውን ስትራቴጂ በማስተዋወቅ "ለአፍሪቃ የሚበጀውን የማውቅ እኔ ነኝ " የሚል አንድምታ ያለው ፖሊሲውን ይፋ አድርጓል፡፤

የዶናልድ ትራምፕ መንግሥት ይፋ ባደረገው አዲሱ በአፍሪቃ አህጉር የሚከተለው ፖሊሲ በዋንኛነት ቀደም ብለው ከአፍሪቃ ሀገራት ጋራ ጠንካራ የኢኮኖሚና የፖለቲካዊ ወዳጅነት የመሠረቱት ቻይና እና ሩሲያን በመቀደም በዓለምአቀፍ ደረጃ ልዕለ ኃያል ሆነው ለመውጣት በማሰብ ነው።

የፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕ ብሔራዊ ፀጥታ አማካሪ አምባሳደር ጆን ቦልተን የአሜሪካ መንግሥት በአፍሪቃ ላይ የሚያራምደው ነው ያሉትን አዲሱን የፖሊሲ ሐሳብ ይፋ ሲያደርጉ ላለፉት ዓመታት ቻይና በአፍሪቃ አህጉር ለግዙፉ የኢኮኖሚና የመሠረተ ልማት አውታር ግንባታ ላይ የተሳተፈችው ከአፍሪቃ ሀገራት መንግሥት ባለሥልጣናት በጉቦ ወይም ተገቢ ባልሆነ ጥቅም እንዲያገኙ ፕሮጀክቶቹ በከፍተኛ ምዝበራ ሌብነት የተቆራኘ በማድረግ ነው ሲሉ ቻይናን ከሰዋል፡

ቻይና ወደፊት በዓለምአቀፍ ደረጃ ኃያል ሆና ለመገኘት ዋንቤልት ዋን ሮድ የተባለ በባቡር እና በአውራ ጎዳና ከአፍሪቃ አህጉር ጋራ የገበያ ትስስርን ለመፍጠር እየሠራች ነው።

ለዚህም ድርጊቷ በምሥራቅ አፍሪቃ ቀንድ የምትገኘው ጅቡቲን እንደ ዋና መንደርደሪያዋ በመቁጠር የመካከለኛው ምሥራቅ፣ የደቡብ ኤዢያ እና የአውሮጳ ሀገራት የባሕር ትራንስፖርት የንግድ እንቅስቃሴን ለመቆጣጠር የሚያስችላት የጦር ሰፈር አቋቁማለች።

ቻይና በጅቡቲ ያቋቋመችው ጦር ሰፈር፣ አሜሪካ በምሥራቅ አፍሪቃ የሚንቀሳቀሱ የሽብር ቡድኖችን እንቅስቃሴ ለመግታት ከተቋቋመው የካምፕ ሌሚኒየር ጦር ሰፈር ጥቂት ማይሎች ርቀት ላይ ነው የሚገኘው።

ባለፈው ግንቦት ወር በጅቡቲ የሚገኘው የቻይና ጦር ሰፈር የሚለቀቅ አደገኛ የሆነ የብርሃን ጨረር አማካኝነት በአካባቢው ቅኝት የሚበሩ ዐሥር የአሜሪካ የጦር አውሮፕላኖችን ያበሩ የነበሩት ዐሥር አብራሪዎች ላይ ጉዳት አስከትላለች። ከዐሥሩ ሁለቱ አብራሪዎች ዐይናቸው ላይ ከፍተኛ ጉዳት እንዲደርስባቸው ማድረጓን የአሜሪካ ከፍተኛ የጦር ኃይል ባለሥልጣናት በማስታወቅ ነገሩን በቸልታ እንደማያዩት አስታውቀዋል።

ለጅቡቲ ከ2014 እስከ 2016 ዓ.ም ባሉ ሁለት ዓመታት ቻይና መንግሥት በረዥም ጊዜ ብድር የሰጠችው አጠቃላይ መዋዕለ ነዋይ በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ከሀምሳ እስከ ሰማኒያ አምስት ፐርሰንት እንደሚደርስስ ይፋ ያደረገው የአሜሪካ መንግሥት፣ የጅቡቲ መንግሥት፣ በቀይ ባሕር ላይ የሚጓጓዙ መርከቦች እንቅስቃሴ ቁልፉ ሥፍራ ያለውን የደራህሌይ ኮንቴነር ተርሚናል የማስተዳደሩን እና የመቆጣጠሩን ሥልጣንም በቻይና መንግሥት ቁጥጥር ሥር ለሚገኙ ተቋማት መስጠቱም አሜሪካን እንዳላስደሰታት ታውቋል።

አሜሪካ ከቻይና ቀጥሎ በአፍሪቃ አህጉር የተፈጥሮ ሀብትን ለመቀራመትና ሰፊ የገበያ ዕድልን ተጠቃሚ ለመሆን ሩሲያ ተመሳሳይ ስልትን በመከተል በአፍሪቃ ያላትን ተደማጭነት እያጎደለች ነው ስትል ትከሳለች።

አሜሪካ፣ ቻይና እና ሩሲያ በግዙፉ የኢኮኖሚ አውታር ግንባታዎች፣ የማዕድን ማውጣት ሥራ ላይ በመሳተፍ ከፍተኛ መዋዕለ ነዋይ በረዥም ጊዜ ብድር በመስጠት የአፍሪቃ ሀገራት የፋይናንስ አቅማቸው ነጻ እንዳይሆን፣የጌታና ሎሌ ገዥነት እንዲኖራቸው እየሠሩ ነው፣ ስትልም ወንጅላቸዋለች።

ቻይና ከ2016 ዓ.ም እስከ 2017 ዓ.ም በአፍሪቃ አህጉር በቀጥታ መዋዕለ ነዋይ ፍሰት 6.4 ቢሊየን ዶላር ኢንቨስት አደርጋለች። በቀጣዮቹ ዓመታትም የቻይና መንግሥት በቀጥታ ወይንም በበከፊል የመንግሥት ይዞታ ባላቸው ኩባኒያዎች አማካኝነት በተያዘ በጀት በርካታ ግዙፍ ፕሮጀክቶችን በባለቤትነት ተረክባ እያካሄዴች ትገኛለች።

እነዚህንና ሌሎች የቻይና መንግሥት በአፍሪቃ ከፍተኛ መዋዕለ ነዋይ በማፍሰስ መጠነ ሰፊ እንቅስቃሴን አሜሪካ በዝምታ አላይም፣ በሚል ይፋ ባደረገችው አዲሱ አፍሪቃን የሚመለከት ስትራቴጂካዊ እቅድ ሦስት ዋና ዋና ዘርፎች ላይ ትኩረት ያደረገ ነው።

## እነዚህ ሦስት የትኩረት አቅጣጫዎችም

1. አሜሪካ ከአፍሪቃ ሀገራት ጋር በንግድና በኢንቨስትመንት ዘርፍ የሁለቱም እኩል ተጠቃሚነትን መሠረት ያደረገ የኢኮኖሚ ትብብር መፍጠር፤
2. በመላው አፍሪቃ ያሉ የእስልምና አክራሪና አሸባሪ ድርጅቶችን እንቅስቃሴ በመመከት እንደ አይሲስ እና አልቃይዳ ያሉ የሽብርተኛ ድርጅቶች ለእኩይ ዓላማቸው የሚሆኑ ግለሰቦችን በመመልመል አቅማቸውን እንዳያደራጁ በፀረ ሽብር እንቅስቃሴ ከአፈሪቃ ሀገራት መንግሥታት ጋራ በጋራ መሥራት፣ በአሜሪካ ዜጎችና ጥቅሞች ላይ ያነጣጣሩ ጥቃቶች እንዳይፈፀሙ የሚያስችሉ ተግባራትን ማከናወን፤
3. አሜሪካ ለአፍሪቃ ሀገራት እንዲውል ከምትለግሰው የእርዳታ ገንዘብ አንድም ዶላር ቢሆን በተገቢው ሁኔታ ለተረጂዎች መዋሉን ማረጋገጥና ከዚሁ ጋራም እስከ አሁን ድረስ በመላው አህጉሪቱ ይካሄዱ የነበሩ የእርስ በእርስ ጦርነቶችን ለማስቆም ተቋቁመው በሥራ ላይ በሚገኙ፣ በተባበሩት መንግሥታት ሥር የሚንቀሳቀሱ የሰላም ማስከበር ግዳጆች ውስጥ ውጤታማ ያልሆኑ፣ የተቋቋሙበትን ዓላማ የማያሳኩትን ለመደገፍ የመደብነውን የእርዳታ የገንዘብ ድጋፍ እናቆማለን የሚሉት ናቸው።

አሜሪካ በአፍሪቃ የተፈጥሮ ሀብትን እንዲሁም ሰፊ የሆነ ገበያን ለመጠቀም ከቻይና ጋራ የጀመረችው እሽቅድድም በዚህ ሰሞን በተከታታይ ቀናት በሱማሊያ የሚንቀሳቀሰው የአልሸባብ ኃይል ላይ በወሰደችው ተደጋጋሚ የአየር ድብደባ እንዲሁም በደቡብ ሱዳን መንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣናት እንዲሁም የጦር መሳሪያ ያቀብሏቸዋል ባለቻቸው ወገኖች ላይ በጣለችው ማዕቀብ የአፍሪቃ የሰላም ዘብ እኔ ነኝ እያለች ያለ ይመስላል የሚሉ ብዙዎች ናቸው።

በዚሁ እንደ አዲስ የተቀሰቀሰ ድብቅ ጦርነት በቅርበት ከሚከታተሉ እውቅ የፖለቲካ ተንታኞች አንዱ፣ ተቀማጭነቱ ጆሃንስበርግ የሆነው ዊሊም ጋምድ ‹‹ አፍሪቃውያን ለሁሉም ኃያላንና ለበለፀጉ መንግሥታት ዘንድ ተፈላጊ መሆናቸውን ያረጋገጡበትን ዕድል ይዞ ነው የመጣው አዲሱ ፍጥጫ

‹‹ አሁን አሜሪካ በአፍሪቃ ሀገራት ሁለንተናዊ ዕድገትና ብልፅግና ላይ ተሳታፊ ለመሆን ያሳየችው ከፍተኛ ፍላጎት፣ የአፍሪቃ ሀገራት አሜሪካ እንዳሻት ከምታሾራቸው የዓለም ባንክ እና የዓለም የገንዘብ ድርጅት የሚያስፈልጋቸውን ብድርና የእርዳታ ገንዘብ ለማግኘት ያስችላቸዋል።

ቻይና እና ሩሲያ እንደታንዛኒያ፣ ሞዛንቢክ፣ አንጎላ፣ ጋና እና ደቡብ አፍሪቃ ያሉ ሀገሮች ከቀኝ ግዛት ለመላቀቅ ያደረጉትን ትግል ወቅት አንስቶ እስከ ቀዝቃዛው ጦርነት በታንዛኒያ በኤርትራ በሱማሊያ በኢትዮጵያ ያሉ የነጻነት እንቅስቃሴዎች ከመደገፍ ጀምሮ በአፍሪቃ ጉልህ ድርሻ አላቸው።

እንደ ራሺያ እና ሩሲያ ሁሉ ሳውዲ አረቢያ፣ እስራኤል፣ ቱርክ፣ ጃፓን እና ሕንድም በከፍተኛ ደረጃ መዋዕለ ነዋዮችውን በአፍሪቃ ኢኮኖሚ ላይ እያፈሰሱ ነው።

በተለይ በምሥራቅ አፍሪቃ ባሉ ጅቡቲ፣ ሱዳን፣ ደቡብ ሱዳን፣ ሱማሊያ እና ኢትዮጵያ ኬኒያ በዓለም ኃያላን መንግሥታት የሚካሄደው ድብቅ የኢኮኖሚ ጦርነት ውስጥ የአሜሪካ ወይንም የቻይና ዋና አጋር የኃይል መነሻ ለመሆን የሀገራቱ መንግሥታት ሽኩቻ የጀመሩ ይመለሳል።

አቡዳቢ፣ ቱርክ፣ የአረብ ኤምሬትስ እና ኢራን ሳይቀሩ በምሥራቅ አፍሪቃ በውትድርናም ሆነ በኢንቨስትመንት ረገድ የትኩረት አቅጣጫቸውን ማድረጋቸው ለምንድን ነው? በርግጥ ቀጣዩ ድብቅ ጦርነት ለምሥራቅ አፍሪቃ ምን ይዞ ይመጣ ይሆን የሚለው ጥያቂ፣ ጊዜው ሲደርስ የምናየው ይሆናል ።

ቀጣዩን በገጽ 24 ይመልከቱ



ደረጀ ይመር

# "መቃብሬ እንደ ሙሴ አይታወቅም"

## የበዓሉ ግርማ ሕይወት እና ሥራዎቹ

ቀይ ብስል ብላቴና ለሀገሩ ባዕድ በሆነ ቋንቋ በሚያሳዝን ቅላጼ ተማጽኖውን ያቀርባል::ሥፍራው የሸገር የንግድ መናገሻ፣በሰው ጫካ ከተወረረው መርካቶ ከአንድ ህንዳዊ ባለጠጋ ሱቅ ደጃፍ ላይ ነበር::ምስኪኑ ብላቴና በቀዬው ናፍቆት እየተንገበገበ፣ የልጅ ገጽታውን ጣምራ ጣምራ ሆነው በሚወርዱ እምባዎቹ ያወረዛል::ይህ እንደአልባሌ ፊት የተነሳው ጨቅላ የወደፊቱ ታላቅ የሥነጽሑፍ ሰው በዓሉ ግርማ ነበር::ነገሩ የተፈጸመው ደግሞ ገና ጉተናው ሳይጠና ትውልድ ቀዬውን ሱጴን ለቆ በነጋዴዎች አማካኝነት ወላጅ አባቱን ለማግኘት መርካቶ በመጣበት ጊዜ ነበር::

ደራሲ እንዳለጌታ ከበደ የበዓሉ ግርማ ሕይወቱና እና ሥራዎቹን በ440 የድርሳን ሞገስ አላብሶ በመጠን ዳጎስ ያለ(Fat book) በ120 ብር የዋጋ ተመን ካቀረበ ሰንበትበት ብሏል::ደራሲው ይህንን ዳጎስ ያለ መጽሐፍ ለማሰናዳት ብዙ እንደደከመ ዋቢ ካደረጋቸው ተጨባጭ ማስረጃዎች መረዳት ይቻላል::በየሰርጡ የተሸሸጉትን እውነታዎች ይፋ ለማደረግ ያለፈበት መንገድ ከደራሲነት ይልቅ የምርመራ ጋዜጠኝነት የገነነበት ነበር።

እውነታው ሲገለጥ

ደራሲው ቅኝቱን የሚያሚሸው ብዥታን በማጥራት ነው:: ከዚህ ቀደም በበዓሉ ግርማ ላይ በተሳሳተ መንገድ ተይዞ የነበረውን እምነት ከሥሩ ይመነግላል::በአብዛኛው በጉምቱ ልሂቃኖቻችን ላይ የሚነሳው ሐሜት፣ያለፉባቸውን የሕይወት ውጣውረዶች በሰነድ ከትበው በማኖር ቀሪው ትውልድ እንዲማርበት አያደርጉም:: በአብዛኛው በአፈ-ታሪክ ግራ ቀኝ ከሚላጉ ሐሜቶች ነው ስለታዋቂ ግለሰቦቻችን የምንፈልገውን መረጃ የምንቃርመው::መናኛ ቁምነገሮች እንደትልቅ ምስጢር ተቆጥረው እንደዋዛ ይታበላሉ::በአጠቃላይ ድብቅነት ባህላዊ ቀኖናን ያቆመ ካስማ ነው ቢባል እውነታውን መዳጥ አይሆንም::

ከዚህ ቀደም በታዋቂ ግለሰቦች የሕይወት ታሪክን በተመለከተ እርስ በርሱ የተመታታ እና የጠራ ግንዛቤ ሳይያዝበት እየተዳፈነ ሲቀር አስተውለናል::ለአብነት ያህል የጥላሁን ገሠሠን የሕይወት ታሪክን በተመለከተ የተከተቡ ድርሳናትን ዋቢ ማድረግ እንችላለን::የበዓሉ ግርማም ቤተሰባዊ ታሪክ ለአብዛኛው ሕዝብ ግራ ሆኖ ቆይቷል::

የበዓሉ ግርማ አሳዳጊ አቶ ግርማ ወልዴ በዓሉን ከአብራካቸው ክፋያዎች ጋር በእኩል ዐይን ተንከባክበው ለማሳደግ የወሰኑበትን ምክንያት ከእዚህ ቀደም በየትኛውም የሕትመት ውጤት ወይም ሚዲያ ሰምተነው አናውቅም::ይህንን የጓዳ ምስጢር የበዓሉ አብሮ አደግ እህት ጽጌ ግርማ እንዲህ ትናዘዛለች፣




የበዓሉ አመጣጥ እንደዚህ ነው:: በቃ አሁን እንደነገርኩህ::እናቱ፣ከሕንድ በመውለዷ ተጽእኖ የተደረገባትና፣ልጁም ተገልሎ ያደገ ይመስለኛል።ስለዚህ በነጋዴዎች በኩል፣የአባቱን አድራሻ ሰጠቻቸውና ይዘውት መጡ::.....አስብ ስንት ጊዜ እንዳአለቀሰ::...መቼም ከሱጴ ሲወጣ እናቱን በእዬዬ ነው የሚሰናበታት::እዚህ ሲመጣ ደግሞ ተቀባይ አጣ:: ደግነቱ አባቴ ተቀበለው:: እንደዚህ ነው አስተዳደጉ....በዓሉ ከእኛ ጋር ሲኖር፣አባቱ ጂምናዳስ ሊያየው አይፍልግም ነበር::.................ይሄ በየጋዜጣው በየሬዲዮኑ የሚነገረው ውሸት ነው::

አቶ ግርማ ወልዴ ከበዓሉ ጋር ምንም ዓይነት የሥጋ ዝምድና የላቸውም::ከኢሉአባቦራ ሱጴ ከእናቱ እቅፍ ተነጥሎ በውል ወደ ማያወቀው መሀል ሀገር እንደመጣ አባቱ ጂምናዲስ ፊት ነሳው፣ይህንን የተመለከቱት የጅምናዲስ ሠራተኛ የነበሩት አቶ ግርማ ወልዴ ሰበኣዊነት ግድ ብሏቸው አፋፍሰው ወደ እልፍኛቸው በመክተት እቅፍ ድግፍ አድርገው ለወግ ማዓረግ ሊያበቁት ችለዋል::ይሁን እንጂ በዓሉ በአቶ ግርማ ወልዴ ስም ለመጠራት የፈቀደው የዩኒቨርስቲ የመጀመሪያ ዓመት ተማሪ ላይ ነው::ጸሓፊው በዳሰሳ ጥናቱ እንደደረሰበት ከሆነ በዓሉ የአያቱን ስም በአቶ ግርማ አባት ወልዴ ፋንታ ኤጀርሶ ብሎ ነው የቀየረው::ለምን ይህን እንዳደረገ ግምቱን እንደሚከተለው ያኖራል፣

እንደእኔ ግምት፣ የሱጴን ምድር የረገጠና አንድ ሁለት ሽማግሌዎችን ያነጋገረ ሰው፣ኤጀርሶ የሚለውን ስም መስማቱ አይቀሬ ነውና፣በዓሉ ስሙን እትብቱ ከተቀበረበት መንደር ጋር ለማስተሳሰር ብሎ የዘየደው መላ ይመስለኛል::ለምን ቢባል፣ያለ ኤጀርሶ ሱጴ ቦሮ የለችም::እንደሚታወቀው ሱጴን የቆረቆረት ነገዎ ቦሮ ነው፤የነገዎ ልጅ ደግሞ ኤጀርሶ፣የኤጀርሶ ልጆችም አያናና ኃይሌ ናቸው::እነዚህን ስሞች ሱጴ የተወለደ እና የኖረ ሁሉ ያውቃቸኂል::

ሽቅርቅሩ ጋዜጠኛ

በዓሉ ከጋዜጠኝነት ሙያ ጋር በፍቅር የወደቀው ገና ኮሌጅ እንደበጠሰ ነበር:: በኮሌጅ የተማሪነት ጊዜ ጠንቅቀው የሚያውቁት በሕይወት ያሉ ባልንጀሮቹ በአንድ ድምጽ እንደሚመሰክሩለት ከሆነ ለአለባበሱ ጠንቃቃ፣አርቆ አስተዋይ እና ለአመነበት ነገር እስከ መጨረሻው የሚፋለም ደፋር ወጣት ነበር::ይህ ደፋር ስብዕናው በጋዜጠኝነት ሙያ በተሠማራባቸው ጊዜያት ላይም አልከሰመም::

በዓሉ ከተራ ጋዜጠኝነት እስከ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ሥራ አስኪያጅነት ባገለገለባቸው በንጉሡ የሥልጣን ዘመን ብዙ እንግልት ደርሶበታል::አንደአንዴም በግሳጼ እየታለፈ ባስ ሲልም ቆንጠጥ ያለ እርምጃ እየተወሰደበት በሆድ ይፍጀው እንጉርጉሮ ያዘገመበት የሕይወት አጋጣሚ የተበራከተ ነው::የመጀመሪያ የጥበብ ሥራውን ከአድማስ ባሻገር የጻፈው ከሥራ ገበታው ታግዶ ከመንግሥት ቀለብ እየተሠፈረለት ነበር::

በቁሳሩ የአገዛዝ ወቅት የመነን መጽሔት አዘጋጅ ሆኖ ሳለ በወቅቱ እንደድፍረት የሚቆጠር ጀብዶ በመሥራት በቤተመንግሥት ሰዎች ዘንድ የመወያያ ርዕስ ሆነ::የመነን መጽሔት የፊት ልባስ በቁሳሩ መንበር ዙሪያ የተሰባሰቡት የንጉሣዊያን ቤተሰብ ብቻ ነበር የሚፈራረቁባት:: በዓሉ ግን በአንድ የሕትመት አጋጣሚ የመጽሔቱን ልባስ በአንዲት በፊልም ተዋናይት ገጽታ ሞላው::ይህም ▶

ድርጊት በቤተመንግሥት ሰዎች ዘንድ እሳት አስነሳ::እናም በአስቸኳይ ከንጉሡ ፊት ቀርቦ ድርጊቱን ለምን እንደፈጸመ ሲጠየቅ እንዲህ ብሎ መለሰ፡

የመጽሔቱ አንዱ ዓላማ ሙያተኞችን ማበራታት ነው፣ያቺ በመነን የፊት ልባስ ላይ የወጣችው ሴት ደግሞ፣በኢትዮጲያ የመጀመሪያዋ የፊልም ተዋናይ ናት፣ድጋፍ ያስፈልጋታል ብዬ በማመኔ ነው::ብሎ የንጉሡን ቁጣ ለማዘለዝብ ሞክራል

ስለተዋናይቷ ማንነት ግን መጽሐፉ የገለጸው ነገር የለም::ጸሓፊው ይህንን እና መሰል ከጋዜጠኝነት ሙያ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ግርምትን የሚያጭሩ ገጠመኞችን በብዕሩ ለመከተብ የኢትዮጲያ ፕሬስ ድርጅት በራፍን ደጋግሞ ለመቆርቆር እንደተገደደ ይናገራል::::

በዓሉ ከሥነጽሑፍ ችሎታው ባሻገር ሴቶች በፍቅር ጠብ እርግፍ የሚሉለት አመላይ ወንዳወንድ ነበር::የዛን ዘመን ኮከብ አቀንቃኝ ብዙነሽ በቀለ በፍቅር ከወደቁት መካከል ትጠቀሳለች::ለእዚህም እማኝነት ሆኖ የቀረበው በ1950ዎቹ የራዲዮ ቴክኒሻን ሆኖ ይሠራ የነበረው ኪሮስ ወልደሚካኤል የተባለው ግለሰብ ነው::

አስብ፣በዚያ ዘመን፣አንድ ታዋቂ ድምጻዊ ለአንድ ወጣት፣ገና ስሙ ላልታወቀ ቆንጆ ጋዜጠኛ፣በስልክ ዘፈኖቿን ስታንቆረቁለት… እና ዜናውን የሚያነብበት ሰዐት ከደረሰ እኔን በምልክት ጠርቶ የስልኩን እጀታ ይሰጠኛል:: “አንብቤ እስክመጣ አዳምጥ፣አዳምጥልኝ” ነው ነገሩ::ሊያነብ ይሄዳል::ዜናውን አንብቦ “ጃንሆይ ወደ ቁልቢ ገብርዓል ሄደው በዓሉን በሰላም አክብረው ተመለሱ”፣ “በልዕልት እገሊት ቀብር ላይ ተገኙ”……ምናምን ብሎ አጠር ፈጠን አድርጎ አንብቦ ሲጨርስ፣ይመጣና ስልኩን ተቀብሎኝ የእሷን ዘፈን ማዳመጡን ይቀጥላል::

የበዓሉ የጋዜጠኝነት ሙያ ከሥርዓት ለውጥ በኋላ ጠንከር ባለ የፈተና ማዕበል እየተላጋ ቀጠለ:: ከበላይ ሹሞቹ የሚሰጠውን ቀጭን ትዕዛዝ ያለምንም ማቅማማት እየተቀበሉ ማዝገም ዕጣ ፈንታው የሆነ መሰለ::ይህንን የሙያ ጭቆና ለማስተንፈስ ዙሪያ ገባውን አማትሮ ከአእምሮ ብቅ ያለው ለጥበብ የተሰጠው መክሊቱ ብቻ ነበር:: በማይፈናፍን ሥራ ውስጥ ሆኖ ስድስት መጽሐፎችን ለሕትምት ማብቃት ችሏል::

ኦሮማይ

በዓሉ በኦሮማይ የጥበብ ሥራው ደርግ ያሰመረውን ቀይ መስመር አለፈ::ጥቁር ነብር እያለ የሚያሞካቸው የሀገሪቱ ርዕስ ብሔር አንጀት እንኳን ሊራራለት አልቻለም::መጽሓፉ ለሕትመት በበቃበት ሳምንታት ውስጥ ከሥራው ገበታ የመታገዱ ነገር ዕውን ሆነ:: ነገሩን ያከፋው ደግሞ በበዓሉ ላይ ጥርስ የሚነክሱት የደርግ ቱባ ሹማምነቶች ከቀን ወደ ቀን ቁጥራቸው እየተበራከተ መሄዱ ነበር::

ፀሐፊው ከገነት አየለ የኮ/ሌ መንግሥቱ ኃይለማሪያም ትዝታዎች መጽሐፍ ደራሲ ጋር ቅርርብ ቢኖረውም ስለበዓሉ የአሟሟት ሁኔታ ከእዚህ ቀደም በሰሚ ሰሚ ከሚነገረው የኮሪደር ወሬ የተለየ ነገር ለመተንፈስ አለደፈረችልትም::ከእዚህ ይልቅ ለሶስተኛ ወገን ሹክ ያለችው ጠቃሚ መረጃ እጁ እንደገባ በሚከተለው መልኩ ይልጽልናል

“አየህ ፈርታሃለች ማለት ነው፤ወይም የተጠረጠረችው ነገር አለ:: እንደዛ ባይሆን ኖሮ ጄነራል ተስፋዬ ወይም የተጠራጠረችው ነገር አለ:: እንደዛ ባይሆን ኖሮ ጄነራል ተስፋዬ ገብረኪዳን እነ መንግሥቱ ኃይለማሪያም ጋ ቀርቦ፣ “በዓሉ እርስዎን ስላቆለጳጰሰ ነው ወይ በጦር መኮንኖች ላይ የሚዘባበት ልብወለድ ሲጽፍ በቸልታ ያለፉት? በኦሮማይ ሰበብ የጦሩ መንፈስ ታውኳል::ልቡ ተከፍሏል::ማጉተምተም ይዟል::እንዴት ከሥራ በማሰናበት ብቻ ይለቀቃል? በዚህም የተነሳ፣ብዙ የጦር መኮንን አቂሞበታል” ብሎ አሳብቋል::በእዚህም ምክነያት ነው በዓሉ የተያዘው፤የተጨከነከበትም::ይህንን፣እራሳቸው ጓድ መንግሥቱ ነግረውኛል ብላ ነግራኛለች፤ለአንተም ልትነግርህ ይገባ ነበር::”

በእዚህም ትዕዛዝ አማካኝነት ፀሐፊው በሰበሰበሰው መረጃ መሠረት በዓሉ ታስሮ የነበረበት ሞት እንደቅንጦት በሚናፈቅበት ቤርሙዳ ትሪያንግል ውስጥ ነው::ነገር ግን ተገድሎ የተቀበረበት ኹነኛ ሥፍራ በማመላከቱ በኩልም አሁንም ጠብ ያለ ነገር ማግኘት አልተቻለም::

በዓሉ ግርማ “ደራሲው” በሚለው የልቦለድ ሥራው “ሲራክ” በሚባል መሪ ገጽ ባህሪ አማካኝነት “እንደ አብርሃም ቤት የለኝም፣እንደ ሙሴ መቃብሬ ላይታወቅ” ብሎ የነብይ ቃል ተናግሮ ነበር::እርግጥ ነው ከበዓሉ መጠሪያ ጋር ተሸቀዳድሞ ወደ አእምሮ ብቅ የሚለው ነገር የአገዳደሉ ፍንጭ አልባነት እና የመቃብሩ ቦታ አለመታወቁ ነው::ምንእልባት ይህ መጽሓፍ የበዓሉን ገዳይ ዱካ አንፍንፎ በማግኘቱ የተነሳ አንድ የቤት ሥራ ለጊዜው ያቃለለ ይመስላል::

በዓሉ በኦሮማይ የጥበብ ሥራው ደርግ ያሰመረውን ቀይ መስመር አለፈ።።ጥቁር ነብር እያለ የሚያሞካቸው የሀገሪቱ ርዕስ ብሔር አንጀት እንኳን ሊራራለት አልቻለም።።መጽሓፉ ለሕትመት በበቃበት ሳምንታት ውስጥ ከሥራው ገበታ የመታገዱ ነገር ዕውን ሆነ።። ነገሩን ያከፋው ደግሞ በበዓሉ ላይ ጥርስ የሚነክሱት የደርግ ቱባ ሹማምነቶች ከቀን ወደ ቀን ቁጥራቸው እየተበራከተ መሄዱ ነበር

ስሙ በመጽሐፉ ላይ እንዲጠቀስ ያልፈለገ ግለሰብ ከገዳዩ ሚስት በቀጥታ ቀዳሁት ያለውን አዲስ ነገር ለፀሐፊው በሚከተለው መልኩ ያጫውተዋል፣

ማታ ነው ::2፡30 ኮሎኔል አርጋው እሸቴ የሳሎኑን በር ከፍቶ ገባ::ሳሎን ተቀምጣ የነበረች ሚስቱ በፊቱ ላይ ያልተለመደ ደስተኝነት አየችበት::ከዚያም፣የጓድ መንግሥቱ ኃይለማሪም ዓይነት የሚመስላትን ድፍረት ለብሶ፣የጓድ መንግሥቱ ኃይለማሪያምን ዓይነት የሚመስላትን እብደት ይዞ፣በጥቁረትም፣በእጥረትም የእሳቸውን ዓይነት ገጽታ ወርሶ፣በድል አድራጊነት ድምጽ አንዳች አስደንጋጭ ነገር ነገራት::”ያንን! በዓሉ ግርማ የተባለውን ሰው ጨርሼ መጣሁ!” አለ

ይህ በደራሲው አውጫጪኝ የተፈለቀቀው ምስጢር ከሁሉም በላቀ ደረጃ ሚዛን እንደሚደፋ እሙን ነው::የዚህን ድብቅ እውነታ ዱካ አነፍንፎ ለማግኘት ብዙዎች ላይ ታች ብለዋል ::አንባቢ እዚህ አንቀጽ ጋር ሲደርስ የታሪኩ የጡዘት ማማን መንካቱ አይቀርም::በርግጥ የታላቁ ደራሲ በዓሉ ግርማ ፍጻሜን በምናብ ሲጠይቅ ለኖረ ሰው መጽሓፉ ኹነኛ ምላሽ ይሆነዋል ቢባል ማጋነን አይሆንም::

እንደ መውጪያ

በዓሉ ግርማ በኢትዮጵያ የሥነጽሑፍ ታሪክ ውስጥ እንደ ጉልላት ዘለግ ብሎ ከዐይን የሚገቡ ዘመን ተሻጋሪ ድንቅ የጥበብ ሥራዎች ባለቤት እንደሆነ ይታወቃል::የደራሲው ሥራዎች በፓለቲካ፣በፍልስፍና እና በታሪክ አሻራዎች የወረዙ፣ በውስጣቸው ያረገዙት ጥልቅ ቁምነገሮች የአስተሳስብ አድማስን የሚፈትኑ፣በቀላል አማርኛ እና በቀልድ እየተዋዙ የምናብ ጠኔን የሚያጠረቁ ናቸው::በዓሉ ለቀልድ እጅ እንደማይጥረው ስለእርሱ የሚወሱ ድርሳናት ይገልጻሉ:: በማስታወቂያ ሚኒስቴር ውስጥ ተቀጥሮ እየሠራ ሳለ ስሜቱን የሚያጎሹትን የሥራ ባልደረባዎቹን ለመገሰጽ የተጠቀመበት አገላለጽ የሚዘነጋ አይደለም:: “የእነዚህን ሰዎች እውቀት ለማወቅ ቅጽበት ብቻ ነው የሚበቃህ፣ተንኮላቸውን ለመረዳ ግን የማቱሳላ ዕድሜ አይበቃህም” ብሎ ነበር:: የደራሲው ድፍረት በዘመኑ መሬት አንቀጥቅጥ የነበሩት፣ሳር ቅጠሉ ከሚያረግድላቸው መለዮ ለባሽ ጋር ፊት ለፊት እንዳላተመው ከመጽሐፉ እንገነዘባለን ::መራራውን ቀይ ወሰን እንዳለፈ የሚያመላክተው ንቃተ ኅሊናው፣ ቀላል እና ቀልድ አዋቂ ስብእናው የጋረደው ይመስላል::ከመለዮ ለባሽ ጋር አጉል ልፊያ ማብዛቱ ፍጽሜው ተገማች ባልሆነ መንገድ ምስጢራዊ በሆነ የአገዳደል ስልት እንደአልባሌ አፈር ለመልበስ ችሏል:: በዓሉ ሲታሰብ የአገዳደሉ ሁኔታ እንቆቅልሽ እንደሆነ ከዚህ ቀደም ለሕትመት ብርሃን በበቁ ድርሳናት፣ጋዜጦች እና ሌሎች የሕትመት ውጤቶች ስንረዳ ነበር::

የእንዳለጌታ የጥናት ውጤት ከዚህ በፊት በጭምጭታ ደረጃ በደራሲው ታሪክ ዙሪያ ሲሰነዘር የነበረውን የኮሪደር ወሬ በተጨባጭ መረጃ እርቃን በማስቀረት የአንባቢያንን ንቃት በማብርታቱ ረገድ የተዋጣለት ነው::ለዚህም ለደራሲው ገድል ባርኔጣ ከፍ ቢልለት የሚበዛበት አይሆንም::



ተስፋ (ኢትዮጵያ) አልታሰብ

# ቦሎ የሚያስፈልጋቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች

በአገራችን ቦሎ የሚደረገው ለመኪና ብቻ ነው:: ቦሎ ሲደረግ አራቱም እግር ፍሬን በትክክል መያዝ አለመያዝ፣ የጎማ ልኬት፤ በዐይን ከሚታዩት የመብራት ክፍል፣የዝናብ መጥረጊያ፣ የአደጋ ጊዜ መብራት፤ ፍሬን (የእጅና የእግር ፍሬን) ፍሬቻ የፊትና የኋላ መብራቶች፣የስሌዳ መብራት የጎን መመልከቻ መስታወቶች (ስፖኪዮ)፣ የግንባር መመልከቻ መስታወቶች፣ መሥራት ያለመሥራቱ ታይቶ፣ እንዲሁም የተሽከርካሪው ውስጣዊ አካል፣ ለተጠቃሚው ምቹ መሆኑን፤ የተሽከርካሪው ሞተር ያለበት ደረጃ፣ ድምጽም ጭምር የካርቦን ልቀቱም እንደሚመረመር በሕጉ ይታወቃል:: ማንኛውም መኪና የቴክኒክ ብቃት ሳይኖረው ቦሎ መለጠፍ አይችልም:: በተመሳሳይ የሀገራችን የፖለቲካ ፓርቲዎች እንደ መኪኖቹ በየዓመቱ ቦሎ ቢያደርጉ ፓርቲዎቹ በየዓመቱ የአዲስ የፖለቲካ አስተሳሰብና የአዲስ ትውልድ ዘመነኛ አመለካካት ሊያመጡ ይችላሉ የሚል እሳቤ አለ::

በ1969 ዓ.ም የተመሠረቱ አንዳንድ የሀገራችን ፖለቲካ ፓርቲዎች እስካሁን ድረስ ከስም ባለፈ አንድም ለሕዝብ የሚጠቅም ተግባር ሊያሳኩ ያልቻሉት ያላቸውን የፖለቲካ ብቃትና አስተሳሰብ በዓመታዊ ቦሎ ደረጃቸው ስለማያስመረመሩ ነው:: ያን አለማድረጋቸው ደግሞ ዛሬ ድረስ በፖለቲካ አስተሳሰባቸው ቀድሞ በነበሩበት ዛሬም እዛው ባለህበት ሂድ እየረገጡ ናቸው:: በ1969 ዓ.ም ተመሥርቶ ዛሬም በዚያው አስተሳሰብ ላይ የቆመ ፓርቲ እንደ ፓርቲ ስያሜ አዝሎ እንዲቀጥል መፍቀድ አሳፋሪ ተግባር ነው:: ምክንያቱም ደግሞ የዘመኑን አዲስ አስተሳሰብ ያልዋጀ፤አዲሱን ትውልድ ዘመነኛ አስተሳሰብ ያላወቀ ቆሞ ቀር ፓርቲ እንደ ፓርቲ በአገራችን ሊንቀሳቀስ ሊፈቀድለት፤ ሕዝብም ፓርቲ ነው ብሎ ሊቀበለው አይገባም ነበር:: ዛሬ ከፖለቲካ ፓርቲዎቹ ራእይና አስተሳሰብ በላይ ሕዝቡ በአስተሳሰብ ፖለቲካ ፓርቲዎቹን ቀድሞ ጥሏቸው ሄዷል:: ይህ የሚያሳየን የፖለቲካ ፓርቲዎቹ የፖለቲካ ብቃት ማረጋገጫ ዓመታዊ ቦሎ (ዘመኑ የሚፈልገው) አስተሳሰብ ላይ መገኘት አለመገኘታቸውን በዓመታዊ ምርመራ ላይ በምርጫ ቦርድ ስለማይፈተሹ ነው:: ምርጫ ቦርድ በየዓመቱ ፖለቲካ ፓርቲዎችን ቦሎ ቢያስደርግ የሀገራችን የፖለቲካ ፓርቲዎች ቁጥር ከአስር አይበልጡም ነበር እንላለን:: የፖለቲካ ፓርቲዎች መብዛት ዋነኛ ተጠያቂው ቦሎ ሳያስደርግ ፓርቲዎችን የሚመዘግበው ምርጫ ቦርድ ሊሆን ይችላል::

ዛሬ በሀገራችን በምርጫ ቦርድ የተመዘገቡ ሕጋዊ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ቁጥር ወደ 72-80 ድረስ የሚጠጋ እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ:: የሁሉም በሕይወት መኖራቸውና ድምፃቸው የምንሰማው በምርጫ ወቅት ብቻ ነው:: በአገሪቱ ያሉ አንዳንድ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በውስጣዊ ልዩነትና በግል ግጭት ሲወዛገቡ መታየት ባሕሪያቸው ነው፣ ምርጫ በመጣ ቁጥር ሁሌ የምንሰማው የእነርሱ ውዝግብ ነው:: ፓርቲዎች የሚታገሉት እውነት ለሕዝብ ከሆነ እርስ በርሳቸው ምን አናቆራቸው? በመካከላቸው መናቆር የሚመጣው የጥቅማ ጥቅም ግጭት እንደሆነ ሕዝብ በደንብ ይገባዋል:: ምክንያቱ ደግሞ ፖለቲካ ፓርቲዎቹ እራሳቸውን ለሕዝብ ጥቅም አሳልፈው ለመስጠት (ለመታገል) የቆረጡ ከሆነ ግላዊ ፀብ በፓርቲ ውስጥ ፈፅሞ ሊመጣ አይችልም:: እንዲህ የሚሆኑት ለሕዝብ ጥቅም ከመታገል ይልቅ በግል ጥቅማ ጥቅም ስለሚጠመዱ ሊሆን ይችላል:: ወይም አንዱ ፓርቲ ሌላውን ፓርቲ ለማፍረስ በጥቅም ተደልሎም የሰረገ ግለሰብ የሚፈጥረው ሊሆን ይችላል:: እንዲህ አይነት ፖለቲካ ፓርቲዎች አላማና ራእይ እንዲሁም ድብቅ እንቅስቃሴአቸው ምን እንደሚመስል ለምን አላማ ፓርቲውን እንደፈጠሩ ምርጫ ቦርድ ዓመታዊ ቦሎ እንዲያደርጉ ስለማያዝ ነው::

ቦሎ ማድረግ ማለት እራስን በሚገባ ማወቅና ወቅትና ጊዜው እንዲሁም ዓለማዊ ሁኔታው የሚፈቅደውን ፖለቲካዊ በብቃትና የአስተሳሰብ ጥራት አሟልቶ መገኘት ማለት ነው:: መኪኖች በየዓመቱ ቦሎ የሚደረጉት በመጀመሪያ ደረጃ መኪኖችን የሚይዝ ግለሰብ መኪናውን ቦሎ ባያደርግ ለራሱና ለቤተሰቡ አላስፈላጊ አደጋ ውስጥ እንዳያስገባ ሲሆን፤ እንደ ሀገር ደግሞ ቦሎ ያልተደረገለት ተሽከርካሪ በሌሎች ንፁሀን ዜጎች ላይ የማስፈልግ አደጋ እንዳያደርስ ለመከላከልና ለመቆጣጠር ነው::

የኛዎቹ የፖለቲካ ፓርቲዎቹ ዓመታዊ ቦሎ ሳይለጥፉ ለአመታት እንደ ፖለቲካ ፓርቲ ሲንቀሳቀሱ እናያለን:: አንዳንድ የፖለቲካ ፓርቲዎች ዓመታዊ ቦሎ ባለማድረጋቸው ምክንያት የፓርቲ ዲሲፕሊን የሌላቸው ሲሆኑ ፤ለመርህ የማይገዙና የአባሎቻቸው ማንነት የማያውቁ፤ አባሎቻቸውንና ደጋፊዎቻቸውን ስርአት ማስያዝ የማይችሉ፤ መሪዎቹ እርስ በርሳቸው በቅንነት የማይነጋገሩ፤ ሁሌ በጠላትነት የሚፈላለጉ፤ ዘወትር እርስ በርሳቸው በነገር የሚነቋቆሩ፤ አንዳንዶች ደግሞ ፖለቲካ ፓርቲያቸውን እንደ ራሳቸው የግል ቤት ሲፈለጉ የሚያፈርሱ፤ሲፈልጉ የሚጠግኑ፤ ሲጣሉ ማህተም የሚደብቁ፤ከሕዝብ የተሰበሰበ ብር የሚዘርፉ፤የቢሮ ቁልፍ የሚቀማሙ፤የሚወነጃጀሉና የሚካሰሱ መሪዎች ናቸው ያሉን፤ የፖለቲካ ፓርቲዎቹ በፕሮግራማቸው፤ ትግላችን ለሕዝብ ነው ይሉናል:: በእውነታ የምናየው ግን እርስ በርሳቸው በጥቅማ ጥቅም ትግል ሲያደርጉ ነው:: ታድያ በእነዚህ ዓመታዊ ቦሎ ባለጠፉ ፖለቲካ ፓርቲዎችና መሪዎች እንዴት እንመራ? ስለ እውነት ለሕዝብ እየታገሉ ስለመሆናቸውን እንዴትስ እንመናቸው? የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች ሕዝብን ነፃ ለማውጣት፤ዴሞክራሲ ለማስፋት፤ሕዝብን ከድህነት ለማውጣት ከመነሳታቸው በፊት፤ መጀመሪያ እራሳቸው ዓመታዊ ቦሎ በማድረግ ከደካማ አስተሳሰባቸውና አመለካከታቸው ነፃ ማውጣት ይጠበቅባቸዋል::

በመሰረተ ሐሳብ ደረጃ የፖለቲካ ፓርቲዎች መኖር ለአንድ ሀገር የዲሞክራቲክ ሥርዓት አንድ መገለጫ ነው:: ይህ የሚሆነው ግን ፖለቲካ ፓርቲዎቹ ዓመታዊ ቦሎ በማድረግ ለሕዝብ ሊታገሉ እንደሆነ ለመረዳት የብቃት ማረጋገጫ ሲያልፉ ሊሆን ይገባል:: ፖለቲካ ፓርቲዎቹ ዓመታዊ ቦሎ ካለጠፉ ሁልጊዜ በፈለጉበት ፤ባመኑበትና የአመለካከት ለውጥ እናመጣለን ባሉት ቅርፅና መልክ ሊጓዙ አይችሉም:: በፓርቲዎች ውስጥ እንከኖች ሲያጋጥሙ ፓርቲን እንደ ግል ንብረት ለማፍረስ ከመሮጥ፤ በቅድምያ የማረሚያ እርምጃዎችን ለመውሰድ የሚያስችሉ ግልፅ ውይይቶችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ማድረግ መቻል፤ ለፖለቲካ ፓርቲው የብቃት ማረጋገጫ አንደኛው መንገድ ሊሆን ይገባል::

የፖለቲካ ፓርቲዎቹ ዓመታዊ ቦሎ ካለጠፉ፤ግልፅ የሆነ ፖሊሲና ስትራተጂ ስለማይኖራቸው ጥራት ያላቸውና ተጠያቂነትና ሀላፊነት የሚሰማቸው አባላትን እንዴት ማፍራት ይችላሉ? በዚህም በዚያም የሚያፈሯቸው አባላትስ ለነገይቱ ኢትዮጵያ ተተኪ የፖለቲካ ፓርቲ መሪ መሆን የሚችሉ ናቸው ወይ? አብዛኛዎቹ ተፎካካሪ ፓርቲዎች አባሎቻቸውን የሚመለምሉት በጠራ የምልመላ ፖሊሲና ስትራተጂ ሳይሆን በአደገኛ የፕሮፓጋንዳ ስሌት በመጠቀም ነው:: እንዳየነውና እንደሰማነው የፖለቲካ ፓርቲዎቹ ዓመታዊ ቦሎ ካለጠፉ በተቃዋሚው ጎራ የአባላት ማፍሪያ ዘዴ ጥቅማ ጥቅም፣ ትውውቅና ዝምድና ወዘተ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል:: ይህ እስካሁን ድረስ የተከተሉት መንገድ ደግሞ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ጠንካራ አባላት እንዳይመለምሉ አድርጓቸዋል:: የዚህ አሰራር ድምር ውጤት ያስከተለው ችግር ደግሞ በተፎካካሪ ፓርቲዎች ካምፕ ተስማምቶና ተከባብሮ በቅንነትና በታማኝነት ለሕዝብ መስራት አለመቻል ባህል ሆኖ ለ40 እና 50 ዓመታት ዘልቋል ::

የፖለቲካ ፓርቲዎቹ እርስ በርሳቸው ለውህደትና የፖለቲካ ፓርቲዎች ቁጥር ለመቀነስ የሚቀረፁት አዲስ መንገድ ከዚህ ቀደም የተፈጠሩትን ችግሮች፣ የተከሰቱትን አላስፈላጊ መለያየቶች፣አለመግባባቶችና እንዲሁም ፓርቲን ለማፍረስ የሚደረጉ ሥርዓት የጣሱ አካሄዶችን ለማረምና ለማስተካከል በቅድምያ የታማኝነት ዓመታዊ ቦሎ ሊለጥፉ ይገባል::

በፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል የታማኝነት ዓመታዊ ቦሎ ካለጠፉ የሚደረገው የውህደት ውይይት፣ ለጊዜያዊ የፖለቲካ ፍላጎትና ፍጆታ ወይም የግጭት ማብረጃ ብቻ ሊውል ▶

ይችል እንደሆን እንጂ በመካከላቸው እውነተኛ የውህደት ለውጥ ማምጣት አይቻልም:: ቁርጠኝነቱ ካለ በፓርቲዎች መካከል የሚፈጠሩ ጥቃቅን ልዩነቶችን አጥብቦ ወደ ውህደት መሄድ አስተዋይነት ነው:: ምክንያቱም ለመራጩም የፖለቲካ ፓርቲዎች ባነሱ ቁጥር መራጭ የሚመርጠውን ፓርቲ በደንብ አስተውሎ ሊለይ ይችላል:: ሰማንያ ተቃዋሚ በአንድ አገር ለሕዝብም ለመንግሥትም የግጭት መነሻ ምንጭ ሊሆንም ይችላል:: ፖለቲካ ፓርቲዎች በሁሉም ላይ መግባባት ባይቻሉም፣ በተመረጡ አጀንዳዎች ላይ መግባባት ላይ ለመድረስ ይቻላል:: ይህ ደግሞ በሰጥቶ መቀበል መርህ መቀራረብና በውህደት ውስጥ ሆኖ ልዩነቶችን ማስታረቅ አንድ አማራጭ መንገድ ነው:: በ1997 ዓ.ም ኢሕአዴግን ፈተና ውስጥ እንዲገባ እና በምርጫ እንዲደናገጥ ያደረገው የአራት ፓርቲዎች ስብስቡ ቅንጅት ነበር:: አራቱ ፓርቲዎች በተናጠል ቢቀርቡ የማሸነፍ እድላቸው የጠበበ ይሆን ነበር:: ስለዚህ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ስትቀራረቡና ስትቀናጁ እንጂ ስትነጣጠሉ አይፈልጋችሁም::አይመርጣችሁም::

ኢሕአዴግ እንደ ገዢ ፓርቲ ድርጅቱን በየአመቱ ቦሎ እያስለጠፈ ስላልመጣ፤ አሁን ኢሕአዴግ ገጠመው ትልቅ ፈተና እያስተዋልን ነው:: በሁለት እግሩ መቆም እየከበደው እንደሆነ እያየን ነው:: ለዚህ ማሳያው 2007 ዓ.ም ምርጫ በሀገር ደረጃ ተቃዋሚዎችን በዝረራ ባሸነፈ፤ፓርላማ 99.9 ወንበሮችን ተቆጣጥሬአለሁ ባለ ማግሥት በሁሉም ሀገሪቱ ክልሎች በሚባል መልክ ከሕዝብ የተነሱት አመፆችና ተቃውሞዎች ማሳያዎች ናቸው:: በአገሪቱ ያሉ መሠረታዊ የፖለቲካ ጥያቄዎች የፖለቲካ ምኅዳሩ በትንሹ በሩን ክፍት አድርጎ ቢሆን፤ አሁን በአንዳንድ ቦታዎች ቦሎ ያለጠፉ ተቃዋሚዎች እየያዙት ካለው ጽንፈኝነትና ኢ-ምክንያታዊነት አካሄድ መዳን ይቻል ነበር:: ዜጎች በየጓዳው የሚያነሷቸው የፖለቲካ ጥያቄዎች በግልጽ ተቀምጠው ክርክር ቢደረግባቸው ኢሕአዴግ አሁን ከደረሰበት ክስረት በመጠኑም ቢሆን መንገዳገድ ይችል ነበር::

ለምሳሌ በተቃውሞ እንቅስቃሴዎቹ ላይ ገኖ የወጣው አንዱ የፖለቲካ ጥያቄ የሕወሓት የበላይነት ጥያቄ ነበር:: ይህ አስተሳሰብ በራሱ በድርጅቱ አባላትና ደጋፊዎች ጭምር ጠርቶ አለመውጣቱ፣ በሕዝቡና በድርጅቱ ውስጥ መተማመን እንዳልተደረሰበት ግልጽ ሆኗል:: ከዚህ ጋር ተያይዞ አደገኛ አዝማሚያ እየያዘ ያለውን የአንድ ብሔር የበላይነት አለ የሚለው አመለካከት ያለቅጥ ተራግቦ እዚህ ባልደረሰ፤ፖለቲከኞቹ ባጠፉት ህዝቡ ባልተቀጣ ነበር:: በኢሕአዴግ ዘንድ ከተለመደው ፍረጃና ማጥላላት ውጪ አዲስ ሐሳብ ምክንያታዊ በሆነ መንገድ ለመደማመጥ ፍቃድ ማጣት ተደጋጋሚ ታይቷል:: ኢሕአዴግ እንደ ድርጅት በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ ለማረጋገጥ ዓመታዊ ቦሎ አስደርጎ ቢሆን ኖሮ መልሱን በቀላሉ ያገኘው ነበር:: ኢሕአዴግ ብዙ ጊዜ የሕዝብ መተማመኛ ድምፅ ስለመኖርህ ቦሎ አላስደረክም ሲባል አጀንዳውን ለመቀበል የሚያንገራግር ነበር::

ኢሕአዴግ አንዳንዴ የሕዝብ ጥያቄና የመልካም አስተዳደር ብሶት መኖሩን እንደሚያምን ተናግሮ በሕዝብ ላይ ያደረስኩት በደልና ብሶት ምንድነው ብሎ ለማወቅ ዓመታዊ ቦሎ ማድረግ ይፈልግና፤ ቦሎ ማስደረጉን ትቶ ተሃድሶ መሰል እንቅስቃሴዎችን ብቻ በማድረግ ታድሻለሁ በማለት ትክክለኛ ቦሎ

> **ዘመኑን የማይመጥኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች በ2012 ምርጫ በዝረራ ከመሰናበት ለመዳን ከወዲሁ ፓርቲያቸውን ዓመታዊ ቦሎ በማስደረግ የጎደላቸውን ሀሳብ፤የጠፉባቸውን ዘመነኛ አመለካከት በጊዜ አሟልተው እንዲዘጋጁ እንጠይቃለን**

ሳያስደርግ በቀላሉ እንደሚያስተካክል ለሕዝብ ቃል ይገባል:: ይሁንና አሁንም በዝግ ስብሰባና በድርጅታዊ መንገድ፣ እርስ በርስ በመገማገምና ጥቂት ሰዎችን ከሥልጣን በማንሳት ከሕዝብ የተነሳበትን ጥያቄ ለመፍታት ይሞክራል:: ኢሕአዴግ በተደጋጋሚ የፖለቲካ ምኅዳሩ የማስፋት ጉዳይ ለኢሕአዴግ ብቻ ሳይሆን ለአገሪቱም እጅግ ወሳኝ ጉዳይ ነው ሲባል እሺ ብሎ ይቀበላል:: ወደ ተግባር ሲለውጥ ግን አይታይም:: በኢሕአዴግ ቤት ከስብሰባ በኋላ ሁሌ ተሀድሶ ይባላል:: ከተሀድሶ በኋላ እንደገና ስም ቀይሮ ጥልቅ ተሀድሶ ይባላል:: ሁሌ ንስሀ ነው::

ኢሕአዴግ የፌደራል ሥርዓቱ መጎልመስና ከሥርዓቱ የሚነሱ ጥያቄዎችን በሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት አግባብ መመለስ ሲገባ፤ ነጻና ሕገ መንግሥታዊ ሚናቸውን የሚወጡ የዴሞክራሲና የፍትሕ ተቋማት መፍጠር ሲገባ፤ የተለያዩ አመለካከቶችን በግልጽነትና በምክንያታዊነት የሚያንሸራሽሩ ሚዲያዎች ማስፋፋት ሲገባ፣ ሙስናና በተለያየ መረብ የተሳሰሩ የጥቅም ትስስሮችን መዋጋት ለአገሪቱ ህልውና ወሳኝ መሆናቸው ሲናገር ይከርምና፤በእነዚህ ችግሮች ላይ ዘላቂ መፍትሄ ሳያመጣና ዓመታዊ ቦሎ ሳያደርግ በንስሀ ብቻ ተመልሶ ሥልጣኑ ወደ ማጠናከር ሲሮጥ ተመልክተናል::

የፖለቲካ ፓርቲዎቹ ዓመታዊ ቦሎ ሳይለጠፉ አገር ለመምራት ቁመናቸው ይፈቅዳል ወይ? የሚለው በቅድሚያ መረጋገጥ አለበት:: ይሄ የሚረጋገጥበት አንደኛው መንገድ፣ እነዚህ ፓርቲዎች የሥራ አስፈፃሚ ስብሰባ በየጊዜው ስለማድረጋቸው፣ ባስቀመጡት የጊዜ ገደብ ጠቅላላ ጉባኤ ስለማካሄዳቸው መመርመር ይገባል:: በተጨማሪም ስልጣናቸው የዘላለም እንዳልሆነ አውቀው አንድ ቀን ለተተኪው ትውልድ በመተካካት ባህል ስልጣናቸውን እንደሚያስተላልፉ የሚያምኑ የፓርቲ መሪዎች ሊኖሩን ይገባ ነበር:: እነዚህን ትንንሽ ዲሲፕሊኖች የማያሟሉ ፓርቲዎች ሀገርን ይወክላሉ፤ አገር ይመራሉ ማለት አንችልም::

በአንድ ሀገር ዴሞክራሲ ዓመታዊ ቦሎ በለጠፉ ፓርቲዎች እንጂ ፓርቲያቸውን ማስመርመር በማይፈልጉ አምባገነኖች ሊመጣ አይችልም:: ዓመታዊ ቦሎ የለጠፉ ፓርቲዎች ለሀገር ያስፈልጋሉ:: የፖለቲካ ፓርቲዎቹ ዓመታዊ ቦሎ ካለጠፉ ዴሞክራሲ፣ ፍትሕና እኩልነት አይኖርም፤ ሙስና አይጠፋም፣ መልካም አስተዳደር አመጣለሁ ማለትም ዘበት ነው:: የድርድሩ የመጀመሪያና የመጨረሻ አላማ መሆን ያለበት በፓርቲውና በአባላቱ መካከል ዴሞክራሲና ፍትህ እንዲኖር ማድረግ ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል::

ሲጠቃለል አንድ አገር የዴሞክራሲያዊ ብዙህነትን ማስተናገድ የምትችለው፤ ዓመታዊ ቦሎ የለጠፉ የፖለቲካ ፓርቲዎቹ ተቋማትና የተቃዋሚ ፓርቲዎችን ማስተናገዷ የግድ ነው:: ዴሞክራሲ ስር እንዲሰድ ደግሞ ፓርቲዎቹ ተቋማዊ የሆነ ይዘት ሊኖራቸው እንደሚገባ የሚያጠያይቅ አይደለም:: አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ዓመታዊ ቦሎ ከለጠፈ ተቋሚዊ ይዘት አለው ሊባል ይችላል:: ፓርቲው ያለውን ራእይ ብስለት ባለውና በጠራ ፖሊሲ ላይ የሚጓዝ ከሆነና ያለውን አባልም የጠራ አስተሳሰብ ማስያዝ የሚያስችል አደረጃጀት ሲኖረው ነው::

የአሁኑ የኢትዮጵያ ያሉት አብዛኞቹ የፖለቲካ ፓርቲዎቹ ዓመታዊ ቦሎ ያልለጠፉ በመሆናቸው የአገሪቱ ሁኔታ እጅግ አሳሳቢና አስቸጋሪ እንዲሆን በር ከፍቷል:: አስቸጋሪ የሆነበት ዋናው ምክንያት እርስ በርስ የመናበብ፣ በረጋ መንፈስ የመደማመጥና የመመካከር ባቡር ላይ ለመሳፈር ዓመታዊ ቦሎአቸውን መለጠፍ ስላልቻሉ ነው:: የፖለቲካ ፓርቲዎቹ ዓመታዊ ቦሎ ካልለጠፉ በመካከላቸው ቅራኔዎች ይኖራሉ:: ገዢው መንግሥት ጨምሮ አብዛኞቹ የፖለቲካ ፓርቲዎቹ ዓመታዊ ቦሎ ስላለጠፉ ለሕዝብ ቃል የገቡትን ወደ ተግባር ሲቀይሩ አናይም:: በወሬ ብቻ ሕዝቡን ማሳመንን እንደ ዋና ሥራ አድርገው ይዘውታል፤ ሕዝብ ደግሞ ወደ መሬት ጠብ የሚል ለውጥ ባለማየቱ በፖለቲካ ፓርቲዎቹ ተስፋ እንዲያጣ ሆኗል::

የፖለቲካ ፓርቲዎቹ የተናገሩትን ወደ ተግባር የመቀየር ዓመታዊ ቦሎ ባለመለጠፋቸው እነሱ ይናገራሉ፣ ሕዝብም ይናገራል:: ሰሚ የለም:: በፖለቲካ ፓርቲዎችና በሕዝብ መካከል መተማን የጠፋው በዚህ የተነሳ ነው::

የፖለቲካ ፓርቲዎቹ ለ2012 ዓ.ም (ካልተራዘመ) ዓመታዊ ቦሎ በጊዜ ለጥፈው በጠረጴዛ ዙርያ ተሰባስበው ጥልቅ ውይይት፣ ወደ ተግባር የሚቀየር ንግግር፣ ተስፋ የሚጣልበት መደማመጥ በማድረግ ወደ ሕዝባቸው ሊቀርቡ ይገባል:: ገዢው መንግሥት ሆነ ተቃዋሚዎች ለ2012 ዓ.ም ምርጫ ያልተጠየቁትን ለመመለስ ከመሞከር የሕዝብን የልብ ትርታ በማዳመጥ ለአገራዊ ለውጥ ቅርብ መሆን አለባቸው::


ዘመኑን የማይመጥኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች በ2012 ምርጫ በዝረራ ከመሰናበት ለመዳን ከወዲሁ ፓርቲያቸውን ዓመታዊ ቦሎ በማስደረግ የጎደላቸውን ሀሳብ፤የጠፉባቸውን ዘመነኛ አመለካከት በጊዜ አሟልተው እንዲዘጋጁ እንጠይቃለን:: አንዳንድ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የማይመጥኑ ፖለቲካ ፓርቲዎች ሀገርንና ሕዝብን ወደ ገደል ከመውሰድ ታቅበው ፓርቲያቸውን የሕዝባዊነት፤ የታማኝነት፤ የግልፀኝነት፤ የሰላማዊነት፤ የውህደት፤ የመቀናጀት ዓመታዊ ቦሎ በማስደረግ ለቀጣይ ምርጫ ለመወዳደር ዝግጅት እንድታደርጉ ከወዲሁ እንመክራለን::

***ኢትዮጵያ ለዘላለም በክብር ትኑር***

# “ ኦነግ መንግሥት ያለውን አልቀበልም፣ ሥርዓቱን በኃይል አፈርሳለሁ ካለ ስህተት ነው”

## “ትናንት የትግሉ ተቃዋሚ ነው በሚል ኦህዴድን ወደ ኋላ መግፋት አይቻልም”

### አቶ ኦልባና ሌሊሳ (የኦፌኮ አመራር)



***ኦልባና ሌሊሳ ኦልጀና በምዕራብ ሸዋ “ጨለያ” ተብላ የምትጠራ ከተማ ነው የተወለደው:: በኦሮሞ ሕዝብ የነጻነት ትግል ውስጥ በግንባር ቀደምትነት ከሚጠቀሱ ፖለቲከኞች መሀል አንዱ ነው:: በዶ/ር መረራ ጉዲና የሚመራው የኦፌኮ (ኦሮሞ ፌዴራል ኮንግረስ) ከፍተኛ አመራር ሲሆን፣ በ2003 ዓ.ም በሽብርተኝነት ተከሶ የአስራ አንድ ዓመት እስርና የአራት ዓመት እግድ ተፈርዶበት፤ ሰባት ዓመታት ያህል በእስር ከቆየ በኋላ ባለፈው ዓመት የካቲት ወር ላይ፣ የፖለቲካ እስረኞች በይቅርታ ሲለቀቁ እርሱም ሊፈታ ችሏል::***

***በአሁኑ ሰዐት በተለያዩ የኦሮሚያ ክልሎች የሚስተዋለውን ግጭትና የፀጥታ ችግር፣ እንዲሁም ከኦዴፓ (ኦህዴዶድ) እና ከፌደራል መንግሥቱ ጋር በተደጋጋሚ ግጭት ውስጥ እየገባ የሚገኘውን ኦነግን አስመልክቶ፣ በወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ ከግዮን ጋዜጠኛ ሮቤል ምትኩ ጋር ያደረገውን ቆይታ እንደሚከተለው አቅርበነዋል::***

**ግዮን፡- ከቅርብ ወራት ወዲህ በኦሮሚያ የተለያዩ አካባቢዎች ከፀጥታ ኃይሎች ጋር በተያያዘ የሚነሱ ሁከቶችና ከአጎራባች ክልል ነዋሪዎች የሚፈጠሩ ግጭቶችን እንዴት አየኸው?**

**ኦልባና፡-** ፎርማሊ ኦሮሚያ ውስጥ ከዚህ በፊትም ሆነ አሁን ሁከት ሲፈጠር አላየሁም:: በተሳሳተ መንገድም ይሁን በትክክለኛው መንገድ የሚደረጉት እንቅስቃሴዎች፣ የራስን አቋምና አላማን የማራመድ ጉዳይ እንጂ ሁከት አይደለም:: ይሄ ነገር መጀመሪያ መታወቅ አለበት::

ሁለተኛውና ከኦሮሚያ ክልል ውጭ ከሆኑ ተዛማጅ ክልሎች ጋር የሚደረጉ ግጭቶች፣ ያለውን የኦሮሞ ሕዝብ ትግል ለማዳከም አቅጣጫ ለማሳትና ለማበላሸት ታስበው፣ ኦሮሞን ተስፋ ለማስቆረጥ ከየአቅጣጫው ታቅደው የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን በተመለከተ የሚደረጉ የትግል ውጊያዎች ናቸው እንጂ በደፈናው ግጭቶች ተብለው የሚገለጹ አይደሉም:: ግጭቶች ሳታስበው በአጋጣሚ በጥቃቅን መንገዶች የሚፈጠሩ ናቸው:: እነዚህ ግን ታስበው፣ ተዘጋጅተው፣ ለኦሮሞ ሕዝብና ለኦሮሞ ፖለቲካ ፓርቲዎች የቤት ሥራ ለመስጠት፣ አላማቸውን እንዳያሳኩ መንገድ የመዘጋት ነገር ነው::

ስለዚህ እውነተኛ ዓላማ ያለውና ትክክለኛውን መንገድ የተከተለው አካል አሸንፎ እስኪወጣ ድረስ ይሄ ነገር ይቀጥላል:: አጠቃላይ የትግል እንቅስቃሴው የኦሮሞ ሕዝብን መብት የማክበር ጥያቄን የተመረኮዘ ነውና:: እኔ ሁኔታውን በዚህ መንገድ ነው የማየው::

**ግዮን፡- በለውጡ ማግስት እንዲህ ዓይነቱ ነገር መባባሱ ተገቢ ነው ብለህ ታምናለህ? ነገሮች በአጭር ጊዜ ሙሉ ለሙሉ የሚስተካከሉ ባለመሆናቸው ትዕግስት አያስፈልግም?**

**ኦልባና፡-** የኦሮሞ ሕዝብ የረጅም ጊዜ ትግል ልምድ ያለው ስለሆነ ሁሉንም ነገር ጠንቅቆ ያውቃል:: አሁን ያለው ነገር ሕዝቡ ያልተመለሱለት ጥያቄዎች እንዲመለሱለት፣ ተገቢውን መልስ ካለማግኘት እንዲሁም ጥያቄውን ካለመረዳት የሚመጡ ነገሮች ትግሉን ለማደናቀፍ በእርሱ ላይ የሚመጡ ጫናዎች እንጂ የግጭት ስሜት አይደለም::

በየቦታው የምታየውን ግጭት የተደራጁ አካሎች ተዘጋጅተው የሚፈጥሩት፣ ሕግ እናስከብራለን የሚሉ አካላቶች፣ በሕዝብ ተመርጠው የሀገርና የሕዝብ መሪ ተብሎ የሚታወቅ አካል በሚያሰማራው ኃይል ነው ግጭቶች እየተፈጠሩ ያሉት:: ለምሳሌ በሱማሌ ክልልና በኦሮሚያ የተፈጠረውን ግጭት ካየኸው፣ የተደራጁ አካላት ናቸው የቀሰቀሱት:: በምዕራቡም በኩል ከተመለከትን የሰለጠኑ የፖሊስ ሥነምግባር ያላቸው፣ የፖሊስ ዩኒፎርም በለበሱ አካላትና በሕዝብ መሐከል ነው እየተደረገ ያለው::

እነዚህ ቦታዎች ላይ ያለው ግጭት ሕግን የማስከበር ብቻ አይመስለኝም፣ ለምሳሌ ኦሮሞና ሶማሌን ብትወስድ አርብቶ አደሮች ናቸው፣ ሁለቱም በግጦሽ መሬት ከብቶቻቸውን በሚያበሉበትና በሚያጠጡበት ወንዞች ላይ ለዘመናት ይጋጩ ነበር፤ ግን ወድያውኑ እዛው በሽማግሌዎች ይስማማሉ:: አሁን ግን የሆነው ይሄ አይደለም:: በሰለጠነ አካል በጦር መሳሪያ ተደግፎ የሚደረግ ስለሆነ ከግጭት ዘልሎ ወደ ጥቃትና ጦርነት ተሸጋግሯል:: በአንዳንድ የኦሮሚያ ክልሎች የሚነሱት ነገሮችም ላልተመለሱ ጥያቄዎች በቂ ምላሽ በፍጥነት የመስጠት ጉዳይ ነው::

**ግዮን፡- ባሳለፍነው ሳምንት መገባደጃ የኦነግ ሊ/መንበር አቶ ዳውድ ኢብሳ ሠራዊታቸው ዕርምጃ እንደሚወስድ ተናግረዋል፤ በዚህ ወቅት እንዲህ ዓይነት መንገድ መከተል ጥሩ ነው ብለህ ታምናለህ?**

**ኦልባና፡-** ተገቢ የሆነውን መልስ በተገቢው ጊዜ ካለ መስጠት የሚመጡ ነገሮች ናቸው ያልኩት ይሄንን ነው:: ኦነግ ለረዥም ጊዜ የኦሮሞን ሕዝብ ጥያቄ አንስቶ ሲታገል ነበር፤ ምናልባትም በእሱ የተጀመረው የኦሮሞ ሕዝብ የመብት ጥያቄ አድጎ ዛሬ ኦዴፓን(ኦህዴድ) ከትግል ተቃዋሚነት ወደ ትግል አጋርነት መልሶ፣ እኛንም አፍርቶ እዚህ ደረጃ ላይ በማድረሱ ትግሉን ሲገፉ የነበሩ ሰዎች ተገደው ወደ ትግሉ ካምፕ ተቀላቅለው ትግሉን አምነው ተቀብለዋል::

ይሄ ነገር ሲፈጠር ዓለም አቀፍ የችግር አፈታቶች በነበሩበት ሥርዓት ወደ ቦታው ከገቡ በኂላ፣ ቁጭ ብለው በጊዜው መፍታት ባለመቻላቸው ወደ ግጭት የመሄድ አዝማሚያ ይዟል:: ሁለቱም አካላት ተስማምተው ወደ ሠላማዊ ትግል ሲገቡ ነባር የሆነ መመሪያ አለ፤ ሁለት አካላቶች በመብት ጉዳይ ተጋጭተው  ከነበረ መጨረሻው በአንደኛው አሸናፊነት ከተጠናቀቀ፣ ተሸናፊው የአሸናፊውን ውሳኔ ይቀበልና አርፎ ይቀመጣል:: ልክ ደርግና ወያኔ ሲያደርጉት እንደነበረው ማለት ነው::

ሌላው ሁለቱ አካላቶች መጣላት ለእኛ አያስፈልግም ብለው፣ ፀቡን በመተው ወደ መስማማት መጥተው ከሆነ ቀጣይ ሂደትን በጋራ ነው የሚነድፉት:: አንድ አካል ብቻ አይደለም የሚያወጣው፤ አሁን የሆነውን ነገር ስንመለከት አንዱ አንዱን አላሸነፈም፤ የተደረገው የሕዝብ ትግል ነው፤ ጥያቄው አድጎ የትግሉን ተቃዋሚዎች በማስገደድ ትግሉንና እውነታውን እንዲቀበሉ በማድረጉ ነው:: ሁለቱም በጅምሩ ቀጣይ ሥራችን ምንድን ነው መሆን ያለበት? የምንመራውስ በምንድን ነው? ብለው አጠቃላይ ዕቅድ ቢነድፉ ኖሮ ይሄ ነገር አይፈጠርም ነበር::

የአቶ ዳውድ ኢብሳን መግለጫ ሰምቼያለሁ፤ ሳይቆራርጡ ሙሉውን ያስተላልፉ አያስተላልፉት ባላውቅም:: እሳቸው ‹‹ኃይሉ ገፍቶ ከመጣብን ራሳችንን ለመከላከል ዝግጁ ነን›› ነው ያሉት፤ ይሄን እኮ እሳቸው በቃል ባይናገሩትም ማንም ኃይል የሚያደርገው ነው::

**ግዮን፡- እንዲህ ብለው መናገራቸው ተገቢ ነው? ኦነግ በሀገሪቱ የመጣውን ለውጥ ተጠቅሞ፣ በሠላማዊ ድርድር ወደ ሀገር የገባ እንጂ ተዋግቶ አሸንፎ ወይም ድል ቀንቶት የመጣ ኃይል አይደለም፤**

**ኦልባና፡-** ልጅ ሆኜ እንስሳቶች በሙሉ ሲወልዱ አያለሁ፤ በቅሎ ግን አትወልድም፤ አንድ ቀን አያቴን "የእከሌ በቅሎ ለምን አትወልድም" ስላቸው "አባቷን ስለናቀችው ተረግማ ነው" አሉኝ:: መጣ በሚባለው ለውጥና ትግል ውስጥ ሁላችንም የራሳችንን ድርሻ ተወጥተናል:: ግን የእዚህ ሁሉ ትግል እሳቤ የመጀመሪያ ባለቤት፣ አያትም ይሁን ቅድመ አያት፣ የኦሮሞ ሕዝብ ትግል ባለቤት ኦነግ ነው:: አሁን የመጣውን ለውጥ ኦነግ አላመጣም አይደለም ነገሩ፤ እዛ ክርክር ውስጥ አንግባ::

ለውጡ ከመጣ በኂላ ያለውን ብንመለከት ኦዴፓ(ኦህዴድ) ይሄን ለውጥ በመምራቱና በማገዝ ላይ ትልቅ አስተዋፅኦ አድርጓል:: አሁን ኦዴፓ ትግሉን ወደ ፊት በመግፋት በኩል ዓይነተኛ ሚና እየተጫወተ ነው:: ትናንት የትግሉ ተቃዋሚ ነበር በሚል ኦህዴድን (ኦዴፓ)  ወደ ኂላ መገፋት የለበትም፣ ስህተትም ነው:: በተደረገው ፍልሚያ አንተ ግምባር ላይ ወይም ደግሞ ሀገር ውስጥ አልነበርክም፣ መሪዎችህ እስር ቤት አልነበሩም፣ ተብሎ ኦህዴድ የሚገፋበት ሁኔታ ላይ አይደለም ያለነው:: ሁሉም በራሱ መንገድ ይሄ ለውጥ እንዲመጣ ዋጋ ከፍሏል:: አስተዋፅኦ አድርጓል::

ከጃዋር መሀመድ ጀምሮ አቶ ዳውድ ኢብሳ፣ እነ ለማ መገርሳ እኛን ጨምሮ በነበርንበት መንገድ በሀገሪቱ ለውጥ እንዲመጣ ሁላችንም ዋጋ ከፍለናል:: አሁን የሚያጣላን ትናንት ማን ምን ሠራ የሚለው አይደለም:: እሱን ታሪክ ለባለቤቱ ይሰጠዋል:: ጥሩ ሥራ ለሠራው ተገቢውን ቦታ መስጠቱ ቆንጆ ነው፣ ግን በዋነኝነት መስማማት ያለብን የዛሬውን ሥራ እንዴት እናስቀጥል በሚለው ላይ ነው:: እኔ ትናንት ትልቅ ድርሻ ስለነበረኝ ዛሬ አንተን አገላለሁ የሚል ከሆነ፣ የሚገለለው አካል ይቀበላል ወይስ አይቀበልም? ብለህ ማሰብ አለብህ::

**ግዮን፡- አንተ በግልህ ኦነግ አሁን እያደረገ ያለው እንቅስቃሴ ትክክል ነው ብለህ ታምናለህ?**

**ኦልባና፡-** ያሉበትን ሁኔታ የሚያውቁት እነሱ ናቸው:: ከሆነ ጊዜ በኂላ አላስፈላጊ የሆነ የሕዝብ ማፈናቀል ችግሮች ስለነበሩበት አሁን በቦታው በትክክል ምን እንዳለ የሚያሳይ መረጃ ስለሌለን፣ ከመስመር ያለፈ ነው የሚል አቋም መያዝ፣ ወይንም ደግሞ ትክክል ነው የሚለው ቦታ ላይ አልደረስንም:: ግን አንድ ኃይል አንተ ያለህበት ካምፕ ድረስ ሊያጠቃህ ከመጣ ራሴን እከላከላለሁ ብለህ መናገር እኮ ተገቢ ነው፤ ሳትናገርም እኮ ትከላከላለህ::

ተጠቅልሎ የተኛን ውሻ ዞረህ ካልነካኸው አይነክስህም:: መስመሩን ይዞ የሚሄደውን ጉንዳን ከነካኸው ይበታተናል፣ ቀጥሎ ራስህን ይነክስሃል:: ስለዚህ አሁን እየተደረገ ያለውን ነገር እንደ ድርጅትም እንደ ግለሰብም ጊዜ ሰጥተን የምናየው ነው:: ከግጭት በኂላ ያሉ ጉዳዮች የሚፈቱበት ዓለም አቀፍ የሆነ ሥርዓቶችን ተከትለው ሁለቱ ወገኖች አንዱ ሌላውን ከመክሰስ ይልቅ፣ መፍትሄ ቢፈልጉ ጥሩ ነው የሚመስለኝ:: ምክንያቱም እውነቱ ነገ ይጠራል:: የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች ብዙ ጊዜ የሚያስቡት የሚቀናቀናቸውን ሰው ማሸነፍን ብቻ ነው:: ግን ማሰብ ያለባቸው ሰውዬውን ካለፍኩ በኂላ እኔ እንዴት አድርጌ ሰርቫይቭ አደርጋለሁ የሚለውን ነው:: አንተ ሳትወድቅ፣ ሳትሳሳት፣ ሳትዋረድ እንዴት አድርጌ እስከመጨረሻው ድረስ እዘልቃለሁ የሚለውን ማሰብ ነበር የሚጠቅመው::ኦነግ ይሄንን መንግስት አልቀበልም፤ ሥርዓቱን በኃይል አፈርሳለሁ የሚል ከሆነ ትክክል አይደለም::

**ግዮን፡- ኦነግ ትጥቅ አልፈታም ማለቱስ ትክክል ነው?**

**ኦልባና፡-** ባለፈው ጊዜ አቶ ዳውድ ኢብሳ መግለጫ ሲሰጡ ትጥቅ አንፈታም አይደለም ያሉት፣ እኔ የሰማሁት እንደዛ ነው:: አሁንም ኦነግ ትጥቅ አልፈታም ያለ አይመስለኝም:: ግን ትጥቅ አፈታት ላይ ስነ ስርዓት አለው እያለ ነው:: ይሄንን ሥርዓት አሁን ያለንበት ደረጃ ያመጣው ኢህአዴግ በራሱ ፍላጎት አይደለም:: እኔ ለውጡን ስላመጣሁ በበላይነት እቀጥላለሁ የሚል ሐሳብ ከኦህዴድ ወይም ከኢሕአዴግ ካምፕ የሚወጣ ከሆነ ትክክል አይደሉም:: ኦነግም እኔ ነኝ ብቻዬን ያመጣሁት ብሎ በበላይነት ልምራ ካለም ልክ አይደለም:: ይሄን ለውጥ ያመጣው ሕዝብ ነው:: ሕዝብ ደግሞ ፖለቲካን መምራት ሳይሆን መብቱን ማስከበር ነው የሚፈልገው፤ ስለዚህ ፖለቲከኞቹ ተስማምተው ተነጋግረው መቀጠል አለባቸው::

ኦነግ የታጠቁ ኃይሎች ካሉት እነሱን የት ያድርጋቸው? እነሱን ተቀብሎ በአግባቡ የሚያስተናግድ ሥርዓት መፈጠር አለበት:: ሥርዓቱ ይፈጠርልኝ ብሎ ጥያቄ ካቀረበ ትክክል ነው፤ ለጠየቀው ጥያቄ መልስ ተሰጥቶት በእድሉ አልጠቀመም ካለ ነው ስህተት የሚሆነው:: ያ ለመሆኑ ደግሞ መንግሥት እስካሁን ድረስ በይፋ የገለፀልን ነገር የለም:: ያረጋገጥነውም ነገር የለም:: ለምሳሌ ሥልጠና ላይ አሉ የተባሉትና ከኤርትራ የመጡትን ሰዎች ለመንግሥት አስረክቧል፤ እነዛ ሰዎች ምን እንደሆኑ እኔ በግልፅ አላውቅም:: ስለዚህ አንዱን ካምፕ ማጠናከር፣ አንደኛውን ማፍረስ ሳይሆን መሆን ያለበት፤ የጋራ የሆነ ቤትና ሥርዓት መገንባት ነው:: ይሄንን ስናደርግ ደግሞ የተሻለ ፖቴንሺያል ያለውን አካል መጠቀም አለብን::

**ግዮን፡- ኦነግ ከሕወሓት ጋር ተወዳጅቷል እየተባለ ነው፤ አቶ ዳውድ ኢብሳ ወደ ሀገር ቤት ከገቡ በኂላ ከኦሕዴድ (ኦዴፓ) ጋር አንድ ጊዜ ሲጣሉ፣ መልሰው ሲታረቁ ፤በቅርቡ ደግሞ ተመልሰው ሲጣሉ ተመልክተናል:: ይሄ ነገር ድርጅቱን ወላዋይና አቋም የለሽ አያደርገውም?**

**ኦልባና፡-** ሕወሓት ይሄን ያህል የባሕሪ ለውጥ አምጥቶ ከእኛም፣ ከኦሕዴድም አልፎ ከኦነግ ጋር ድርድር ጀምሮ ከሆነ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ከሥሩ ተለውጧል፤ ሕወሓቶችም ከጥፋታቸውና ከስህተታቸው ታርመው ወደ ትክክለኛው መንገድ እየመጡ ነው የሚል እሳቤ ነው የሚፈጥርብኝ፤ እውነት ከሆነ ማለቴ ነው:: ምክንያቱም እስከማውቃቸው ድረስ የኦነግ አመራሮች ይሄን ያህል የወረደ ስህተት ይሰራሉ ብዬ አላስብም::

የኦሮሞ ሕዝብ አብዛኛው ሰው ከኦነግ የወጣ ነው፣ ወይም አሁን ከኦነግ ጋር ያለ ነው፤ ትናንት በኦሮሞ ሕዝብና ትግሉ ላይ እንደዛ ዓይነት ዘግናኝ ግፍ ሲፈፀም ከነበረ አካል ጋር ያለ ምንም ተጨባጭ ምክንያት ሄዶ ኦነግ ይደረደራል የሚል ዕምነት የለኝም:: ያንን የሚያሳይም መረጃ አልደረሰኝም:: መረጃው ከደረሰኝ ግን እኔ ብቻ ሳልሆን ድርጅቴ ኦፌኮም የራሱን አቋም ይወስናል:: አሁን ያለው ሐሜትና የማጥላላት ነገር ይመስለኛል::

ከእነ ለማ ጋር የሚደረገውን ግጭትም የከፋ ነገር አድርጌ አልቆጥረውም:: በሥራ ላይ አለመስማማት አለ፤ ለሕዝባቸው እንዲሰራ በሚፈልጉት እንኳን የትኛው ይቅደም በሚባለው ራሱ አለመስማማት ይኖራል:: የከፋ ግጭት እስካልገቡ ድረስ:: ቅርብ ለቅርብ ተገናኝተው እስካልተገናኙ ድረስ:: በኦነግና በኦዴፓ (ኦህዴድ) በኩል እስካሁን ድረስ ያለው ነገር ያን ያህል መጥፎ የሚባል አይመስለኝም:: ልዩነቶች መኖራቸው ግን ሐቅ ነው::

**ግዮን፡- እናመሰግናለን::**



በምስጋን ዝናቤ ተሜ

# የሥልጣን ዕፀ በለስ

ዘሬም ከቅድመ አያቶቻችን አዳምና ሔዋን ነገረ ታሪካችንን መነሻ ማድረጋችን አያስደንቅም። እነርሱ የታሪክ እርሾ ናቸውና፤ ያለ እነሱ የተቦካ ነገር እህል ዉኃ የለውም። ለምሳሌ በሩጫ ሕግ ወደ ኋላ ተንደርድሮ ወደፊት መሮጥ የሚል ጥበብ አለ። ምሥጢሩ የረቀቀ አይደለም፤ ኃይል ለመጨመር እንደሆነ እናምናለን። በተለይ ዝላይ ለመዝለል በደንብ የመንደርደርና የመስፈንጠር ሁናቴ ይታያል። እኛም ወደኋላ ስንስፈነጠር ወደፊት ለመስፈንጠር ጥበባችን እንደሆነ እናምናለን። ስለዚህ በዚያን ጊዜ እንዲህ ሆነ። ሰይጣን ለአዳምና ለሔዋን የሀሰት የሹመት ደብዳቤ በእባብ በኩል ላከላቸዉ። ደብዳቤውም ቀድሞ ለሔዋን ሲነበብላት መግቢያው እንዲህ ይላል። "የሰማይና የምድር ንግሥት ሆይ ደስ ይበልሽ" ይሄኔ የሔዋን ልብ ማለለ። ገነትን የመሰለ ውብ ሀገሯን ልትሰናበታት በምኞት አንቀልባ ታዘለች። የመጀመሪያው የሥልጣን ጥማትም በሔዋን አዕምሮ ተጸንሶ በአዳም ልብ ተወለደ። ሊኀቃን የኃጢአት ልደቱን "ኃጢአተ አዳም" ይሉታል። የኃጢአት ነገረ ብኩርናውን ሲያጠኑ ማለት ነው። ቀጥለውም የሰው ልጅ በፍጥረት መጀመሪያ ቢፈጠር ኖሮ እኒህን ሁሉ ፍጥረቶች እኔ ነኝ የፈጠርኳቸዉ ብሎ ይሸመጥጥ ነበር። ፈጣሪ ግን ይህ ሙግት እንዳይከሰት ብሎ የሰውን ልጅ በፍጥረት መጨረሻ ፈጠረው ይላሉ። ልክ የመላእክት አለቃ የነበረው ሳጥናኤል እኔ ነኝ አምላካችሁ ብሎ ወደ እንጦርጦስ እንደ ተወረወረው ሁሉ የሰው ልጅም ሥልጣን በመመኘቱ ከገነት ወደ ፈተና ቦታ ምድር ተወረወረ። እዚህ ላይ ልብ የምንለው ነገር ከአዳምና ሔዋን የሥልጣን መሳከር ባሻገር እግዜር በጠየቃቸዉ ጊዜ የመለሱትን መወነጃጀል ነው። እሱም አዳም ሔዋን አሳተችኝ ሲል፤ ሔዋንም እባብ አሳተችኝ ብለው ለየብቻ ስበብ ፈጠራ ተሰማርተው መፈላሰማቸው ነዉ። ይበልጥኑ የሚያስገርም።

> የፖለቲካ ቲፎዞ አራጋቢዎችም እርስበርስ ተካሰዉ ይወነጃጀላሉ። የኩነኔ ቀንበሩን ይዋዋሳሉ። ያኛው መንግሥት እንዲህ ነበር። ይኸኛው መንግሥት እንዲህ ነዉ። እየተባባሉ ዘመናቸውን በመፈራረጅ ይገፋሉ። በተለይ እኛ ኢትዮጵያዊያን የሥልጣን ጥማታችን ከፍ ያለ በመሆኑ ሁልጊዜ የጠባችን መነሻ ይኼው መሆኑ ያሳዝናል

ፈጣሪም የሁለቱን መቅበዝበዝ ተመልክቶ "አሁን ለሆነ ነገር ምክነያት አያድንም" ብሎ ሲባርቅባቸዉ አዳምና ሔዋን ቅጠል ለበሱ። አፈሩ፣ ምነው ባላደረግነው፣ ምነው ትእዛዙን ባልተላለፍን እያሉ የመቶ ዓመት ሱባዔ ቢያካሂዱም ቅሉ ከመርገመ ፍርዱ አላመለጡም። ከቃሉ መዛነፍን የማይወደው አምላክ "አዳም... ወደየት ነህ" እያለ ፍለጋ ሲመጣ አዳም እያወቀ የሻራት ትእዛዝ ባይኑ ውል እያለበት ይባስኑ ተሸማቆ ገላው የመርግ ያህል ከብዶት ጫካ ዉስጥ ተሸሸገ። ፈጣሪ ግን ሁሉንም ያውቃልና የዕዳውን ደብዳቤ ለመቅደድ ከአዳም አንድ መልካም ነገር አገኘ። ፍቅር፤ ፍቅር ደግሞ እግዚአብሔርን ይማርከዋል። አዳም የአምላኩን ትእዛዝ ተላልፎ የበለሷን ፍሬ ከሔዋን እጅ የጎረሰዉ ፍቅር አሸንፎት ነው። ስለዚህ በፍቅር የተሸነፈ አዳምን በፍቅር ሊያድነው ከአጠፋችዉ የሔዋን ዘር አዳኙ እንደሆነችም ለማዘከር ክርስቶስ ከልጅ ልጁ (ከማርያም) ተወለዶ አዳነው። ይህንን ታሪክ እንደ ጉርሻ ወይም እንደ መነሻ መሰላል ያደረኩበት ምክንያት ትውልድ ከዚህ የተለየ ዳና ተከትሎ እንዳልመጣና ወደፊትም የተለየ መንገድ እንደ ማይመርጥ ለማሳየት ያህል ነው። ዛሬም እንደ ትላንቱ ዓለም ያረቀቃት የሥልጣን ዕፀ በለስ እንዳሳደደችን አለች። ሀገር በቃል ኪዳኗ እንደ ፈጣሪ መስቀለኛ ጥያቄ ስጠይቀን መልሳችን ሥልጣን እንደ እባብ መልክተኛ ሆና አሳተችን የሚል ይሆናል። የፖለቲካ ቲፎዞ አራጋቢዎችም እርስበርስ ተካሰዉ ይወነጃጀላሉ። የኩነኔ ቀንበሩን ይዋዋሳሉ። ያኛው መንግሥት እንዲህ ነበር። ይኸኛው መንግሥት እንዲህ ነዉ። እየተባባሉ ዘመናቸውን በመፈራረጅ ይገፋሉ። በተለይ እኛ ኢትዮጵያዊያን የሥልጣን ጥማታችን ከፍ ያለ በመሆኑ ሁልጊዜ የጠባችን መነሻ ይኼው መሆኑ ያሳዝናል።

አፍርሶ ገንቢ ጀግንነት ይመስል ሁልጊዜ አዲሱ መንግሥት ነባሩን ሳያጣጥል አዲሱን ፖሊሲ አይጀምርም። በርግጥ የፖለቲካ ጨዋታው እንደዚያ ነው። ቢሆንም ከመራራው ጣፋጭ እንደሚገኝ ሁሉ ከእነሱ የስህተት ባሕር ተመልሼ እንዳልዘፈቅ የትኛውን ላሻሽል፣ የትኛዉን ላስቀጥል፣ የትኛውንስ ልተዉ ብሎ የባለፈን ሰነድ ገልጦ ለማንበብ ይጸየፈዋል። ይህም የመጥፎ ነገር ወራሽ ዓመል ያለበት ያስመስለዋል። ልብ ካልነው እኮ ሰይጣንም አስተማሪ ነው። እንደውም የጠላት አስተማሪነት ከሁሉም ▶

የበለጠ መሆኑን ፈላስፎች ይራቀቁበታል። በሀገራችን የሥልጣን ሽግግርም ሆነ የሥልጣኔ ቅብብሎሽ ትንሽ እንደ ትል እሳት ቦግ ብሎ የታዘብነው ከአጼ ቴዎድሮስ እስከ አጼ ምኒልክ ያለውን ዘመን እንደ ናሙና ማንሳት እንችላለን። እሱም ቴዎድሮስ በዘመነ መሳፍንት የተበታተነች ኢትዮጵያን አንድ ለማድረግ ታገሉ። ትግሉን አጼ ዮሐንስ ተቀበሉ። እርሳቸውም በድፕሎማሳዊ መንገድ ለምኒልክ አስረከቡ። ምኒልክ ደግሞ የሁላቸውንም ህልምና ረቂቅ ሐሳብ በአንድላይ ቀይጠው በአማረ ዲፕሎማሳዊ ሥርዓት ኢትዮጵያን በአብራካቸው ፈጠሩ። ኢትዮጵያም ልጃቸው ምኒልክን ትመስላለች። ሆኖም እነ ተፈሪ መኮንን "ሥዩመ እግዚአብሔር" ብለው ራሳቸውን በራሳቸው ሲያነግሱ ለሀገሪቱ የተለየ ነገር ይዘው ብቅ አሉ። እሱም በ1920 ዎቹ የተጀመረው የተጻፈ ሕገ መንግሥት ከዚህ ሥርዓት ይልቅ እንደ ሕገ ልቦና ባልተጻፈ ሕገ መንግሥት እየተመራን ሳለ የተሻለ ነበርን ለማለት ያስደፍራል። በዚያን ጊዜ ምንም እንኳን መንደራዊ የሥልጣን ሽርኩቻ አልፎ አልፎ መንጸባረቁ ባይቀርም። የድሮ ነገሥታቶች ግን በፍቅረ ሥልጣን ውስጥ ሀገርን በልባቸው አንግሰው ስለሚማጎቱ ከዛሬ ፍቅረ ነዋይ ወይም ሃይማኖተ ገንዘብን በልባቸው ካነገሱ ፖለቲከኞች በእጅጉ የተሻሉ ናቸው። በርግጥ ያም እንደ ዘመኑ ይህም እንደ ዘመኑ ሲመዘን በኢትዮጵያ ጥቁር ነጥብ ያላሳረፈ መንግሥት የለም ለማለት አያስደፍርም። ሁሉም ሥልጣናቸውን ለማራዘም ወይም አይነኬ ፖለቲካቸውን በነጻነት ለማራመድ ሲሉ ለሀገር የሚበጁ ጎምቱ ምሁራኖችንና ታዳጊ ብላቴኖችን እንደ ሔሮድስ ጨፍጭፈዋል። እነ ንጉሥ ቴዎድሮስ ይህንን መሳፍንታዊ አገዛዝ ወደ አንድ መንግሥታዊ ጥላ ሥር ለመሰተር ያስከፈላቸዉ ዋጋ ቀላል አልነበረም። በዚያ ግርግርም ብዙ ወርቃማ የኢትዮጵያ ልጆች በጉርኖ ቤት ተቃጥለዋል። ሁነቱን "አይጥ በበላች ዳዋ ተመታ" ዐይነት ያስመስለዋል። በታሪክ ስንክሳር የማንዘነጋው የታኅሣሥ ግርግርም የሀገራችን ዊልበር ራይቶችን ወይም ወንድማማች ግርማዊ ነዋይና መንግሥቱ ነዋይን ብሎም ሌሎች ብርቅዬ የኢትዮጵያ ልጆን አሳጥቶናል።

ከዚህ ሁሉ ኹነት ቀጥሎ ኢትዮጵያን ከፍ ወዳለ ፈተና ያሸጋገራት ኢሕአዴግ በጎሰኝነት እጁ የቀነጠሳት እፀ በለስ እንደሆነችና ትውልዱንም ኢትዮጵያዊ የጥበብ ክህሎት እንዳያዳብር በተወናበደ ወይም በተደባለቀ ምዕራባዊ ፍልስፍና አብዶ ወጀብ እንዳናወጣት መርከብ እንድቅበዘበዝ በር የከፈተ፤ የቃየል ደቀመዝሙር ተብሎ የተፈረጀ፤ ብዙ የበረከት ንፍገት፣ ብዙ ሀገራዊ መርገምን ያስከተለ፣ ሶዶማዊ ታሪክ ተብሎ በመጥፎ መዝገብ ሊነግስ እየተጣደፈ ያለ ቢመስልም አሁንም ነገሩን ልብ ብለን ካየነው ከእስከዛሬዉ ሀገራዊ ፖለቲካ የተለየ መልክና ይዘት ይዞ አልመጣም። ምናልባት ልዩ የሚያደርገው በመንግሥትም ሆነ በሕዝቡ መካከል ኢትዮጵያዊ ፍቅሩ መቀዝቀዙ ይሆናል። ይኼ ከባድ ፈተና ነው። አንድ ንጉሥ በሥልጣን ምክንያት መርገም ቢያስከትልም ለሀገሩ የመስዋዕት በግ ሆኖ ራሱን እንደ ሚሰቅል አያጠራጥርም። ይኼ ደግሞ እኛን ይማርከናል። እንደ ካሳ ሆኖልናልና። ንጉሥ ቴዎድሮስ መነሻቸው ሽፍትነት ነበር። ንጉሥ ምኒልክም ከሽፍትነት ያላነሰ ነው አጼ ዮሐንስን በፈተና ድንኳን ከልለው ግራ ቀኝ አዋክበዉ ያዳከሚቸዉ። ንጉሥ ኃይለሥላሴም ብላቴናው

ልጅ እያሱን ወይም ወግ አጥባቂዋ ንግሥት ዘውድቱን በሥሩ ለማሳደር ያልሸረቡት የተንኮል ድሪ አልነበረም። ኮለኔል ጓድ መንግሥቱ ኃይለማርያምም እንዲሁ ጃንሆይ "እጄ አመድ አፋሽ" ሆነ ብለው እስኪጸጹቱ ድረስ ራሳቸው አሰልጥነው ባቀኑት ልጃቸው ከመንበረ ዙፋናቸዉ ተፈናቅለዋል። ሁሉም የዘራውን ያጭዳል እንደ ተባለ ሁሉ ጓድ መንግሥቱም በታጋይ ብርቱ ትግል እንኳን ከሥልጣነ መንበርና ከሀገራቸዉ ተሳደዋል።

ይኼን ሁሉ ፖለቲካዊ ስንክሳር ልብ ብለን ስንፈትሸው በሥልጣን እጸ በለስ የተከሰተ ቢሆንም አንድ መሠረታዊ ነገር ግን በቀጭኑ ተጎንጉኖ ይታየናል። እሱም የአፍሪቃ መሪ ወንበር ከያዘ ለመልቀቅ ሞት ይመስለዋል እንደተባለ ሁሉ የኛ ሀገር የሥልጣን ሽግግርም ያለ ጦርነት የሆነ የለም። ያሸነፈ ጀግና ዙፋኑ ላይ ይነግሳል። ስለዚህ በምርጫ አሸንፌ የምወዳት ሀገሬን አገለግላለሁ ብሎ የሰነቀ ኢትዮጵያዊ መሪ (ፖለቲከኛ) አማራጩ ጦርነት እንጂ የምርጫ ሳጥን እንዳልነበር እንታዘባለን። በዚህ ዉጣ ውረድ የተገኘች ወንበርን ከመልቀቅ ሞቴን እመርጣለሁ የሚል መሪ መበርከቱ ደግሞ ሥልጣኔአችንን ቁልቁል እየነዳ ግራ ቀኝ እያዋከበ ሽቅብ ዝንቅ ያላገዋል። ክርስቶስ "ኃጣንን ላድን እንጂ ጻድቃንን ላድን አልመጣሁም" እንዳለው ሁሉ አዳዲስ የሚነግሱ መሪዎቻችንም ይህንን ሕግ ለሕይወት መመሪያቸው ቢጠቀሙበት ምናልባት ይህ ሁሉ ፈተና ባልተከሰተ ነበር። እነርሱ ግን ሹም ሆኖ ያልበላ ሲወርድ ይቆጨዋል በሚለው አባባል የተታለሉ

> **ጋራ ተራራ እየገመሱ፣ በቆዛሚ የጎሰኝነት ግንብ ታጥረው የቤተሰብ መደባቸዉን ለማስፋፋት የነገሱ ይመስል ኢትዮጵያዊያንን በእኩል ዐይን ያለ ማየት አባዜ በገቢራቸዉ መኻል ይንጸባረቃል**

ይመስላሉ። እሱም በንግሥና ዘመናቸው ዘር ቀለም እየቆጠሩ፣ ወንዝ ፈፋ እየተለሙ፣ ጋራ ተራራ እየገመሱ፣ በቆዛሚ የጎሰኝነት ግንብ ታጥረው የቤተሰብ መደባቸዉን ለማስፋፋት የነገሱ ይመስል ኢትዮጵያዊያንን በእኩል ዐይን ያለ ማየት አባዜ በገቢራቸዉ መኻል ይንጸባረቃል። ይህ ዓይነቱ አስተሳሰብ ግን የቀድሞዎቹን መሪ አብዝቶ አያካትትም። እነሱ የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች መሆናቸውን በተለያዩ የጦርነት ፊልሚያዎች ማለትም ቴዎድሮስ በመቅደላ፣ ዮሐንስ በመተማ፣ ምኒልክ በዐድዋ፣ ያላቸውን ብርቱ ኢትዮጵያዊነት ፍቅር አሳይተዋል። ከእነዚህ የቀደሙት ኢትዮጵያዊ ነገሥታቶች የጎላ እንከን ስሌለባቸዉ ወይም ሕገ ልቦናዊ አስተዳደር ስለነበራቸው ያያን ያህል ብናመሰግናቸዉ እንጂ ብንወቅሳቸዉ ተገቢ አይሆንም። ከዚያን ወዲህ ከበፊቶቹ ሰለጠንን ብለው በተጻፈ ሕገመንግሥታዊ ሥርዓት የነገሡ መሪዎችን ስንታዘባቸው ወጥ የሆነ ገድል አናይባቸዉም። አሁን ደግሞ ይባስ ብሎ አንድ መሪ ሲሾም ምን ያህል ብቁ ነው ብሎ ከመገምገሙ ይልቅ ከየትኛው ብሔር መጣ የሚል የዘረኝነት መነፀር መበጀቱ በአንድ አገር ላይ ብዙ አገር ያለ ይመስል ረባሽ ስዕላዊ ባንዲራ ያዉለበልባል። በጥቅሉ ይኼን ትውልድ ከእስከዛሬው ለየት የሚያደርገው ይኼው ነው። ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር በዚህ ትውልድ ልብ ነግሳለች ለማለትም ያያን ያህል በልበ ሙሉነት ለመናገር አያስመካም። ሁሉም ለሠፈሩ ታሪክና ለመንደሩ ጀግና መዘመር ጀምሯል። አይዘመር ማለታችን ሳይሆን ምናልባት እንደ ዋዛ ኢትዮጵያን እንዳንረሳት ብለን ስለ ሰጋን እንጂ።

አሁን የሥልጣን ትንቅንቁን ከደመ ነፍሳዊ ወደ ነፍሳዊ፣ ከካድሬነነት ወደ ፍትሐዊ ሥርዓት ለማዘመን የዶክተር ዐቢይ ተጋድሎ ቀላል አይደለም። ምናልባት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ይህንን ታሪክ ከቀየሩ በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመሪያው ወይም ዳግማዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ሳይሆኑ አይቀርም። በምርጫ ቦርዱ የተሰየሙ አመራሮች የሕዝቡን ተስፋ ከፍ ያደርጋሉ። ሥልጣን ለእኩል መካፈል ወይም ባለ ሥልጣን ለሕዝብ አገልጋይ መሆኑን ለማሳየት ቀና ደፋ እያሉ ነዉ። ሁሉም ይህንን ታሪካዊ ሽግግር አንግሶ የባለፈውን የኋላ ታሪክ ተረት ተረት ብሎ ለማውጋት ቸኩሏል። ኢትዮጵያም እንደ አውሮፓዊያን ፍትሐዊ የሥልጣን ሽግግር ሀ ብላ ጀምራ እንደሁ ሁ ብላ የታሪክ ንባብ ለማንበብ ናፍቃለች። 2012 የኢትዮጵያ የትንሳዔ ምፅዓት ነች። ከዚያን በኋላ ነው የኢትዮጵያ ህልውና ከሲኦል ገሃነማዊ ወደ ገነታዊ ህልውና ይቀየራል የሚባለው። ዛሬ በዋዜማ ምርጫው የመንግሥትን ትንቢታዊ ምልክቶች በሥራ ሚዛን እየመዘንን እንገመግማለን። በኢትዮጵያ ሰማይ የሚያንዣብቡት የፖለቲካ ፓርቲዎችም እንደ ጥንብ አንሳ አሞራ ሥልጣን ፈላጊዎች ናቸው ወይስ እንደ ንሥር አሞራ ለወጥ ፈላጊዎች ናቸው። ሁሉንም በዋዜማ ምልክታቸው ለመገምገም ብንሞክርም በዕለተ ቀኑ ጊዜ ያፋርደናል። (እስከዚያዉ ዕድሜና ጤና ለኢትዮጵያና ለሕዝቦቿ እንዲሁም ለእህት ጎረቤት ዓለማቶች መልካሙን ሁሉ እንመኛለን።)

# “ልውጥ” እና . . .

ከገጽ 28 የዞረ

የተሟላ የሕይወት ይዘት የሚያውቅ የዕጽዋት ግዛት አለ:: ‹‹ከኔ በላይ የለም›› ይላል የዕጽዋት ግዛት፤ ባለማወቁ ግን የእንስሳ ግዛት ይስቅበታል! … ‹‹ትልቁ የሕይወት ይዘት የሰብዓዊያን ግዛት ነው›› የሚሉ አሉ፣ ግን ተሳሳቱ - ትልቁ የሕይወት ግዛት የእግዚአብሔር ግዛት ነው!

የማዕድን ግዛት እንዴት ወደ ዕጽዋት ያልፋል? ሮዝ አበባ የበቀለበትን ቆሻሻ የጭቃ አረንቋ እንይ! ጭቃ እንዴት አበባ ሆነ? ራሱን ማንሳት አይችልም:: አንድ መንገድ ብቻ አለ:: ትልቁ ግዛት ወደ ትንሹ ይወርዳል፡- ትንሹ ግዛት ‹‹ንጥረ-ነገሩን›› ለዕጽዋት ያስረክባል፤ ወደ ላይ ይመጠጣል፣ ወደ አማረ አበባ ይለወጣል:: ከላይ ይወለዳል:: ለትልቅ የሕይወት ብቃት ከታች ሳይሆን ከላይ መወለድ ያስፈልጋል:: ‹‹እናንተ ከታች ናችሁ፤ እኔ ከላይ ነኝ …›› አለ ኢየሱስ (ዮሐ. 8፡23):: ከላይ ያልተወለደ የሚነረል ግዛት የዕጽዋትን ግዛት አያይም:: የሚነረል ግዛት እንዲወጣ፣ የዕጽዋት ግዛት መውረድ አለበት:: የሕይወት ሕግ ነው:: ትንሹ ትልቅ እንዲሆን ትልቁ ትንሽ መሆን አለበት!

‹‹ሕይወት ከታች ይወለዳል›› የሚሉ አሉ:: ውስጣዊ ግፊትና ደመ-ነፍስ “ችግር” እንደሆን በማሰብ፣ ልጓም-የለሽ ስሜት ተሞርዶና ለስልሶ የሕይወት ብቃት መላበስ ይቻላል ይላሉ:: በመጠኑ እውነት ነው:: በስሜት መቃወስ ምክንያት ተገቢ የሕይወት ብቃት ለሌላቸው ሰዎች ሐኪም ሊረዳ ይችላል:: የአእምሮን ጥልቅ ሃይል የሚያውቅ ዶክተር ያግዛል:: ከታች የሚወለድ ሕይወት ግን ጥራቱ ዝቅተኛ ነው:: ‹‹ሕይወት እንዲኖራቸውና እንዲበዛላቸው መጣሁ›› ካለው የኢየሱስ ቃል አይገናኝም:: (ዮሐ. 10፡10)::… ውስጣዊ ችግርና ጠማማ አስተሳሰብ መፍታት የተሻለ ብቃት አያስገኝም ማለት አደለም፤ ለዘላለም ሕይወት አያበቃም እንጂ! ውስጣዊ ግፊትና ደመ-ነፍስ መግታት ስሜትን ለማስተካከል ይረዳል፤ ወደ እግዜር መንግሥት ለመግባት ግን ተፈላጊ ለውጥ አያስገኝም:: ከታች በሚደረግ ለውጥ ሰው መሻሻልና መሰልጠን ይችላል - ግን ያው ኃጢአተኛ ነው! ሽክፍክፍ ያለ ኃጢአተኛ! … ለእውነተኛ ሕይወት ከላይ መለወጥ ያስፈልጋል!

ለሰው ከተገለጹ አስደናቂ እውነታዎች ትልቁን፣ ማለት ኃያል አምላክ ከላይ ወርዶ፣ እርሱን እንድንመስል እርሱ እኛን መምሰሉን እንመርምር:: የክርስቶስ ወደ ዓለም መምጣት አስደናቂ ሐቅ ተተረከ፡- ‹‹በባሕርዩ አምላክ ሆኖ ሳለ፣ ከእግዜር መተካከልን ሊለቅ እንዳይገባ አድርጎ አልቆጠረም፣ ግን የባሪያን መልክ ይዞ በሰው አምሳል ተገኝቶ ራሱን ባዶ አደረገ፣ ሰው ሆኖ ተገልጦ ራሱን ዝቅ አደረገ፣ … እስከ ሞት፣ ያውም በመስቀል እስከ መሞት ታዛዥ ሆነ›› (ፊልጵ. 2፡ 6-8):: … እግዜርን ለማወቅ፣ ወደ ‹‹ወሰን-አልባው›› መውጣት አያስፈልገንም፤ ወሰን-አልባው በፍቅር ወደ ‹‹ውስኑ›› ወረደ! ሰው ሆነ!

እኛ ወደ አምላክ መውጣት፣ ወይም እርሱ እንዳይወርድ መከልከል እንደማንችል ስናውቅ፣ የኩራት ከንቱነት ሲገባን፣ የእኔነት እምቡጥ ይደርቃል:: ‹‹ጥረን-ግረን እንድናለን›› የሚል እብጠት ይሟሸሻል! … አንድ እውነት በሕሊናችን ይታተም! ክርስቲያናዊ ለውጥ፣ እግዜር እኛን ለማግኘት ያደረገው እንጂ እኛ እርሱን ለማግኘት የምናረገው የጥረት ውጤት አይደለም! እኛ ከመለወጣችን በፊት እርሱ መለወጥ ነበረበት - እርሱን እንድንመስል ወደ እኛ አምሳል መለወጥ ነበረበት! ጽንፈ-ዓለምን የፈጠረ ታላቅ አምላክ፣ ከ2000 ዓመት በፊት በሕጻን መልክ በታየባት ቤቴልሔም ውስጥ ተለወጠ! ስነ-መለኮት አዋቂዎች ‹‹ትምሕርተ-ሥጋዌ›› አሉት - ‹‹አምላክ እንደ እኛ ሆነ›› ማለት ነው:: እግዜር ወደ እኛ አምሳል ባይለወጥ፣ ወደ እርሱ መለወጥ አንችልም ነበር!!


ወሳኝ ጥያቄ እንጋፈጥ፡- ‹‹ክርስቶስ መጥቶ እግዜርን መግለጡ በቂ ነበር? ማመን ያለብን ያን ብቻ ነው?›› መልሱ ‹‹አይደለም›› ነው:: እግዜርን ሊያሳየን ብቻ አልመጣም፤ ሊቤዥንም እንጂ! የመጥምቁ ዮሐንስ አባት ዘካርያስ እንዲህ አለ፡- ‹‹ሕዝቡን መጥቶ የተቤዠ እግዚአብሔር ይባረክ›› (ሉቃስ 1፡68):: ጎብኝቶን ብቻ ሊቤዠን ቻለ:: ደመና ላይ ተቀምጦ ሰማያዊ ትዕዛዝ አልሰጠም፤ በኃጢአታችን አቧራ እጁ እንዳይቆሽሽ በሰማያዊ ጉጠት ለቀም አርጎ መንግሥተ-ሰማይ አልወሰደንም:: ይልቅ በመሐላችን ኖረ! በድሕነታችን፣ ፈተናችን፣ ችግራችን፣ ፍላጎታችን፣ ጥላቻችን መሐል ኖረ፤ ከሁሉ በላይ በኃጢአታችን መሐል ኖረ፣ … ግን ያለ ኃጢአት ኖረ!

ከሁሉም ሰብዓዊ አስፈልጎቶች (Needs) ተጣመረ፤ በሰው ረሃብ ተራበ፣ በሰው ሕመም ታመመ፣ በሰው እስራት ታሰረ፣ በሰው ብቸኝነት ተካፈለ፣ በሰው ጥማት ተጠማ፤ በሰው ኃጢአት ግን አልተካፈለም!…በጽንፈ-ዓለም ፍ/ቤት ኃጢአት የከመረብንን አስፈሪ ዕዳ ሊከፍልግን የኛን ኃጢአት መሸከም መረጠ፤ በብር ሳይሆን በደም ከፈለ! ‹‹የእግዜር ጠላቶች ሳለን በልጁ ደም ከእርሱ ጋር ታረቅን… ሕይወቱን ለወዳጆቹ አሳልፎ ከመስጠት የሚበልጥ ፍቅር ማንም የለውም›› (ሮሜ፡5፡10፤ ዮሐ.15፡13)::

‹‹… ድምጹን ስለሚያውቁ ይከተሉታል›› እንዲል (ዮሐ. 10፡ 4)፣ ክርስቶስን መከተል መላ ስብዕና ያነቃል! ከርታታ ፕላኔታችን ወደ አዲስ ምሕዋር ትገባለች! …አንዳዶች ይጠይቃሉ፡- ‹‹እርሱን ከመከተል በፊት ስለ እርሱ ሁሉን ማወቅ አለብን?›› … የለብንም! ሁሉን ለማወቅ ከጠበቅን፣ መከተል አንጀምርም:: ስለ ኤሌክትሪክ የሚያውቁ ጥቂት ናቸው፤ ትሩፋቱ ግን ለቢሊዮኖች ነው:: ታዋቂ ፊዚስት ሰር ኬልቪን እንዲህ አሉ፡- ‹‹’ኤሌክትሪክ በትክክል ምንድነው?’ ቢሉኝ እንደማላውቅ መናገር አለብኝ:: እስከማውቅ ብዬ ግን በጭለማ አልኖርም:: ብርሃን እፈልጋለሁ፤ ብርሃን ‘ሚሰጥ ደሞ ኤሌክትሪክ እንደሆን አውቃለሁ::››ስለ ክርስቶስ የማናውቃቸው አንድ ሺህ አንድ ነገሮች ነበሩ:: ኃይልና ጎልምዎቱን ለመለማመድ ግን ሁሉን እስክናውቅ መጠበቅ እንደሌለብን እናውቅ ነበር::

ለሰዎች ሶስት ምልከታ አለን - ወይ እንርቃቸዋለን፣ ወይ እንጠላቸዋለን፣ ወይ እንጠጋቸዋለን! የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ በውነተኛ ለውጥ ይጠፋሉ:: ከሰው መራቅ እንተዋለን! ጥላቻ እናቆማለን! … አዲስ የተለወጠ ክርስቲያን እንዲህ አለ፡- ‹‹ጠብ ያለሽ በዳቦ ነበርኩ:: ካገኘሁት ጋር እጣላ ነበር! … ስለወጥ ግን፣ የቦክስ ጓንቶቼ ወለቁ:: በቡጢ ሰው የሚቀልቡ እጆቼ ሰው መጨበጥ ጀመሩ!››:: ስንደመድም፣ ጽንፈ-ዓለምን ሰንጥቆ የሚያልፍ ሥልጣናዊ መስመር አለ፤ ኢ-ልውጥን ከልውጥ ይለያል! በእግዜር እንጂ በሰው አልተሰመረም! … መጀመሪያ እግዜር ራሱ የሰው ሥጋ ለበሰ፤ እግዜር ምን እንዲመስል በደንብ አሳየን! … ከታሪክ ታላላቅ ቅጽበቶች አንዱ የፊሊጶስ ጥያቄ ሆነ፡- ‹‹አብን አሳየንና ይበቃናል::›› ኢየሱስ መለሰለት፡- ‹‹እኔን ያየ አብን አየ›› (ዮሐ.14፡9):: መልካም የገና በዓል!

> ለሰዎች ሶስት ምልከታ
> አለን - ወይ እንርቃቸዋለን፣
> ወይ እንጠላቸዋለን፣
> ወይ እንጠጋቸዋለን!
> የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ
> በውነተኛ ለውጥ ይጠፋሉ



አቤል መንግሥተአብ

# "ልውጥ" እና "ኢ-ልውጥ"

ሁለት ሴቶች ዘንጠው ትልቅ ሆቴል ሲዝናኑ፣ የምታውቃቸው ሴት መጣችና፡- ‹‹ምን ተገኘ? ሽክ አላችሁብኝ!››አለቻቸው:: ‹‹የቤቢ ልደት እኮ ነው!››:: ‹‹ቤቢ ታዲያ የታለ?››:: ‹‹ለእማዬ ጥለነው መጣን! ቤቢን ይዘን መዝናናት አንችልም፤ ያስቸግረናል!››::... (‹‹ባለ 'ልደቱ' ተጥሎ እቤት፣ ጨፈሩ እነሱ ቀን ከሌት!››ይሏል ይህ ነው::)... ‹‹ክርስቲያን በሁለት ነገር ይታወቃል›› አሉ መምሬ፤ ‹‹ከእግዜር ጋር ስለ ሰዎች ያወራል፤ ከሰዎች ጋር ስለ እግዜር ያወራል::›› ... ብዙዎች ከእግዜር ጋር ስለ ሰዎች ያወራሉ፤ ከሰዎች ጋር ግን ስለ እግዜር አያወሩም!... በተለይ በዕለተ-ልደቱ ስለ ጌታ ማውራት ተገቢም አግባቢም ነው! ማሕበራዊና ፖለቲካዊ ቅቡልነት ባላቸው ጉዳዮች ብቻ ሳንወሰን፣ገድሉን እንተርክ! ለውጡን እናብስር! ... መልካም ንባብ! ...

* * *

በሆንግኮንግ የተሰበሰቡ 29 የቤተስኪያን መሪዎች የለውጥ ግንዛቤ ጠፋ አሉ! አደጋ እንዳለው አስጠነቀቁ!...በርግጥም ዓመት ሙሉ ቤተስኪያን ብንቀመጥ ስለ ‹‹ለውጥ›› ላንሰማ እንችላለን:: ስለ ‹‹ስነ-ምግባርና ባልንጀራን መርዳት›› እንሰማለን፤ ስለ ለውጥ ግን ብዙ አንሰማም!‹‹ካልተለወጣችሁ ... መንግሥተ ሰማይ አትገቡም›› አለ መጽሐፍ (ማቴ. 18፡3):: በብሉይ እና አዲስ ኪዳን 150 ጊዜ ስለ ለውጥ ተጻፈ!

‹‹ልውጥ›› እና ‹‹ኢ-ልውጥ›› ተብለው ሰዎች በእግዜር ተከፈሉ:: ጥቁር፣ ነጭ፣ ሃብታም፣ ድሃ፣ ምሑር፣ መሃይም፣... ዓይነት ክፍፍል ትርጉም አጣ:: "ልውጥ ወይ ኢ-ልውጥ" እንጂ፣ የት ወይ እንዴት ተወለድን ወሳኝ አይደለም:: ሁለተኛው እንጂ የመጀመሪያው ልደት ዘላለማዊ ዕጣችንን አይወስንም! ... ለድሃና ጎስቋላ ብቻ ሳይሆን ለሃብታምና ቱጃርም ‹‹ለውጥ››አስፈለገ:: ሰለጠኑ ከሚባሉት ጀርባ ባዶነትና መንፈሳዊ ክስረት አለ:: ከእግዜር የማይኖር ከራሱ አይኖርም! የነፍሳቸውን ችግር ወደ አካላቸው ባስተላለፉ ‹‹ጭንቀታሞች›› የሐኪሞች ቢሮ ተጨናንቋል:: የሳይካትሪስቶች ደሞ ይብሳል፤ አንዳንዴ ሳይካትሪስቱ ራሱ ጥብብ ይለዋል:: የመፍትሔ ሳይሆን የችግሩ አካል ይሆናል:: (ከተራ ሰዎች ይልቅ በፕሮፌሽናሎች ዘንድ ራስ-ማጥፋት ይበዛል::)

ያልተለወጠ ሕይወት ትርጉመ-ቢስ ነው:: የዘመኑ መለያ ፍሬ-ቢስነት እንደሆን ታዋቂ ሳይንቲስት ካርል ጀንግ ተናገሩ:: ባይታወቀው እንኳ፣ 21ኛ ክ/ዘመን ‹‹ድነት እና ለውጥ›› ተጠማ:: ጽንፈ-ዓለምን ዓላማ-ቢስ ማድረግ የዘመኑ ባሕርይ እንደሆን አሜሪካዊ ፕሮፌሰር ገለፁ:: ሕዝባቸው በጭንቀት መናጡን ጃፓናዊ ዶክተር በቴሌቪዥን ቀርበው ተናገሩ -‹‹ውስጣዊ ባዶነት›› አሉት:: ‹‹ውስጤ ባዶ!›› የሚል ጩኸት ሞላ:: ግን ተሸፋፈነ፤ በክሕደት ካባ ተጀቦነ!

በኢየሩሳሌም በተካሄደ የፈላስፎች ጉባኤ ዶ/ር ሆኪንግ እንዲህ አሉ፡- ‹‹ሰው ራሱን እስከተወሰነ ደረጃ ያደርሳል፤ ፍጹም ለመሆን ግን ግብዓት እንደሌለው ያውቃል፤ ከራሱ ውጭ፣ ከራሱ በላይ በሆነ ነገር ፍጹም ይሆናል!››... ዶ/ሩ ‹‹ለውጥ›› አላሉም! ‹‹በሆነ ነገር ...›› ብቻ አሉ:: አንድ ካሕን ግን አለቀቃቸውም:: ‹‹ዶ/ር ሆኪንግ፣ ምነው ቃሉን ዘለሉ?››፣ ‹‹የቱን ቃል?››፣ ‹‹'ልውጠት' 'ሚለውን!›› ... ‹‹እኔ ፈላስፋ ነኝ፤ ቃሉን ልል አልችልም፤ እርሶ ካሕኑ በሉት!››:: ‹‹ወደኔ አያዙሩ፤ እርሶ ካወቁት ራስዎ በሉት››:: ሆኪንግ በአንደምታ ወይ በገላጭ-ዝምታቸው ልውጠትን ገለጹ! ... ሰውን ፍጹም የሚያደርግ ግብዓት ፍልስፍና አይሰጥም:: ሳይካትሪም እንደዛ ነው:: ከራሱ እንዲስማማ ሰውን ይረዳል፤ ከእግዜር ማስማማት ግን አይችልም፤ ዕውቀት የለውም:: ታዋቂው ሳይካትሪስት፡- ‹‹ሃይማኖት ያስፈልገኛል፤ ታካሚዎቼ አምጣ ይሉኛል፤ ከሌለኝ ምን ልስጣቸው?›› ማለቱ የማይደንቀው ለዚህ ነው::

ባዶነት ተንሰራፍቶ፣ ሰው ደፈር የማይል ለምንድነው? ‹‹ለውጥ›› የማይለው ለምንድነው? ምክንያቱ ኩራት ነው! (በዘመኑ አባባል፡- ራስ-መቆለል ነው):: ‹‹ችግሬን ራሴ እፈታለሁ›› እንላለን:: ‹‹መለወጥ አንችልም›› ማለት ይከብደናል፤ ክብራችንን ያቆስላል:: የቆለልነው ማንነት ይናዳል:: ኩራት መንፈስ ያደነድናል፤ ውጫዊ እገዛ ይቃወማል:: በጥረታቸው ክርስቲያን መሆን 'ሚሞክሩ ስሕተታቸው ይህ ነው:: ራሳቸውን ለማሻሻል የማይቆፍሩት የለም፤ ማሻሻል ከሚሹት ከዚያው ማንነታቸው መዳን እንዲያስፈልጋቸው አያውቁም!

በዓለም ላይ ብዙ ለውጥ አለ:: ክርስቲያናዊ ለውጥ ግን ይለያል፤ ቀን ከሌት እንደሚለይ ይለያል! ከፍተኛ የሕይወት ውጤት የሚያስገኝ ይዘት አለው:: ... ሕይወት ሁሉ ለውጥ ነው:: ሁሉ ነገር ይለወጣል:: ውሃና አየር የዕጽዋት ምግብ እንዲሆን፣ የፀሐይ ጉልበትን ለዋጭ ሂደት (ፈውቶ'ሲንተሲስ) እንውሰድ:: ይህ ለውጥ ከሌለ ሕይወት የለም:: የሰው ልጅ ሲወለድ ለውጥ ይጀምራል - ምግብ ወደ ጉልበትይለወጣል፤ ጉልበት ወደ ክንውን ይለወጣል:: የኢንዱስትሪ ዓለም በለውጥ ላይ ተመስርቷል - ጥሬ-ዕቃ ወደ ምርት ይለወጣል:: ... ምድራዊ ሕይወት ሁሉ ከትንሽ ወደ ትልቅ ይለወጣል፤ ማዕድን ወደ አትክልት ይመጠጣል፤ አትክልት ወደ እንስሳ፣ እንስሳ ወደ ሰው! ... እኒህ ግዛቶች መናገር ቢችሉ፡- ‹‹ከኔ በላይ ግዛት የለም›› ባሉ ነበር:: ‹‹ከሚነራል በላይ የለም›› ይላል የማዕድን ግዛት፤ ግን

ቀሪውን በገጽ 27 ይመልከቱ

# ግዮን መጽሔት


በአጭር ጊዜ ገበያ ውስጥ ለመግባት
የቻለችው ግዮን የእርስዎ መፅሔት

## በየሳምንቱ ቅዳሜ ከእጅዎ ትደርሳለች።



+251 911 227661
+251 912 165606
+251 118 122333

www.faceboook.com/enqu2013
**Facebook**
Gihon-meg Fekadu
**ኢ-ሜይል:**
enqu2013@gmail.com




# አዲስ መጽሐፍ በገበያ ላይ ዋለ

## አሳታሚና አከፋፋይ ጃፋር መጽሐፍት መደብር